

ማውጫ

ገጽ

የመግቢያ ውል (ስምምነት) . . . . . .
ዝርዝር ማስጠነቀቂያ . . . . . .

1. ምዕራፍ አንድ - እኔን የሚያስተዋውቅ . . . . . .
2. ምዕራፍ ሁለት - ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ጌታ ነው. . . . . .
3. ምዕራፍ ሦስት - አንተ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ነህ? . . . . . .
4. ምዕራፍ አራት - ደቀመዛሙርት ዋጋ ስለ መክፈል . . . . . .
5. ምዕራፍ አምስት - የእግዚአብሔር ቅርጽ ያላት ቤተክርስቲያን . . . . . .
6. ምዕራፍ ስድስት - የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የሚጠራጠር ሕይወት ይወድቃል. . . . . .
7. ምዕራፍ ሰባት - የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት የሚለማመድ ክፍል ቡድን . . . . . .
8. ምዕራፍ ስምንት - የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ነፍስን መማረክ. . . . . .
9. ምዕራፍ ዘጠኝ - በደስታ የጌታ ደቀ መዝሙርት መሆን . . . . . .



ማውጫ

ምዕራፍ አንድ - ስለ ሌሎች የመፀለይ ጥሪ .....
ምዕራፍ ሁለት - በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሌሎች ፀሎት.....
ምዕራፍ ሦስት - ስለ ለሌች መፀለይና የመንፈስ ጦርነት.....
ምዕራፍ አራት - በስልጣን ስለሌሎች መፀለይ .....
ምዕራፍ አምስት - ስለሌሎች መፀለይና በዓለም ላይ ወንጌልን መስበክ.....
ምዕራፍ ስድስት - ስለሌሎች የፀሎት ልምድ፤ ስለሌሎች የፀሎት ልዩ ወታደር.....





የደቀመዛሙርት ሕይወት

መግቢያ

በዚህ ዘመን ሰዎችን ክፍቶ ሰዎች ጊዜውን ክፍት ነው፡፡ ይህ የሆነው ሥራውን የሚያከናውን ሰዎች ሳይወለዱ የሚሥሩት ነገር ነው፡፡ የዓለም ራዕይ ደቀመዛሙርት ዩንቨርሲቲ ዳግመኛ የተወለዱ የሚሰጠውን ትምህርት የሚለማመዱ ክርስቲያኖች ጥሩ ወታደር ሆነው እንዲወጡና ታማኝ ወታደሮች እንዲሆኑ የሚያበቃበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ የሠለጠኑት ክርስያኖች በመንፈሳዊ ነገር ጥሩ ወታደራዊ መሪዎች እንዲሆኑ የሚያደርግበት ቦታ የዓለም ራዕይ የደቀ መዛሙርት ዩንቨርሲቲ ነው፡፡ በዚህ ዩንቨርሲቲ ሦስት ሴሚስተሮች አሉ፡፡ 1ኛ. ሴሚስተር የደቀመዛሙርት ሕይወት፣ 2ኛ. ሴሚስተር የወታደሪነት ሕይወትና 3ኛ. ሴሚስተር እንደገና ደቀመዛሙርት የማድረግ ሕይወት ናቸው፡፡

የ1ኛ ሴሚስተር ግብ፡ - በወንጌል ስበከት በትንሽ ቡድን የክፍት ስብከት መሪ ማድረግ ነው፡፡
የ2ኛ ሴሚስተር ግብ፡ - ደግሞ የክፍል መሪዎችን ማድረግ ነው፡፡
የ3ኛ ሴሚስተር ግብ፡ - በየክፍላቸው እና በየቡድናቸው ተማሪዎችን በመገንባት እንደገና ደቀመዛሙርት ማድረግ ነው፡፡

ግብ ያለውን ሥራ መሥራት አስፈላጊ ነው፡፡ ልምምድ ሲኖር ግቡ ወንጌልን የሚሰብክ ደቀመዛሙርት፣ ክፍል መሪዎች ይገነባሉ፡፡ እነዚህ ደቀመዛሙርት ታንጸው የየራሳቸውን ሥራ እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ.28÷18-20 ባለው ክፍል ላይ "እናንተ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ አህዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዘሙርት አድርጋአቸው" ብሎ የመጨረሻውን የኑዛዜ ቃል ተናገረ፡፡ ይህ ኑዛዜ እኛ ሊናደርግው የሚገባ ተልዕኮ ነው፡፡ጌታ ኢየሱስ በራሱ ፋንታ በምድር በኖርበት ጊዜ ቀጣዩን ሥራ እንዲሠሩ ደቀመዛሙርቱን በማስተማር በእነርሱ ላይ ብዙ ጊዜና ጉልበት ወስዶአል፡፡ የደቀመዛሙርት የልምምድ (የሥልጠና) ትኩረት የሐሳብ (የዋጋ) ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ለየተኛው ነገር ዋጋ መስጠት እንዳለብን ሕይወታችንን በመፈተሽ ጉዳዩን በማረጋገጥ መፍተሔ የሚናገኝበትን አቅጣጫ አሳይቷአል፡፡ ለዓለም ነገር የምንሰጠውን ዋጋ ለእግዚአብሔር መንግሥት ዋጋ ይበልጥ የምንሰጥበት ዓይን ቢከፈት ሁሉም ሰዎች ፍጹም ይለወጣሉ፡፡

የደቀ መዛሙርት 1ኛ ሴሚስተር "የደቀ መዛሙርት ሕይወት" በሚለው ኮርስ ስለደቀ መዛሙርት ትርጉም፣ ጥሪና ዋጋ ስለመክፈል መማር ይቻላል፡፡ የደቀ መዛሙርት ሕይወት ማለት ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መውሰድ፣ ማምጣት ማለት ነው፡፡ ይህንን የመጀመሪያ ሴሚስተር ኮርስ የተማረ ክርስቲያን የክፍት ስብከት መገንባት ይችላል፡፡ የዚህ ሴሚስተር ማለትም የደቀ መዛሙርት ሕይወት የዋጋ ለውጥ መሠረታዊና ብዙ የሚለወጥበትም ደረጃ ስለሆነ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ በዚህ ኮርስ ብዙ ሰዎች ስለ ደቀመዛሙርት ጥሪና ዋጋ ስለመክፈል ዓይኖቻቸውን ከፍተው ሌሎች ሰዎችን ወደ ጌታ የሚማርኩ እንዲሆኑ ተስፋ ይሰጣል፡፡

ማውጫ

ገጽ

የመግቢያ ውል (ስምምነት) . . . . . .
ዝርዝር ማስጠነቀቂያ . . . . . .

1. ምዕራፍ አንድ - እኔን የሚያስተዋውቅ . . . . . .
2. ምዕራፍ ሁለት - ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ጌታ ነው. . . . . .
3. ምዕራፍ ሦስት - አንተ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ነህ? . . . . . .
4. ምዕራፍ አራት - የደቀመዛሙርትን ዋጋ ስለ መክፈል . . . . . .
5. ምዕራፍ አምስት - የእግዚአብሔር ቅርጽ ያላት ቤተክርስቲያን . . . . . .
6. ምዕራፍ ስድስት - የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚጠራጠር ሕይወት ይወድቃል. . . . . .
7. ምዕራፍ ሰባት - የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት የሚለማመድ ክፍል ቡድን . . . . . .
8. ምዕራፍ ስምንት - የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ነፍስን መማረክ. . . . . .
9. ምዕራፍ ዘጠኝ - በደስታ የጌታ ደቀ መዝሙርት መሆን . . . . . .

★ የመግቢያ ውል (ስምምነት)

እኔ ይህንን "የደቀ መዛሙርት ሕይወት" ልምምድ በሚቀበልበት ጊዜ ከዚህ በታች ያሉትን ሥርዓቶችን (ሕጎችን) ለመፈጸም አስቀድሜ በፈቃደኝነት በእግዚአብሔር ፊት ቃል እገባለው፡፡

1. እኔ የኢየሱስ ጥሩ ደቀ መዛሙርት ለመሆን በመጀመሪያ በጠንካራ ፍላጐትና እምነት ሥልጠናውን እከታተላለሁ፡፡
2. ኢየሱስ ክርቶስን በየቀኑ የሕይወቴ ጌታ አድርጌ ራሴን በመካድ ለእርሱ እታዘዛለሁ፡፡
3. በኃይለኛ ሕመም ሁኔታ በስተቀር በክፍል ለመገኘት እጥራለሁ፡፡
4. በየሣምንቱ የሚሰጠውን የቤት ሥራ በታማኝነት እሠራለሁ፡፡
5. ቃል፣ ፀሎት፣ ምስክርነት፣ ከሌሎች ጋር ያለው ህብረት፣ አምልኮና አገልግሎት ወዘተ. . .የሰርከ ሕይወት መሠረት እንደሆነ በማመን ይህንን ሕይወት በታማኝነት አደርጋለሁ፡፡
6. በየእሁዱ ወደ ቤተክርስቲያን በመምጣት ለጌታ ቤት ክርስቲያን የሚሰጠውን ገንዘብ፣ ንብረት የተለያዩ ነገሮች በመስጠት አገለግላለሁ፡፡

7. በቃሉ በኩል ሕይወቴን ለማስተካከል እየሞከርሁት ራሴን ከትዕቢትና ከፖለትካ ነገር ነጻ በማድረግ ሁልጊዜ የሚሰጠኝን አስተያየት በትህት እቀበላለሁ፡፡
8. ሥጋንና መንፈስን የሚፈውስ ኮንፋራንስ፣ ክፍት ስብከት፣ ክፍል ቤተሰብ ስበከትና ስለመሪዎች በሚሰጠው ልምምድ ለመገኘት እጥራለሁ፡፡
9. ለሚያለማምደው (ሥልጠና ለሚሰጠው) አስተማሪ በመውደድ ስለ እርሱ በታማኝነት እፀልያለሁ፡፡
10. አብሮ ለሚማሩ ሠልጣኞች እፀልያለሁ፤ ደግሞም ለሚያስፈልጋቸው ርዳታ በማድረግ እሳተፋለሁ፡፡
11. ለሕማን በመታዘዝ ሲያዝዙኝ እታዘዛለሁ፡፡
12. "የደቀ መዛሙርት ሕይወት" ኮርስ በሚወስድበት ጊዜ ችግር ሲኖር በፀሎት ለማሸነፍ እሞክራለሁ፡፡

ዓመት፡ _____ ወር፡ _____ ቀን፡ _____

★ ዝርዝር ማስጠነቀቂያ

1. "የደቀ መዛሙርት ሕይወት" ለመለማመድ እንደመጣህ በእምነት ተቀበል፡፡
2. የሚያለማምድህን አስተማሪህን በመውደድ ስለ እርሱ በትርፍ ጊዜህ በታማኝነት ለመፀለይ ትጋ፡፡
3. ቀሪነት ላለማብዛትና በትምህርት ላለመውደቅ ሞክር፤ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ መቅረት አደጋ ስለሆነ ርዳታ ወደሚሰጡ ሰዎች ዘንድ ለመሄድ ጥረት አድርግ፡፡
4. ለምምድ ሲትቀበል በአንደኛ ደረጃ ላይ የደቀ መዛሙርት ዩንቨርሲቲ አስቀምጥ፤ የክርስቲያኖች ታላቅ በረከት የመንሳዊ ሕይወት ማደግ ነው፡፡ "የደቀ መዘሙርት ሕይወት" የሚለውን ኮርስ በሚትቀበልበት ጊዜ ሕመም ሲኖርብህና ልቅሶ በሚያጋጥምህ ጊዜ መማር አይቻልም፡፡ የተዕልኮ ሰው አይሞተም፡፡
5. ከትምህርት ቤት የተሰጠውን የቤት ሥራ ፍጹም ሊትሠራ ይገባሃል፤ የቤት ሥራ በመስራትና ባለመስራት ውስጥ ከፍተኛ ልዩነት አለ፤ ያ ደግሞ ያንተ የልብ አቋም ምን ዓይነት እንደሆነ ይገልጻል፡፡
6. በየሳምንቱ ትምህርቱ የሚያዝዘው የቤት ሥራ አስቀድሞ የመስራት ልምድ ይኑርህ፡፡
7. የሰርከ መሠረታዊ ሕይወት በራስህ ሕይወት እየተለማመድህ እርሱ የሚያዝዘውን 6 ዓይነት ሕይወትና የቤት ሥራ እየሠራህ ለራስህ ነጥብ ስጥ፡፡
8. በሥጋና በነፍስ ልትሠለጥን ያስፈልጋል፤ አስተማሪህ አንተን ሊቀይርህ አይችልም፤ አንተ ትምህርቱ የሚለውን (አውድ) በሕይወትህ ሊትተግብርና ሕይወትህን ሊታስተካክል ይገባሃል፤ ይህ ደግሞ ዕውቀትና ፍላጎት በማሳደር ሥጋህንና ነፍስህን ያሳድጋል፡፡
9. ወደ አምልኮ ስፍራ፣ ወደ ክፍል ቤተሰብ ስብከትና ወደ ክፍል ስብከት ለመምጣት ጥረት አድርግ፤ ወደ ደቀ መዛሙርት ዩነረቨርሲቲ የገባኸው አንተ ሕይወትህን የሚታስተካክልበት ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነ አውቀህ ለምምድ ሊታደርግ ይገባሃል፡፡
10. አብሮ የሚሠለጥኑ ተማሮዎችን በመውደድ ስለ እነርሱ ሊትፀልይና እነርሱን ሊታገለግል ይገባሃል፤ ምክንያቱም እነርሱ ያንተ ጓደኞች ናቸው፡፡

ሉቃ. 9÷23 "ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡፡ በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡"

ምዕራፍ አንድ
እኔን የሚያስተዋውቅ

● ሐዋ. 26÷9-23

9-እኔም ራሴ የናዝሬቱን የኢየሱስን ስም የሚቃወም እጅግ ነገር አደርግ ዘንድ እንዲገባኝ ይመስለኝ ነበር።

22-23 ከእግዚአብሔርም ዘንድ ረድኤት ተቀብዬ ለታናሹም ለታላቁም ስመሰክር እስከዚች ቀን ድረስ ቆሜአለሁ፤ ነቢያትና ሙሴ ይሆን ዘንድ ያለውን፥ ክርስቶስ መከራን እንዲቀበል በሙታንም ትንሣኤ ለሕዝብና ለአሕዛብ ብርሃንን በመጀመሪያ ሊሰብክ እንዳለው፥ ከተናገሩት በቀር አንድ ስንኳ የተናገርሁት የለም።

እኔ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት እንዳመንሁ የሚገልጽበት የምስክርነት ክፍል በጣም ወሳኝ ነው፡፡ እግዚአብሔር እኔ ከእርሱ የተቀበልሁትን ፀጋን ለሌሎች ሰዎች እንዳካፍል ይፈልጋል፡፡ በመዝ.145÷1 ላይ ንጉሡ ዳዊት እግዚአብሔርን እንደዚህ እያለ ያመሰግናል፡፡ "አምላኬ፤ ንጉሤ ሆይ፤ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፤ ስምህንም ለዘላለም ዓለምም እባርክለሁ፡፡ በቁጥር 7 ላይ ደግሞ እነርሱ የቸርነትህን ብዛት መታሰብ ያወጣሉ፤ በጽድቅህምሐሤት ያደርጋሉ፡፡ በማለት የራሱን ድምጽ ከፍ በማድረግ ያመሰግናል፡፡ ዳዊት የእግዚአብሔር የልቡ ሰው ሆኖ ተስማምቶ እንዲኖር ያደረገው በየቀኑ በሕይወቱ የእግዚአብሔርን ስም ከፍ ከፍ እያደረገ በምስጋና ሕይወት በመኖሩ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተባረኩ ሰዎች ተብለው የተመሰከሩ ከዚህ በታች ያሉት ናቸው፡፡ እነርሱም አብርሃም፣ ሙሴ፣ ዳዊት፣ ሣሙኤል ወዘተ. . .ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች በብዙ ተቃወሞ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ንሰሐ እየገቡ ፀጋን (በረከትን) እንደተቀበሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል፡፡ ስለዚህ እኛ ደግሞ ከእነርሱ ልምድ የምንማር ሰዎች ነን፡፡ ምክንያቱም እኛ በግልጸኝነት ልባችንን ከፍተን ሕይወታችንን እየገነባን ስለሌሎች ሕይወት የሚሰማን ሰዎች ሊንሆን ይገባናል፡፡ የጌታ ልጆች የሆኑት

ሲሰበሰቡ ስለ እነርሱ በጌታ ፊት ንሰሐ እየገባን በረከትን (ፀጋን) እየተከፋፈለን በግልጻችነት አብረን እየተረዳዳን ሊናድግና ይህንን ፀጋ ሊንከፋፍል ደግሞም በዚህ ልምምድ ደስተኞች ልንሆን ይገባናል፡፡

የመጀመሪያ ግብ፡- በልምምድህ ጊዜ ሕይወትን ሌሎች አካፍል፡፡
የሁለተኛ ግብ፡- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እምነትህን መመርመር (መፈተሽ)

1. የሕይወት ታሪክ ምስክርነት ቃል ማለት ሕግ የሚያዝዘውን የምንገልጽበት ሥፍራ ማለት ነው፤ የሕግ ቢሮ ትክክለኛ የሆነ ነገር የሚናገርበት ቦታ ነው፡፡ እኛ ክርስቲያኖች አስፈላጊ ከሆነ እግዚአብሔር ለእኛ በሚሰጠው ፀጋ ሁሉንም መተረጎም ነው፡፡ የምስክርነት ግብ እግዚአብሔርን ማክበርና ስለ ተሰጠን ፀጋ እርሱን ማመስገን ነው፡፡ ምስክርነት ማለት ምን ማለት ነው? ምስክርነት ማለት የራሱን ቃል እንደገና አስተካክሎ (አደራጅቶ) መናገር ማለት ነው፡፡

1) ዮሐ.4÷39 ላይ የሰማሪያ ከተማ ሴት የተናገረችው የምስክርነት ቃል እንዲህ የምል ነው "ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ" በማለት መሰከረችው፡፡ ምስክርነት ማለት እግዚአብሔር የሰጣትን ፀጋ መልሳ ለሌሎች ሰዎች ተናገረችው ማለት ነው፡፡

● ዮሐ.4÷39
39-ሴቲቱም። ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ስለ መሰከረችው ቃል ከዚያች ከተማ የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት።

2) የዐይነ ስውር ሰው የምስክርነት ቃል እንዲህ የምል ነው፤ ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም፤ ዕውር እንደነበርሁ ጭቃ በዓይኖቼ ላይ ቀብቶ ሂድ በሰሎሆም መጥመቂያ ታጠብ አለኝ እኔም ሄጄ ታጠብሁ እያየሁ መጣሁ ብሎ መሰከረ፡፡

● ዮሐ.9÷25
25-እርሱም መልሶ፡- ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም፤ ዕውር እንደ ነበርሁ አሁንም እንዳይ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ አለ።

3) 1ዮሐ.1÷3 ላይ ያለው የምስክርነት ቃል ያየውንና የሰማውን ቃል መናገር ነው፡፡

● 1ዮሐ.1÷3

3- እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን። ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።

2. እኛ ለምን እግዚአብሔር የሰጠውን ፀጋ ለሌሎች ክርስቲያኖችና ላላመኑ ሰዎች እንመሰክራለን?
1) ማር.5÷19 ላይ ጌታ ኢየሱስ በጌርጌሴኖን አገር በአጋንንት ተይዞ የነበረውን ሰው ፈውሶ "ሂድ ጌታ ያደረግልህን ለቤተሰቦችህ መስክር" ብሎ አዘዘ፡፡

★ ዲያብሎስ የተያዘ ሰው፤ ሕመምተኛ ሰው የሚለየው በምንድን ነው?
በዲያብሎስ የተያዘው ሰው ጠንካራና ኃይለኛ ሲሆን ያንን ኃይል ብዙ ጊዜ የአገልጋዮች አይን አያይም፤ ምክንያቱም በአይናቸው ፊት ጨልሞ ስላላቸው እጆቻቸውን ሲጭኑ ብቻ ያ ነገር ይታያል፡፡ በሽተኛው (ሕመምተኛው) ግን ሰውነቱ ከበሽታው የተነሳ የተጎዳ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም የበሽታ ዓይነቶችን ይፈውሳል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን በአጋንንት የተያዘውን ሰው ፈውሶ ለቤተሰቦቹ መስክር አለው፡፡ ስለዚህ የምስክርነት ሕይወት የሌለው ማለት መመስከር የማይችል ክርስቲያን እምነት የሞተ እምነት ነው፡፡ ሕያው ቤተክርስቲያ ምስክርነትን በየቀኑ የሚታደርግ ናት፡፡

● ማር.5÷19
19- ኢየሱስም አልፈቀደለትም፥ ነገር ግን። ወደ ቤትህ በቤተ ሰዎችህ ዘንድ ሄደህ ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ እንዴትስ እንደ ማረህ አውራላቸው አለው።

★ ማስጠነቀቂያ
በአጋንንት (በዲያብሎስ) የተያዙ ሰዎችን በሚታገኝበት ጊዜ ሥልጣንህን መከታ አታደርግ፤ ምክንያቱም ትኩረትህን በደቀመዛሙርት ልምምድ ላይ አድርግ፡፡ በዲያብሎስ የተያዘውን ሰው ሌሎች ሰዎች ከአዳራሹ አውጥቶ ወደ ሚፀልይበት ክፍል ሊወስዱ ይገባል፡፡

2) 1ጴጥ.2÷9 ላይ እንደምገልጸው የጌታን በጎነትን መናገር አለብን፡፡

● 1ጴጥ.2÷9
9- እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤

3) ሐዋ.1÷8 ላይ እንደምገልጸው ምስክሮች ሊንሆን ያስፈልጋል፡፡

● ሐዋ.1÷8
1 በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።
2- ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።
3- ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።

4- በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።
5- ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም።
6- ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤
7- ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ።
8- ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ፥ እርሱ ብርሃን አልነበረም።

4) ሚል.3÷16 ላይ እንደምገልጸው መጽሐፉን መጻፍ አለብን፡፡

● ሚል.3÷16

16- የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈሩ እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ እግዚአብሔርም አደመጠ፥ ሰማም፥ እግዚአብሔርንም ለሚፈሩ ስሙንም ለሚያስቡ የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተጻፈ።

5) መዝ.9÷1 ላይ እንደምገልጸው የጌታን ታምራት የሚንናገር (የሚንመሰክር) ሰዎች ሊሆን ያስፈጋል፡፡

● መዝ.9÷1

1- አቤቱ፥ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፥ ተአምራትህንም ሁሉ እነግራለሁ።

3. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመመስከር ምላሽን መቀበል

ሐዋ.26 ምዕራፍ ላይ የምገልጸው የሐዋሪያ ጳውሎስ ምስክርነትን ነው፡፡ሐዋሪያ ጳውሎስ ከመዳኑ በፊትና ደህንነትን ካገኘ በኋላ ያለውን የሕይወት ለውጥ በንስሐ እየተናገረ ይገልጻል፡፡

ከሐዋሪያ ጳውሎስ ምስክርነት 4 ዓይነት የምስክር ዘዴዎችን አግኝ፡፡

1) ኢየሱስ ክርስቶስን ከማመኑ በፊት ያለው ሁኔታ
ኢየሱስ ክርስቶስን ከማመንህ በፊት ሕይወትህ ምን ይመስላል? በሕይወት ብዙ መጥፎ ታርከችን መናገር አያስፈልግም፡፡

2) ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲታምን ያደረገህ ስሜትና ትምህርት ምንድን ነው?
ምሳሌ፡- የሚሰማ ሰው ሊረዳ የሚችለውን ነገር መናገር የተሻለ ነው፡፡ ሕይወቴ በመጀመሪያ ሥላም የሌለ ባዶ ነበር፡፡

3) በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ስለ ራስህ ሕይወት ንስሐ ግባ፡፡
በሕይወትህ ውስጥ ንስሐ የሚትገባበት ነገር ይኖራል፤ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡
በሚትመስክርበት ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ትኩረት አድርግ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተን እንደሚወድ፣ እንደምባርክ (ፀጋን እንደምሰጥ) ትኩረት ሊታደርግ ይገባል፡፡

4) ኢየሱስ ክርስቶስን ከተቀበልህ በኋላ ሕይወትህ የተለወጠው ነገር ምንድን ነው?
በሕይወትህ ውስጥ ስላለው ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ስቃይ፣ ብቸኝነትና ስለ ተለያዩ ችግሮች መፍተሔ አግኝተሃል? ለአንተ ታላቅ ስሜት የሚሰጠውን ትኩረት በማድረግ እውነተኛ የሆነውን ጻፍ፡፡ ሥላም የሰጠውን እምነትህም ያረጋገጠውን በውስጥህ አሁን ያለውን ስሜት ለሌሎች አካፍል፡፡ የሕይወትህን ታላቅ ልምምድ እንደ አንተ ኃጢአተኛ ለሆኑት ሰዎች እነርሱ ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወታቸው ጌታ (አዳኝ) አድርገው እንዲቀበሉ መስክር፡፡

★ ልምምድ የሌሉ ሰዎችን በቀላሉ ሊጥሉ የሚችሉ ነገሮች

1) ስለ እምነታቸው መጠራጠር፡፡
2) ስለ ወንጌል አለመመስከራቸው፡፡
3) በመንፈሳዊ ነገር ድኻ መሆን፡፡
4) ስለመዳናቸው አለማመስገናቸው፡፡

4. ሐዋሪያ ጳውሎስ በሐዋ. 22÷6-16 ላይ ስለ ራሱ ሕይወት በጌታ ፊት ንስሐ መግባቱን ይገልጻል፡፡ ከእርሱ ሕይወት ብዙ ነገር ሊንለማመድ እንችላለን፡፡ ነገር ግን አንተ እንደ ሐዋሪያ ጳውሎስ ልምምድ ከሌለ ምን ታደርጋለህ?

5. ምስክርነት የሚታከፋፍልበት አቋም እንዴት ነው?

1) ምስክርነትህን ከማከፋፈልህ በፊት ምስክርነትህን በጽሑፍ ካዘጋጀህ በኋላ በሌሎች ሰዎች እንዲካፈል ያስፈልጋል፡፡

2) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምስክርነትህ ማዕከል አድርገህ አቅርብ እንጂ የራስህን ታርክ አታንጸባርቅ፡፡ ከጥሩ ምስክርነት ሁል ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላንተ ምን እንደምሰጥ ያንኑን ትኩረት ሊታደርግ ያስፈልጋል፡፡

3) አንተ የተቀበልከውን ፀጋ ለሌሎች ሰዎች አካፍል፡፡ እግዚአብሔር ለአንተና ለእኔ የሰጠውን ፀጋ ለሌሎች ሊናካፍል ያስፈልጋል፡፡

4) በታማኝነትና በግልጸኝነት ተለማመድ፡፡ ስሜትና ውበት የሚሰጠውን አትጨምር፤ ምስክርነትህ ኃይል እንዲኖርህ ግልጽ አድርግ፡፡ ጊዜና ቦታ በትክክል የማይገልጸውን ረጅም ምስክርነት ማቅረብ አያስፈልግም፤ ከ3-4 ደቂቃ ያህል ብቻ ለመጠቀም ወስን፡፡

5) ከቀልድና ከመጥፎ ድርጊቶች መራቅ አለብህ፡፡ ሰዎችን ለማስደሰት ብለህ የሚታደርገውን ነገር ማስወገድ አለብህ፡፡

6) ስሜት፤ ግብ፤ ማስተማር ያለውን ወዘተ. . .አትናገር፡፡

7) ለእግዚአብሔር ብቻ ክብር በመስጠት ለስሜታዊ ሰው የእግዚአብሔርን ፀጋ በማካፈል የስሜታዊውን ሰው ተቃወሞ በመልካም ስነ ምግባር ማሸነፍ አለብህ፡፡

★ የሚስተካከል
አራት ዓይነት በምስክርነት ዘዴዎች የራስህን የሕይወት ምስክርነት ከ3-4 ደቂቃ የሚያህል ጻፍ፡፡
★ መስጠነቀቂያ
ምስክርነት በሚታቀርብበት ጊዜ ስብከት መስበክ አይቻልም፤ ምስክርነት ሊታቀርብ የፈልከውን ከጻፍክ በኋላ አቅርብ፡፡

★ ፀሎት
በየቀኑ አንተ ስለ መዳንህ ደስተኛ ሆነህ እየኖርህ ምስክርነትህን ለሌሎች ማቅረብ ኃይለኛ ፀሎት ፀልይ፡፡

ምዕራፍ ሁለት
ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ጌታ ነው

● ሉቃ.6÷46-49

ክርስቲያኖች ቀላል የእግዚአብሔር ልጆች ሊሆኑ ፍጹም አያስፈልጋቸውም፡፡ ክርስቲያኖች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት ልክ እስክደርሱ ድረስ ሊያድጉ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የክርስቲያኖች እምነት እያደገና ታዛዝነታቸው እየበዛ (እየተገለጠ) ሲሄድ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ጌታ መሆኑን የሚከተሉ ሰዎች በቀላሉ ይረዳሉ ማለት ነው፡፡ የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስን ቢመለከቱ ጌታ የሚለውን ቃል ሁለት ዓይነት ትርጉም ይሰጣል፡፡

የመጀመሪያው ትርጉም አዳኝ(Saviour) የሚለው ነው፡፡ ይህ ትርጉም 10% ብቻ ነው፡፡ ሌላው ሁለተኛው ትርጉም ጌታ(Lord) የሚለው ነው፡፡ ይህ ትርጉም 90% ነው፡፡ ይህ ማለት እኛን የሚመራና የሚጠብቅ ማለት ነው፡፡ የእውነተኛ ሕይወት ማሸነፍ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ጌታ መሆኑን እንዳውቅ ነው፡፡

ያ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ጌታ ነው ብለህ ስትስማማ አሸናፊ ነህ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ካልተስማማህ ተሸናፊ ነህ ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለተቀበሉትም ሆነ፤ ላልተቀበሉት ለሁሉም ሰዎች ጌታ ነው፡፡ እኛን ኢየሱስ በደሙ ዋጅቶናል፡፡ (1ቆሮ.6÷19-20) ኢየሱስ ክርስቶስ በዋጋ የመግዛቱ ምክንያት እርሱ ፈጣሪያችን ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ እርሱ በራሱ ደም እኛን ስለገዛን እኛ የራሳችን አይደለንም፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው ብለን ብንታዘዝ እርሱ የእኛ ፈጣሪ መሆኑን አወቅን ማለት ነው፡፡

1. ማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር ፊት የሕይወት መሪ እንደመኪና ሲሆን ሹፌሩ ደግሞ ራሱ ግለሰቡ ይሆናል፡፡ ከዚህ የተነሣ ስለ መሪ 4 የተለያዩ አቋሞች አሉ፡፡

1) ፍጥረታዊ ሰው(Natural man)
ይህ ሰው የሕይወቱን መሪ ራሱ ይዞ ኢየሱስ ክርስቶስን በመኪና ዕቃ መጫኛ ቦታ ላይ ያስቀመጠ ነው፡፡
★ የዚህ ሰው ልዩ ፀባይ ምንድን ነው?
A. በሕይወቱ ዙፋን ላይ ራሱን ማስቀመጡ
B. ኢየሱስ ክርስቶስን በሕይወቱ ውጭ ማስቀመጡ
C. ሁሉንም ሥራ በራሱ ቁጥጥር ማድረጉ ያ ደግሞ ብዙ ጊዜ ውድቀትንና ግራ መጋባትን ያመጣል፡፡
D. በራሱ ልብ መታመኑ
E. ዓለምን መከተሉ ናቸው፡፡

① 1ቆሮ.2÷14 እንደምገልጸው መዳንን ያልተቀበለ ሰው ነው፡፡

● 1ቆሮ.2÷14
14- ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም።

② ሮሜ1÷28-32 እንደምገልጸው ለማይረባ አዕምሮ አልፎ የተሰጠ ሰው ነው፡፡

● ሮሜ1÷28-32

28- እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤

29- ዓመፃ ሁሉ፥ ግፍ፥ መመኘት፥ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፥ ነፍስ መግደልን፥ ክርክርን፥ ተንኰልን፥ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሹኩ፥

30- ሐሜተኞች፥ አምላክን የሚጠሉ፥ የሚያንገላቱ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥

31- የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ናቸው፤

32- እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።

③ ገላ.5÷19-21 እንደምገልጸው የሥጋ ሥራዎችን ሚከተል ሰው ነው፡፡

● ገላ.5÷19-21

19- የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥

20- መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥

21- መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።

④ ኤፌ.2÷1-3 እንደምገልጸው በበደሉና በኃጢአቱ ምክንያት ሙታን፣ የማይታዘዝና የቁጣ ልጅ የሆነ ሰው ነው፡፡

● ኤፌ.2÷1-3

1-2 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።

3- በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።

2) የልጅነት ሰው (Baby in Christ)

ይህ ሰው የሕይወት መሪ ራሱ ይዘ ኢየሱስ ክርስቶስን በመኪና በስተኋላ ያስቀመጠ ነው፡፡

★ የዚህ ሰው ልዩ ፀባይ ምንድን ነው?

እርሱ እምነቱን ወደላይና ወደታች የሚል ሰው ነው፡፡ የዚህ ሰው ጥፋት ታላቅ ነው፡፡ ነፋስን የሚከተል ሐዘን በሕይወቱ የሚፈራረቅ ሰው ነው፡፡ ደግሞም በጥልቀት ነገሮችን የማይረዳ በረከት ፍለጋ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣ (ያመነ) ሰው ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ክርስቲያን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በልባቸው ጌታ አድርገው ተቀብለዋል፤ ነገር ግን የሕይወቱ ጌታ ራሱ አድርገው በዙፋኑ ላይ ያስቀመጠ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ገና ሕፃን የሆነና በክርስቲያንና ክርስቲያን ባልሆነው መካከል ልዩነትን የማያውቅ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ክርስቲያን በረከት ብቻ የሚፈልግ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ቃል የማይታዘዝ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ክርስቲያን ሁኔታ ምንድን ነው?

① ሮሜ.7÷14-23 በጅምር እምነት የሚቆዩ ናቸው፡፡

● ሮሜ.7÷14-23

14- ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ።

15- የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም።

16- የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደ ሆነ እመሰክራለሁ።

17- እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ።

18- በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም።

19- የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።

20- የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ።

21- እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ።

22- በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥

23- ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ።

② ሮሜ.8÷7፤ ዕብ.5÷12-13 በኃጢአተኝነት ሥፍራ የሚመላለሱ ናቸው፡፡

● ሮሜ.8÷7

7- ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤

● ዕብ.5÷12-13

12- ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም።

13- ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤

3) ወጣት(ሮሜ.7 ምዕራፍ)(Youth)

★ የዚህ ሰው ልዩ ፀባይ ምንድን ነው?

① በደስታ ጊዜ ኢየሱስ ንጉሥ የሚያደርጉት፤ በሐዘን ጊዜ ራሳቸውን ጌታ የሚያደርጉት ሰው ነው፡፡

② በውሳኔ የራሰቸውን ያጸድቃሉ፡፡

③ በመንፈስ ጀምሮ በሥጋ ይጨርሳሉ፡፡

④ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አያዩም፡፡

⑤ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይማራሉ፤ ነገር ግን ዕውቀት ብቻ አላቸው፡፡

⑥ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ብቻ አላቸው፤ ነገር ግን ፍሬ የላቸውም፡፡

⑦ ሁል ጊዜ ራሳቸውን ደካማ አድርገው ይቀጥራሉ፡፡(ሮሜ ምዕራፍ 7)

4) የሚያድጉ ክርስቲያኖች(Spirtual men)

የሕይወታቸውን መሪ ለኢየሱስ ክርስቶስ አስረክበው ራሳቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ አጠገብ ና ከኋላቸው የተቀመጡ ናቸው፡፡

★ የሚያድጉ ክርስቲያኖች ልዩ ፀባይ ምንድን ነው?

① ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት ልክ እስክደርሱ ድረስ የሚያድጉበት ደረጃ አላቸው፡፡

② ኢየሱስ ክርስቶስን መሪያቸው ያደርጋሉ፡፡

③ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ይኖራሉ፡፡

④ ኃጢአትን እስከ ደም ማፍሰስ ድረስ ይዋጋሉ፤ በመጨረሻም አሸነፊዎች ይሆናሉ፡፡

⑤ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን በፍጹም ይታዘዛሉ፡፡

● 1ቆሮ.2÷15

15- መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም።

● ዕብ.5÷14

14- ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።

የሚያድጉ ክርስቲያኖች የራሳቸውን ሕይወት መንፈስ ቅዱስ እንዲመራ ለመንፈስ ቅዱስ ያስረከቡ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወታቸው ጌታ አድርገው የተስማሙና የኢየሱስ ክርስቶስን መሪነትን የተቀበሉ ሰዎች ናቸው፡፡

★ የሚያድጉ ክርስቲያኖች የሕይወት ፍሬ ምንድን ነው?

① ገላ.5÷22 የመንፈስ ፍሬዎች በሕይወታቸው ይበዛል፡፡

● ገላ.5÷22

22- የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።

② ገላ.2÷20 በሕይወታቸው ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ ያደርጋሉ፡፡

● ገላ.2÷20

20- ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።

③ ፊልጵ.4÷13 በእግዚአብሔር ሥልጣል ይኖራሉ፡፡

● ፊልጵ.4÷13

13- ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።

★ የሚከፋፈል

ራስህን አሁን በየተኛው ደረጃ ላይ እንዳለህ አይተህ ከጻፍክ በኋላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡፡

2. መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ስለመሆኑ የሚናገርበት ዝርዝር አግኝ፡፡

1) አስቀድመን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ጽድቁንና ስለ ቤተክርስቲያን ራዕይ እንዲናደርግ ይገልጽናል፡፡ ያ ደግሞ መሬት ገዝተን ትልቅ ቤተ ክርስቲያንን የመስራት ራዕይ ሳይሆን ለመሪዎች ታላቅ ዋጋ ያለውን ራዕይ ማስጨበጥ ነው፡፡

● ማቴ.6÷33

33- ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።

2) ታላቅ ዋጋ ያለውን ቤተክርስቲያንን መገንባት ነው፡፡ ክርስቲያኖች የራሳቸውን ሕይወት አሳልፈው በመስጠት ቤተክርስቲያንን ሊያገለግሉ ያስፈልጋል፡፡

● ማቴ.22÷37

37- ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ።

3) እኛ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች እንደሆነን ይገልጻል፡፡ የጌታ ደስታ የእኛ ደስታ ነው፡፡ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ማለት አያድንም፤ ጌታ የተናገረውን ቃል መፈጸም ነው እንጂ፡፡

- ሉቃ.6÷46

46- ስለ ምን። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም አታደርጉም?

4) ዕለት ዕለት ልንሞት ያስፈልጋል፡፡ ዘውትር በሚንፀልይበት ጊዜ ሞተናል ማለት ነው፡፡ ፀሎት ማለት እኛ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ መጥተን እንዲንታዘዝ የሚያደርግ ነገር ነው፡፡

- ሉቃ.9÷23

23- ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።

3. ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወታችን ጌታ እንደሆነ የተስማማንበትን በዝርዝር መግለጽ አለብን፡፡ ሕይወታችንን አስረክበን ኢየሱስ ክርስቶስን መታዘዝ ይገባናል፡፡ በሚንኖረርበት ሥፍራ ሁሉ ለመጽሐፍ ቅዱስ ዋጋ ሊንከፍል የሚንችልበትና የጌታን ፈቃድ እንዴት መታዘዝ እንደሚገባን ፈልገህ አግኝ፡፡

1) በቤተሰብ ሀሳብ

ከእግዚአብሔር ይልቅ ቤተሰብን የሚንወድ ከሆነ ያ ጣአት ነው፡፡

ቤተሰብን እንደ እግዚአብሔር ፍቅር ሊንወድ ያስፈልጋል፡፡

- ማቴ.10÷37

37- ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤

2) በንብረት ሀሳብ

ሁሉም ንብረቶች የእግዚአብሔር እንደሆነ ሊንገነዘብ ያስፈልጋል፡፡ እኛ ንብረቶችን የሚናስተዳድር ሰዎች ነን፡፡ እኛ በጥቂቱ ታምነን እግዚአብሔርን ሲንታዘዝ ከ30 እጥፍ በላይ በረከትን ጌታ ይሰጠናል፡፡

- ሉቃ.14÷33

33- እንግዲህ እንደዚሁ ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።

3) በባህል ሀሳብ

1ቆሮ.6÷12 ላይ ሰይጣን (ሉስፈር) በሰማይ ለእግዚአብሔር ዝማሬን የሚያቀርብ መልአክ ነበረ፡፡ ነገር ግን ከመታበዩ የተነሣ ከእግዚአብሔር መንግሥት ወደታች ተወርውሮአል፡፡ ሰይጣን ብዙ ጊዜ ባህልን፣ ዘፈንን፣ ቴሌቭዥንና የመሳሰሉትን በመጠቀም የሰውን ሕይወት ያበላሻል፡፡ ስለዚህ እኛ ከእነዚህ ሕይወታችንን ሊያጠፉ ከሚችሉ ነገሮች ሊንቆጠብ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ዘፈኖች የሚናዳምጥ፣ መጥፎ ፍልሞችን የሚንመለከት ከሆነ መንፈሳችን በቀላሉ ይወሰዳል፤ ደግሞም በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ አዝኖ ወጥቶ ይሄዳል፡፡

- 1ቆሮ.6÷12

12- ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም።

4) በጋብቻ ሀሳብ

2ቆሮ.6÷14-16፣ ኤፌ.5÷31፣ ኤፌ.4÷4-6 ላይ እንደምገልጸው ሥጋችን የራሳችን ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ስለዚህ በሥጋችን ላይ አደጋ ሲደርስ ጌታ ሥልጣን አለው፡፡ ሚስቶቻችንን በምንመርጥበት ጊዜ ከፀለይን በኋላ ውሳኔ ማድረግ የእኛ ድርሻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ውሳኔ አይሰጥም፡፡ ምክንያቱም ከፀሎት በኋላ ለራሳችን የሚትመቸውን የትዳር ጓደኛ ሊንወስን ያስፈልጋል፡፡ ቤተሰብ ታላቅ መንፈሳዊ ልምምድ የሚናደርግበት ሥፍራ ነው፡፡ ዘፍ.2÷18 እንደሚለው ጋብቻ የሚንረዳዳበትና ከኃጢአት እንዲንርቅ የሚያደርግ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሠረት ሁሉም ሰዎች ሊያገቡ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን 1ቆሮ.7÷1-5 ላይ እንደተገለጸው ልዩ የሆነ ራሱን ጀንደረባ ያደረገ ሰው ላያገባ ይችላል፡፡ ወንድና ሴት ሆነው ጋብቻን መመስረት ይቻላል፡፡ ጋብቻ ማለት አንድ ሰው ከወላጆቹ ራሱን ችሎ የሚወጣበት ማለት ነው፡፡

- 2ቆሮ.6÷14-16

14- ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?

15- ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?

16- ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፡- በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።

5) በጊዜው ሀሳብ

ኤፌ.5÷16 በችኮላ የሚደረግ ነገር ሳይሆን በየተራው የሚደርስ ነገር ነው፡፡

● ኤፌ.5÷16
16- ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።

6) <u>በእግዚአብሔር መንግሥት ሀሳብ</u>
<u>ሐዋ.18÷1-3 እኛ ለሁሉም መንግሥት ተልዕኮ ያለን ሰዎች ነን፡፡ የእኛ ዋና ተልዕኮ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ደጋግመን ሰዎችን ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው፡፡</u>
● ሐዋ.18÷1-3
1- ከዚህም በኋላ ጳውሎስ ከአቴና ወጥቶ ወደ ቆሮንቶስ መጣ።
2- በወገኑም የጳንጦስ ሰው የሚሆን አቂላ የሚሉትን አንድ አይሁዳዊ አገኘ፤ እርሱም ከጥቂት ጊዜ በፊት ከሚስቱ ከጵርስቅላ ጋር ከኢጣልያ መጥቶ ነበር፥ አይሁድ ከሮሜ ይወጡ ዘንድ ቀላውዴዎስ አዞ ነበርና፤ ወደ እነርሱ ቀረበ፥
3- ሥራቸውም አንድ ስለ ነበረ በእነርሱ ዘንድ ተቀምጦ በአንድ ላይ ሠሩ፤ ሥራቸው ድንኳን መስፋት ነበረና።

7) <u>በሥራ ሀሳባ (ዘፍ.1÷28)</u>
<u>እንደምገልጸው ስድስት ቀን ሙሉ የሠራ ሰው በሰባተኛው ቀን ማለትም በእሁድ ቀን እግዚአብሔርን ያመልካል፡፡ አንተ ምን ዓይነት ሥራዎችን ትሠራለህ? ገንዘብን ማሰባሰብ ብቻ ሳይሆን ክርስቲያን ህብረሰብን ብርሃንና ጨው ሆነህ ሊታገለግል ያስፈልጋል፡፡</u>
<u>★ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚሠራ ሰው የበረከት ሀሳብ</u>
① <u>ሥራ ማለት በረከት እንደሆነ ይረዳል፡፡(ዘፍ.1÷28)</u>
② <u>ሰንበት በረከት እንደሆነ ያውቃል፡፡ (ዘፍ.2÷3)</u>
③ <u>ጋብቻ በረከት እንደሆነ ይረዳል፡፡ (ዘፍ.2÷24)</u>
<u>ሥራ የማይሠራ የተረገመ ነው፤ እግዚአብሔር ይሠራል፡፡ (ዮሐ.5÷17) የማይሠራ ሰው አይበላም፡፡ ሥራ ከአምልኮ አንዱ ነው፡፡</u>

● ዘፍ.1÷28
28- እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፡- ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።

8) <u>በሥጋ ሀሳብ</u>
<u>1ቆሮ.6÷19-20 ሥጋህን መንፈሳዊ የጦር ዕቃና ለእግዚአብሔር ክብር ማዋል አለብህ፡፡</u>
● 1ቆሮ.6÷19-20
19-20 ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።

9) <u>በቋንቋ ሀሳብ</u>
<u>ያዕ.3÷5-8 አንድበታችን (ምላሳችን) ክፉ ስለሆነ ልንቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ መልካም ስነ ምግባር የሆነው ብቻ መነጋገር አለብን፡፡</u>
● ያዕ.3÷5-8
5- እንዲሁም አንደበት ደግሞ ትንሽ ብልት ሆኖ በታላላቅ ነገር ይመካል። እነሆ፥ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ትልቅ ጫካ ያቃጥላል።
6- አንደበትም እሳት ነው። አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና፥ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፥ በገሃነምም ይቃጠላል።
7- የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ በሰው ይገራል፥ ደግሞ ተገርቶአል፤
8- ነገር ግን አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይችልም፤ የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፋት ነው።

<u>★ ማስተካከያ</u>
<u>የመንፈስ ቅዱስ ዋጋ በማሰብ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ጌታ መሆኑን አውቀን ራሳችንን ሊንፈትሽ ያስፈልጋል፡፡ ራሳችን በርትተን የሚንቋቋምበት ነገር ምንድን ነው? አንተ ሕይወትህን እንዴት ሊታስተካክል እንደፈልግህ ከጻፍክ በኋላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡፡</u>

<u>4. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉም ሰዎች ወደ ራሱ ልክ እንዲያድጉ ይፈልጋል፡፡</u>
<u>1) ፍጥረታዊ ሰው የሆኑ ክርስቲያኖች ለመቀየር ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?</u>
① <u>ዮሐ.1÷12 የእግዚአብሔር ልጅ መሆን አለባቸው፡፡</u>
● ዮሐ.1÷12
12- ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤

② <u>ሮሜ10÷9-10 ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፋቸው መመስከር አለባቸው፡፡</u>
● ሮሜ10÷9-10
9- ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤

10- ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።

2) <u>በመንፈሳዊ ሕይወት ልጅ የሆኑት ለማደግ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?</u>
① ገላ.5÷16 የመንፈስ ቅዱስ ምሪት መከተል ያስፈልጋል፡፡
● ገላ.5÷16
16- ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።

② <u>1ጢሞ.4÷5 በፀሎትና በቅድስና ሊኖሩ ያስፈልጋል፡፡</u>
● 1ጢሞ.4÷5
5- በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና።

③ <u>ኤፌ.5÷18-21 የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መፈለግ አለባቸው፡፡</u>
● ኤፌ.5÷18-21
18- መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤
19- በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤
20- ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።
21- ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ።

3) <u>ሁሉም ክርስቲያኖች ለተከታታይ እንዴት ማደግ አለባቸው?</u>
① 1ጢሞ.4÷15 እውነትን በመደግ ሊያሳዩ ይገባቸዋል፡፡
● 1ጢሞ.4÷15
15- ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ፥ ይህንም አዘውትር።

② <u>ኤፌ.4÷15 ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት ልክ እስክደርሱ ድረስ ሊያድጉ ያስፈልጋል፡፡</u>
● ኤፌ.4÷15
15- ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤

<u>★ ማስተካከያ</u>
<u>ራስህን ለማሳደግ ከክርስቲያኖች ህብረት አንተን ያደናቀፈው ነገር ምን እንደሆነ ካወቅህ በኋላ ጽፈህ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተከፋፈል፡፡</u>

<u>★ ፀሎት</u>
<u>ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት ልክ ለመድረስ ከክርስቲያኖች ጋር አንድ ላይ ፀልይ፡፡</u>

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>
<u>አንተ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ነህ፡፡</u>
● ማቴ.4÷19
19- እርሱም፦ በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው።

<u>በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሦስት ዓይነት ሰዎች አሉ፡፡</u>
<u>1ኛ ሰው</u> <u>ወደ ቤተክርስቲያን ያለ ዓላማ ዝም ብሎ የሚሄድና የሚመለስ ሰው ነው፡፡ ይህ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ አድርጎ ያልተቀበለ (ያላመነ)፤ ነገር ግን ወደ ቤተክርስቲያን ዝም ብሎ በመሄድና ቃሉን ሰምተው የሚመለስ ስለ መንግሥተ ሰማይ መኖር ያላረጋገጠ ዕውቀት ብቻ ለማግኘት ከሰዎች ጋር ህብረት የሚያደርግና ወላጆችን ለመታዘዝ ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄድ ሰው ነው፡፡</u>

<u>2ኛ ሰው</u> <u>ክርስቲያን የሆነ ሰው ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ የተቀበለ፣ ስለ መንግሥተ ሰማይ መኖር ያረጋገጠ ሰው ነው፡፡ እግዚአብሔር በሰጠው ፀጋ በዓለም የተትረፈረፈ ሕይወት ለመኖር የሚፈልግና ከዚህ ዓለም መጨረሻ በመንግሥተ ሰማይ የዘላለም ሕይወት መኖሩ ያረጋገጠ ደግሞም በሰማይ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ለዘላለም ለመኖር የሚፈልግ ሰው ነው፡፡ ስለዚህ አንተ ያለ ዓላማ ዝም ብለህ ወደ ቤተክርስቲያን የሚትሄድና የሚትመለስ ሰው ሊትሆን አያስፈልግም፡፡ አንተ ኢየሱስ ክርስቶስን ያመንህ (የተቀበልህ) እውነተኛ ክርስቲያንና ስምህን በመንግሥተ ሰማይ ያስጻፍክና የእግዚአብሔር ልጅ ሆነህ የእርሱን መንግሥት ሊትወርስ ይገባሃል፡፡</u>

3ኛ ሰው ደቀ መዛሙርት የሆነ ሰው ነው፡፡ ክርስቲያኖች ደቀ መዛሙርት ቀዳሚዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ መዳንን የተቀበሉ ሁሉ ያዳናቸውን ጌታ በመውደድ ሊኖሩና እርሱን ሊከተሉ ይገባቸዋል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ክርስቲያኖች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጠራቸው ደቀመዛሙርቴ ናቸው ብሎ ይጠራቸዋል፡፡ ስለዚህ ከሕፃንነት ወደ አዋቂነት ድረስ የሚያድግ ክርስቲያን ሊሆን ያስፈልጋል፣ ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄድ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ የዳነ፣ እርሱን የሚወድና የሚከተል ታማኝ ደቀመዛሙርት መሆን አለበት፡፡

1. ደቀመዛሙርት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፈልገህ አግኝ፡፡

1) ደቀ መዛሙርት ማለት ተማሪ ማለት ነው፡፡ ሐዋሪያ ጳውሎስ እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ በማለት የራሱን ሕይወት እንዲማሩ ተናገረ፣ መሪ የሆነ ጌታ ኢየሱስ ስለ አገልግሎት ሁኔታ ለደቀመዛሙርቱ በመግለጽ እነርሱ የእርሱ ተማሪዎች እንደሆኑ አስታወቃቸው፡፡ ስለዚህ ሰውን ማሳደግ የሚችለው ቤተክርስቲያን ሳትሆን እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

● 1ቆሮ.11÷1

1 እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።

2) በኢየሱስ ክርስቶስ ፋንታ ሊሠሩ የተጠሩ ማለትም 12ቱ ደቀ መዛሙርት ማለት ነው፡፡ እነዚህ ደቀ መዛሙርት በምርጫ የተወሰዱ ሰዎች ናቸው፡፡

● ማር.3÷13-15

13- ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ።

14- ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥

15- ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤

3) ደቀ መዛሙርት የአስተማሪን ሥራ ተቀብሎ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

● ማቴ.28÷18-20

18- ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።

19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

4) ደቀ መዛሙርት መላክ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡

● ዮሐ.17÷8፣ 20÷21

8- የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፥ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ።

20-21 ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ።

2. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበትን ዓላማ የመንግሥቱን ሥራ በሦስት ዓመት ውስጥ ገለፀ፡፡ ኢየሱስ በዓላማ ላይ 12ቱን ደቀመዛሙርት ይገነባቸው፡፡ ኢየሱስ እነዚያን 12ቱን ደቀመዛሙርቶችን እንዴት አስተማራቸው?

1) የራሱን ሥራ በተሻሌ ሁኔታ እነርሱ እንዲሠሩ አለማመዳቸው፡፡

● ዮሐ.14÷21

21- ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ።

2) ራሳቸውን ፍጹም እንዳይወዱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ ደቀመዛሙር ሆኖ እንዲኖሩ አስተማራቸው፡፡ ሐዋሪያ ጳውሎስ የተሻለ ብዙ ሰዎች ለመማረክ የተዘጋጁ አገልጋዮች እንዲሆኑ ገለጻቸው፡፡

● 1ቆሮ.9÷19-21

19- ከሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ስሆን የሚበልጡትን እንድጠቅም እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ።

20- አይሁድንም እጠቅም ዘንድ ከአይሁድ ጋር እንደ አይሁዳዊ ሆንሁ፤ ከሕግ በታች ያሉትን እጠቅም ዘንድ፥ እኔ ራሴ ከሕግ በታች ሳልሆን፥ ከሕግ በታች ላሉት ከሕግ በታች እንዳለሁ ሆንሁ፤

21- ሕግ የሌላቸውን እጠቅም ዘንድ፥ ያለ እግዚአብሔር ህግ ሳልኖር ነገር ግን በክርስቶስ ሕግ በታች ሳለሁ፥ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደ ሌለኝ ሆንሁ፤

3) ኢየሱስ በሦስት ዓመት ውስጥ ግልጽ የሆነ የደቀ መዛሙርት ሕይወት እንዲያዩና አብሮ እንዲኖሩ ደግሞም እንዲመሰክሩ በሚገባ አስተማራቸው፡፡

● ማር.3÷13-15

13- ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ።

14- ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥

15- ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤

4) የዓለም ራዕይን በውስጣቸው አስቀመጣቸው፡፡ ወንጌልን ለሚሰብከው ሰው ታላቅ ሥልጣንን ሰጠ፡፡

● ማር.16÷15

15- እንዲህም አላቸው፡- ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።

3. ኢየሱስ ክርስቶስ የጠራቸው ሰዎች ደካሞችና ብዙ ችግር ያሉአቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን በልምምድ ድክመታቸውንና ችግሮቻቸውን ቀረፈላቸው፡፡

እንዴት ጌታ ኢየሱስ የእነርሱን ድክመት ለወጠ?

1) የራሱን ሕይወት ሳይፈልግ በታማኝነት አስተምሮ ለወጠላቸው፡፡ ስለዚህ አንተ ራስህን ደቀ መዛሙርት እንደሆነህ ሊትቀበል ይገባል፡፡

2) ከሌሎች ጋር አብሮ እየኖረ በታማኝነት የሚያስተምር አስተማሪ በመሆን ለወጠላቸው፡፡

3) እነርሱ መንፈሳዊ ቤተሰቦች እንደሆኑ ግምት ውስጥ በማስገባት ይህም የሚያስፈልግ ነገር እንደሆነ በማወቅ የእነርሱን ድክመት ለወጠላቸው፡፡ ታማኝ ትውልድ እስከ መጨረሻ ድረስ አይቋረጥም፡፡

4) የብዜትን ትምህርት ራዕይን በማድረግ እነዚያን ሰዎችን ለወጠላቸው፡፡

● 2ጢሞ.2÷2

2- ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።

★ መመርመሪያ (መፈተሻ)

① ራዕይ አለህ?

② ስትራቴጅ አልህ?

③ መሥራት ትችላለህ?

የቤተክርስቲያን ተከላና የወንጌል ስብከት ሥራ የአንድ ጊዜ ሥራ ሳይሆን አንድ ሰው ሌላውን ደቀ መዛሙርት እያደረገ ለዘመናት የሚሠራ ራዕይ ነው፡፡

4. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ሲለማመዳቸው ታማኞች እንዲሆኑ ነው፡፡

ታማኝ ደቀ መዛሙርት ልዩ ፀባይ ምንድን ነው?

1) ታማኝ ደቀ መዛሙርት የሕይወት ዓላማና ግብ ግልጽ ነው፡፡ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁን ቅድሚያ በመስጠት ከቤተክርስቲያን ጋር ራዕያቸውን ያከናውናሉ፡፡

● ማቴ.6÷33

33- ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።

2) ታማኝ ደቀ መዛሙርት ዋጋ ይከፍላል፡፡ ራሱን ይክዳል፡፡

● ሉቃ.9÷23

23- ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።

3) ታማኝ ደቀመዛሙርት የራሳቸውን ሕይወት አይፈልጉም፡፡

① እንደ ወታደር ሆኖ የወታደርነትን ኑሮ ይኖራል፡፡

② መስመሩን ጠብቆ እንደሚሮጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተከትሎ ይሮጣል፡፡

③ ጊዜውን ጠብቆ እንደሚሠራ ገበሬ ከእርሻው የመጀመሪያውን ወስዶ ደስ እንደምለው ታላቅ ሽልማት በመንግሥቱ ሰማይ እንዳለ ተስፋ አድርጎ ሥራው በጊዜው ይሠራል፡፡

● 2ጢሞ.2÷3-4

3- እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል።

4- የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም።

4) ታማኝ ደቀ መዛሙርት በእግዚአብሔር ቃል ይደሰታል፡፡ ሁለት ክንፎች መሠረት በማድረግ የረጅም ጊዜ የሚወስድ ሥራ ይሠራል፡፡

● ማቴ.4÷4

4- እርሱም መልሶ፡- ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።

5) ታማኝ ደቀ መዛሙርት የአገልጋይነት ልብ አለው፡፡ የአገልጋይነት ልብ ማለት ሌላውን የሚያገለግል ሰው ደቀ መዛሙርት ልምምድ ያደረገ ሰው ማለት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ብዙ አውቆ ነገር ግን የማያገለግል እርሱ ደቀ መዛሙርት ያልሆነ ሰው ነው፡፡

● ማር.10÷45

45- እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።

6) ታማኝ ደቀመዛሙርት በራሱ ጉልበት የማይመካ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ እርሱን የሚከተልና በእርሱ የሚመካ ነው፡፡

● ፊልጵ.3÷3
3- እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና።

7) ታማኝ ደቀመዛሙርት በእያንዳንዱ ሁኔታ አይጠመድም፡፡ በህብረት ሥራ ይደሰታል፡፡
● ገላ.2÷20
20- ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።

8) ታማኝ ደቀ መዛሙርት በደልን አይቆጥርም፡፡ ኃጢአቱን ይቅር የሚል ሰው እርሱ ጥሩ ሰው ነው፡፡
● ዕብ.12÷15
15- የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፥ ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ፥ ሴሰኛም የሚሆን እንዳይገኝ፥

9) ታማኝ ደቀ መዛሙርት ራሱን ይቆጣጠራል፡፡ መልካም መሪ ራሱን ክዶ እግዚአብሔርን የሚታዘዝ ነው፡፡
● 1ቆሮ.9÷24-27
24- በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡት፥ ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ።
25- የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፥ እኛ ግን የማይጠፋውን።
26- ስለዚህ እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፥ ነፋስን እንደሚጎስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም፤
27- ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።

5. ኢየሱስ ጥሪን ከተቀበልከው ካንተ ምን ይፈልጋል?
1) እግዚአብሔር እንዴት እንደጠራ እንዲታረጋግጥ ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ፈጣሪያችን እኛ ደግሞ የተፈጠርን ሰዎች ነን፡፡
● ገላ.1÷1
1-2 በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታንም ባነሣው በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ የሆነ እንጂ ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ ጳውሎስ ከእኔም ጋር ያሉት ወንድሞች ሁሉ፥ ወደ ገላትያ አብያተ ክርስቲያናት፤

2) የጌታን በረከት እንዲንከፋፍል ይፈልጋል፡፡
● ሐዋ.8÷4-8
4- የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።
5- ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው።
6- ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ።
7- ርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና፤ ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤
8- በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።

3) የጠፉ ሰዎችን እንዲናድን (እንዲንመልስ) ይፈልጋል፡፡
● 1ቆሮ.9÷16
16- ወንጌልን ብሰብክ እንኳ የምመካበት የለኝም፤ ግድ ደርሶብኝ ነውና፤ ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ።

4) ደቀ መዛሙርት ሆነን ሌሎችን ደቀ መዛሙርት እንዲናደርግ ይፈልጋል፡፡
ጌታን ሲንታዘዝ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ሆነን ማለት ነው፡፡ ሁለት ክንፍ ሕይወት በሚንኖርበት ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ሆነን ማለት ነው፡፡ ደቀ መዛሙርት የሚሆኑበት መንገድ በጣም ሩቅ፣ ጠባብና አደገኛ መንገድ ነው፤ አንተ በመጀመሪያ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚትከተል ሰው ብትሆን ሌሎች ሰዎች አንተን አይተው ኢየሱስ ክርስቶስን ሊከተሉ ይችላሉ፡፡ በረከት ፍለጋ ደቀመዛሙርት ከመሆን ደቀመዛሙርት ሆነህ ብትገኝ በረከት ወደ አንተ ይመጣል፡፡ ስለዚህ አንተ አስቀድመህ የጌታ ደቀመዛሙርት ሁን፤ ከዚያ በኋላ ሌሎች ሰዎችን ደቀ መዛሙርት ማድረግ ትችላለህ፡፡ ስለዚህ እነርሱ ያንተን ሕይወት እንዲያዩ አድርግ፡፡ ስለ እነርሱ የሚታስበው ነገር ሊኖርህ አፍቃሪ፣ ታማኝ ሰው ሆነህ ታማኞችን የሚታገኝ ሰው ሊትሆን ይገባል፡፡ የሁለት ክንፎች ሥርዓት ማወቅ ብቻ ሳይሆን በቀላሉ ዘዴ ደጋግሞ በአንድ ዓመት ውስጥ ለውጥን ማምጣት ማለት ነው፡፡ በመጨረሻ የሕይወት ለውጥ ልምድ ታገኛለህ፡፡
● ማቴ.28÷19-20
19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

★ ማስተካከያ
ከዚህ ምዕራፍ የተማርኸውን አዲስ ያወቅኸውን ያንተን ሕይወት ሊታስተካክል የፈልግኸውን ከጻፍህ በኋላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል

★ ፀሎት
የደቀ መዛሙርት ጥሪ ለመታዘዝ በደንብ ድምፅህን አውጥተህ ፀልይ፡፡

ምዕራፍ አራት
የደቀመዛሙርት ዋጋ ስለ መክፈል፡፡

● ማቴ.10÷37-39
37- ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤
38- መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም።
39- ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።

ለዝነኛው ፍራንስስ ሁለት ወጣቶች መጥቶ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ለመሆን ፈልገው ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ፍራንስስ የወጣቶቹን ጥያቄ ሰምቶ አንዲት ተከል በመሬት ተክሎ እንዲህ አላቸው፡፡ "እኔ ለትንሽ ጊዜ ወደ ሌላ ሥፍራ ሄጄ እመለሳለው፤ እናንተ ግን በእኔ ቦታ (ፋንታ) ሆናችሁ አታክልቶቼን ተንከባክቡ፤ ይህንን በምትሠሩበት ጊዜ የተክሎቹን ቅርንጫፍ ወደ መሬት ውስጥ አድርጋችሁ የተክሎቹን ሥር ደግሞ ወደ ላይ ማለት ከመሬት በላይ አድርጋችሁ ተንከባክቡ" ብሎ ተናግሮ እነርሱን በእርሻ ቦታ (በማሳ ውስጥ) ትቶ ወደሚሄድበት ሥፍራ ሄደ፡፡ ከሄደበት ተመልሶ ትዕዛዝ ለሰጠዋቸው ወጣቶች መጥቶ አንደኛው የሠራበትን ሁኔታ ሲጠይቅ ወጣቱ ለፍራንስስ "የተናገርከውን ሁሉ አድርገዋለሁ ይኸው የተክሉን ቅርንጫፍ በመሬት ውስጥ ሥሮቹን ደግሞ ከመሬት በላይ" ብሎ ያደረገውን አሳየ፡፡ ሁለተኛው ወጣት ግን ለሽማግለው ፍራንስስ እንዲህ ብሎ የሠራውን ተናገረ፡፡

"የተናገርከው ስህተት ነው፤ ስለዚህ እኔ ትክክለኛውን አሠራር ጠብቄ ተክሉን ሥሮችን ወደ መሬት ውስጥ አድርጌ ደግሞም ቅርንጫፎቹን ከመሬት በላይ በማድረግ ተከልሁ" አለ፡፡ ፍራንስስ ሥሮቹን በመሬት ውስጥ ላደረገው ወጣት "አንተ የተክሎቹን ሥሮች በመሬት የተከልህ ሰው ጎበዝ ሰው ነህ፤ ነገር ግን አንተ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሊትሆን አትችልም፡፡" ከዚያም በኋላ ሌላኛውን ወጣት ማለትም ሥሮቹን ከመሬት በላይ አድርጎ የተከለውን "አንተ ፍጹም የታዘዝህ ሰው ነህ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሊትሆን ትችላለህ፡፡ አንተ ብቻ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንዲትሆን ፈቃድ ሰጥቻለሁ፡፡" ብሎ ተናገረ፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት አስተማሪዎች ሳይሆኑ የጌታን ትዕዛዝ በሙሉ የሚፈጽሙ የራሳቸውን ሀሳብና ፈቃድ የማያደርጉ ነገር ግን ለጌታ ፈቃድ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ለዓይን ስውሩ ጭቃ በዓይኖቹ ላይ ቀብቶ "ሂድ በሴሎሆም መጭመቂያ ታጠብ" አለ፡፡ ነገር ግን ዓይን ስውሩ ዘውትር በዚያ ውሃ ይታጠብ ነበር፤ ግን የጌታ ትዕዛዝ ስለሆነ ሄዶ ታጠበ እያየ መጣ፡፡

1. በደቀ መዛሙርነት ሕይወት የሚኖር ሰው ምን ዓይነት ሰው ነው?

1) አዲስ ፍጥረት ነው፡፡
● 2ቆሮ.5÷17
17- ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

2) ጽድቅን፣ ቅድስንና እውነት የሚከተል ሰው ነው፡፡
● ኤፌ.4÷24
24- ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።

3) የሚያደርግ ሰው ሆነ።
① ወዲያውኑ የሚያደርግ
② እስከ መጨረሻ ድረስ የሚያደርግ
③ ፍሬ እስከሚያገኝ ድረስ ሁሉንም በፅቅድ የሚያደርግና የሚታዘዝ ሰው ነው፡፡
● ኤፌ.2÷10
10- እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።

4) የራሱን ፀባይ በሥራ አሳይቶ ሌሎች እንዲከተሉ የሚያደርግ ሰው ነው፡፡
● ፊልሞ.3÷17
17- እንግዲህ እኔን እንደ ወንድም አድርገህ ከቁጠርከኝ ልክ እንደ እኔ አድርገህ ተቀበለው፡፡

5) ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብሮ የሚኖር ሰው ነው፡ ፡

● ማር.3÷13-15

13- ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ።

14- ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥

15- ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤

2. ደቀ መዛሙርት የሚያስተምረውን አስተማሪን በታማኝነት የሚከተልና በፍጹም የሚታዘዝ ሰው ነው፡ ፡ አንተ የደቀመዛሙርት አቋም እንዴት ታደርጋለህ?

1) ሕያው የሆነውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወቱ ጌታ አድርጎ በንስሐ በፊቱ በመውደቅ የደቀመዛሙርትን **አቋም** የሚከፍል ሰው ሊሆን ያስፈልጋል፡ ፡

● ሮሜ1÷1

1-2 ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ።

2) ከጌታ ኢየሱስ ጋር በመኖሩ ደስተኛ በመሆን፡ ፡

● ማር.3÷13-15

13- ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ።

14- ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥

15- ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤

3) ከእግዚአብሔር መንግሥት አስበልጦ ቤተሰቦቹን ለመውደድ የማይስማማ ሰው በመሆን፡ ፡

● ማቴ.10÷34-37

34- በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም።

35- ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤

36- ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል።

37- ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤

4) ራሱን ክዶ ዕለት ዕለት መስቀሉን ተሸክሞ የሚከተል ሰው በመሆን፡ ፡ እኔ ዕለት ዕለት በመሞት የጌታ ተልዕኮውን መፈጸም እችላለሁ፡ ፡

● ማቴ.10÷38

38- መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም።

5) ሕይወቴን ሙሉ በሙሉ መስዋዕት በማድረግ፡ ፡

● ማቴ.10÷39

39- ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።

3. ጌታ ኢየሱስ ለምን እንደዚህ ዓይነት ሰው ይፈልጋል?

1) ሁሉንም ነገድ ደቀ መዛሙርት አድርገው የዓለምን ራዕይ ግብ እንዲያደርሱ ነው፡ ፡

● ማቴ.28÷18-20

18- ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።

19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

2) የእግዚአብሔርን የጦር ጋሻ ለብሰው በመንፈሳዊ ውጊያ ድል እንዲያደርጉ ነው፡ ፡ የእኛ ውጊያ ከደምና ከሥጋ ጋር ሳይሆን ከጨለማ ዓለም ገዥ ከሆነው በሰማያዊ ሥፍራ ካለው ከክፉ መናፍስት ጋር ነው፡ ፡

● ኤፌ.6÷10-12

10- በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።

11- የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።

12- መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

3) የሥጋ ምኞት፣ የዓይን አምሮትንና የኑሮ (የዚህ ዓለም) ትምክት እንዳያደርጉ ነው፡ ፡

● ሉቃ.18÷21-23

21- እርሱም፡- ይህን ሁሉ ከሕፃንናቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ አለ።

22- ኢየሱስም ይህን ሰምቶ፡ አንዲት ገና ቀርታሃለች፤ ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው።
23- እርሱ ግን ይህን ሰምቶ እጅግ ባለ ጠጋ ነበርና ብዙ አዘነ።

4) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሥራቸውን እንዲያደርጉ ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ማለት የእግዚአብሔር ቃልና ፀሎት ነው፡፡
● ገላ.5÷16
16- ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።

● ሐዋ.1÷8
8- ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

4. የደቀ መዛሙርት ሕይወት የማይኖሩትን ሰዎች ሰይጣን እንዴት ባለው ስትራቴጅ ይጠቀማል?
1) ከተልዕኮ ውጭ የሆነ ሥራ እየቸኮሉ እንዲሠሩ በማድረግ፡፡ የወንጌል ስብከት ሥራ ትቶ ሌላውን እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡
● ያዕ.4÷13
13- አሁንም። ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ፥ ተመልከቱ፥ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና።

2) በዓለም ሀሳብ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፡፡ ክፉ የሆነውን ባህል ተስማምቶ እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡
● ያዕ.4÷16
16- አሁን ግን በትዕቢታችሁ ትመካላችሁ፤ እንደዚህ ያለ ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው።

3) በራሳቸው ሀሳብ እንዲጠመዱ በማድረግ፡፡ በራስ ወዳድነት ውስጥ ያስገባቸዋል፡፡
● 1ጢሞ.6÷9
9- ዳሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ።

4) በፍቅር እንዳይከተሉ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ሐዋሪያ ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ትቶ የሰውን ሀሳብ እንዲያደርግ ሰይጣን ወደ ውስጡ በመግባት አነሳሳው፡፡
● ማቴ.16÷23
23- እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን። ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።

5) የራሳቸውን ልምድ ይዘው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዳይመሩ ያደርጋል፡፡
● ገላ.5÷16-17
16- ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።
17- ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቃወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።

6) በሥጋ ምኞት፣ በዓይን አምሮትና በኑሮ ትምክት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፡፡
● 1ዮሐ.2÷15-16
15-16 ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።

7) ስለ ቅድሚያ ሥራ ግራ መጋባትን ይሰጣል፡፡ (ያደነጋግራል)አስፈላጊ ሥራ የተኛው እንደሆነና የሚያስፈልገው ሥራ የተኛው እንደሆነ እንዳንለይ ያደርጋል፡፡
● ሮሜ12÷2
2- የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።

★ በዓለም ላይ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎች
1) ከእግዚአብሔር ጋር ህበረት ማድረግ
2) ሕያው የሆኑ ነፍስን ወደ ክርስቶስ መማረክ
3) መልካም የሆነ ሰው መገንባት
4) ጠንካራ የሆነችውን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን መገንባት ናቸው፡፡

5. ስለዚህ እኛ በየቀኑ የእግዚአብሔርን ኃይል ሊንቀበል ያስፈልጋል፡፡ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ተልዕኮአቸውን ለመፈጸም ከሰማይ የተቀበሉት ሥልጣን ምንድን ነው?

1) የእግዚአብሔር ልጅ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ልዩ ሥልጣን፡፡
በእጅ ከመዳሰስ፣ በዓይን ከማየት እንዲሁም በጆሮ ከመስማት የሚበልጥ ሥልጣንን አረጋገጠልን፡፡

● ዮሐ.1÷12
12- ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤

2) የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ መልበስ፡፡ የእግዚአብሔር ሥልጣን የጦር ዕቃ ለብሰው፣ በራሳቸው የመዳንን ቁር፣ በደረታቸው የጽድቅ ጥሩር፣ በወገባቸው እውነትን ታጥቀው፣ ለሰላም ወንጌል በመዘጋጀት በእግሮቻቸው ተጫምተው ክፉን ፍላጻ ለማጥፋት የእግዚአብሔርን ጋሻ የመንፈስን ሰይፍ ይይዛሉ፡፡

● ኤፌ.6÷10-17
10- በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።
11- የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።
12- መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።
13- ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።
14-15 እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤
16- በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤
17- የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።

3) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚፈልጉትን ይጸልያሉ፡፡

● ኤፌ.6÷18-20
18- በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤
19- ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፤
20- ስለ ወንጌልም በሰንሰለት መልእክተኛ የሆንሁ፥ መናገር እንደሚገባኝ ስለ እርሱ በግልጥ እናገር ዘንድ ለምኑ።

4) በተረጋገጠው (በጸደቀው) ስትራቴጅ ጋሻ ይለብሳሉ፡፡

① **እናንተ: -** ሠልጥናችሁ (ልምምድ አድርጋችሁ) የእርሱ ደቀ መዛሙርት ሆናች የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው፣ አስተማሪዎች፣ ወንጌል ሰባኪዎችና የፈውስ ፀጋ ያላችሁ ሰዎች ሊትሆኑ ይገባቸዋል፡፡ በምኞት ውስጥ የገባ፣ ትዕቢተኛና የማይፀልይ ስለ ኃጢአቱ በምስማር ተቸንክሮ በመስቀል ላይ በተሰቀለው ደሙንም ባፈሰሰው በጌታ ፊት መውደቅ (ንስሐ መጠየቅ) ያስፈልጋል፡፡

② **ሂዱ: -** ወደ መንግሥት መሥሪያ ቤት፣ ወደ ቢሮ፣ ወደ ት/ቤት፣ ወደ ሠፈር፣ ሰዎች ወደ ሚገኙበት አካባቢ ሁሉ መሄድ አለብን፡፡ ከሰዎች ጋር አንድ ላይ በመሄድ ክፍት ስብከት ሊንሰብክ ያስፈልጋል፡፡

③ **ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው:-** ከማስተማር በፊት ተማሩ፤ ከዚያ በኋላ ሌለች ሰዎችን ደግሞ አስተምሩ፡፡ የሚታስተምሩአቸው ክፍት ስብከትንና የደቀ መዛሙርት ሕይወት የሚለውን መጽሐፍ ነው፡፡

④ **አጥምቁአቸው: -** ለወታደርነት ዓላማ የተጠራው ሰው አዛዡን ለማስደሰት እንደምጥር እነዚያ የሚጠመቁ ሰዎች ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ እንዲኖሩ አድርጉአቸው፡፡

⑤ **አስተምሩና ጠብቁ: -** እንደገና ደቀመዛሙርት እያደረጋችሁ አብዙ፡፡

● ማቴ.28÷18-20
18- ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።
19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

5) ወንጌልን በሚንመሰክርበት ጊዜ ኃላፍነቱን ሕያው ለሆነው ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት አለብን፡፡ ስለምንበላው ምግብ፣ ስለምንጠጣው ነገርና ስለምንለብሰው ልብስ መጨነቅ አያስፈልግም፡፡ ወንጌልን ለመስበክ ሌላ ተስፋ ሊኖረን አያስፈልግም፡፡

● ሐዋ.20÷24
24- ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።

★ ማስተካከያ

ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተማረኸው ነገር ሕይወትህን ለማስተካከል የፈለግከውን ከጓፍክ በኃላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡

★ ጸሎት

በድካም ሁሉ ዋጋ የሚትከፍል ደቀ መዛሙርት ሊትሆን በደንብ ጸልይ፡ ፡

ምዕራፍ አምስት

የእግዚአብሔር ቅርጽ ያላት ቤተክርስቲያን

● ሐዋ.2÷42-47

42- በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።

43- ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።

44- ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤

45- ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ÷ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።

46- በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ÷ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤

47- እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

ብዙ ቤተክርስቲያኖችን ለመገንባት ጠንክረን መሥራት አስፈላጊ ነው፡ ፡ ነገር ግን የተሻለ የሚያስፈልገን ነገር የቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆነውን ፍጹም ማወቅ ነው፡ ፡ ጌታ ኢየሱስ ወደ በምድር ዳግመኛ መጥቶ ሊያገኛት የሚፈልገው ቤተክርስቲያን ክቡር የሆነች ቤተክርስቲያንን ነው፡ ፡ ጌታ ኢየሱስን የሚትፈልግ ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚትሠራ ቤተ ክርስቲያን ናት፡ ፡ የመጀመሪያ የሐዋሪያት ቤተ ክርስቲያን እሳት የሆነች በወንጌል ዓለምን የማረከች የመጨረሻ ዘመን ቤተክርስቲያን ናት፡ ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊገነባ የሚፈልገው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቅርጽ ያላት የሚትበርር ሁለት ክንፍ ያላትን ቤተ ክርስቲያንን ነው፡ ፡

1. የብሉይ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የሚትበር ሁለት ክንፍ ያላት ቤተክርስቲያን ናት፡ ፡ የዚህ ልዩ ፀባይ አግኝ፡ ፡

1) ትልቅ ቡድን በመሰባሰብ የሚታመልክ ሁለት ክንፍ ያላት የእግዚአብሔር ታላቅ ልምድ ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት፡ ፡

① የመጀመሪያ የሐዋሪያት ቤተ ክርስቲያን (ሐዋ.2÷46) በየቀኑ በአንድ ልብ ሆኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሰባሰብ እንጀራ የሚትቆርስ ሁለት ክንፍ ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት፡ ፡

② የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን በአንደኛው ክንፍ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን የሚታመልክ ትልቅ ክንፍ ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት፡ ፡

③ በሁለተኛው ክንፍ ደግሞ በቤት ውስጥ እግዚአብሔርን የሚታመልክ ትንሽ ክንፍ ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት፡ ፡

2) በሥጋና በነፍስ በትንሽ ቡድን ክንፍ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የሚታደርግ ናት፡ ፡

3) ሁለት ክንፎች በሚዛን የሚታደርግ የእግዚአብሔር ቅርጽ ያላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነች የፀናች ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡

4) ንስር የሚትበርርበት ምክንያት ምግብ ፍለጋ እንደሆነ ሁሉ ዓለምን ለማሸነፍ ሰይጣን ማርከ የወሰዳቸውን ሰዎች ማዳን አለብን፡፡ የዛሬ ክርስቲያኖች የንስር ባህርይ ሊወስዱ ይገባቸዋል፡፡

5) ሁለት ክንፎች ይህንን ሥራ እየተረዳዱና ተያይዘው የጠፉትን ነፍሳት ለመማረክ ይጠቅማል፡፡

2. ክፍል ቤተ ክርስቲያን ጉባኤውን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ትጀምራለች፡፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገለጸውን አግኝ፡፡

1) ስላሴ እግዚአብሔር በጉባኤ መካከል አለ፡፡

● ዘፍ.1÷26

26 እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።

2) ጉባኤ ማለት ከሌሎች ጋር በህብረት የሚያደርጉበት ኑሮ ማለት ነው፡፡ በህብረት መረዳዳት ማለት ነው፡፡ በመጽናናት የጸሎትን ምላሽ በመቀበል በፍቅር ህብረትን ልንለማመድ ይቻላል፡፡

● ሐዋ.2÷44-45

44- ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤

45- ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።

3) እግዚአብሔር ቤተሰብ ጉባኤን በሥጦታ ይሰጣል፡፡

● ዘፍ.2÷24-25

24- ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።

25- አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፥ አይተፋፈሩም ነበር።

4) ኢየሱስ ክርስቶስ ከ12ቱ ደቀ መዛሙርት ጋር ጉባኤ አድርጎአል፡፡

● ማር.3÷13-15

13- ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ።

14- ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥

15- ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤

5) በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የተገለጸው የጉባኤ ሁኔታ ምንድን ነው? ሐዋሪያ ጳውሎስን በደረሰው ጭንቀትና መከራ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ከእርሱ ጋር አብራ ሆናለች፡፡

● ፊልጵ.4÷14-15

14- ሆኖም በመከራዬ ከእኔ ጋር ስለ ተካፈላችሁ መልካም አደረጋችሁ።

15- የፊልጵስዩስ ሰዎች ሆይ፥ ወንጌል በመጀመሪያ ሲሰበክ፥ ከመቄዶንያ በወጣሁ ጊዜ፥ ከእናንተ ብቻ በቀር ሌላ ቤተ ክርስቲያን በመስጠትና በመቀበል ስሌት ከእኔ ጋር እንዳልተካፈለች እናንተ ደግሞ ታውቃላችሁ፤

6) በሮሜ ቤተ ክርስቲያን የተገለጸው የጉባኤ ሁኔታ ምንድን ነው? በህብረት በመኖር ጥያቄዎቻቸውን መፍታት ነው፡፡

● ሮሜ16÷5

5- በቤታቸውም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከእስያ ለክርስቶስ በኵራት ለሆነው ለምወደው ለአጤኔጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ።

7) በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን የተገለጸው የጉባኤ ሁኔታ ምንድን ነው? ትልቅና ትንሽ ቡድን መሥርቶ ይኖራሉ፡፡

● ቄላስይስ.4÷15

15- በሎዶቅያ ላሉቱ ወንድሞችና ለንምፋን በቤቱም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልን።

3 ሐዋ.2÷43-47 ላይ የሚገለጸው የቤተ ክርስቲያን የጉባኤ ሁኔታ አግኝ፡፡ እንዴት እነዚህን ሁኔታዎችን ማድረግ እንደሚንችል ዘጠኝ ዓይነት የጉባኤ ሁኔታዎች ይገኛሉ፡፡

1) ታምራት የሚደረግ ጉባኤ
2) ኢየሱስ ክርስቶስን ያመኑት የሚያደርጉት (የሚሰበሰቡበት) ጉባኤ
3) ንብረቶችን በህብረት የሚጠቀሙበት ጉባኤ
4) ዕቃዎችን ሸጦ እንደየፍላጎታቸው የሚያከፋፍሉበት ጉባኤ
5) በየቀኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡበት ጉባኤ

6) በቤት ውስጥ እንጀራ የሚቆርሱ ያንንም በደስታ በንጽሑ ልብ የሚያደርግ ጉባኤ
7) እግዚአብሔርን በዝማሬ የሚያመሰግን ጉባኤ
8) ለሰዎች ምስጋናን የሚቀበለው ጉባኤ
9) ዕለት ዕለት የሚድኑ ነፍሳት የሚጨመርበት ጉባኤ ናቸው፡፡ እነዚህን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያደርጋሉ፡፡

● ሐዋ.2÷43-47
43- ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።
44- ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤
45- ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።
46- በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤
47- እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

4. ሰይጣን ጉባኤውን ማበላሸት የጀመረው በኤደን ገነት ነው፡፡ ሰይጣን ጉባኤውን እንዴት እንደሚያፈርስ አግኝ፡፡
1) በኤደን ገነት የሰይጣን ሤራ የእግዚአብሔርንና የሰው ህብረት ሰበረ፡፡ ስለዚህ የማይታዘዝ ህብረት ይፈርሳል፡፡ ሰይጣን በእኛ ሕይወት ህብረት ሊኖረን አያስፈልግም፡፡ የምናወርሰውን ነገር ልንገነባ ያስፈልጋል፡፡ ክርስትና በሃይማኖት የምንወዳደርበት ሳይሆን ህብረት የምናደርግበት ነው፡፡
● ዘፍ.3÷1-6
1- እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።
2- ሴቲቱም ለእባቡ አለችው። በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን
3- ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም።
4- እባብም ለሴቲቱ አላት። ሞትን አትሞቱም
5- ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።
6- ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።

2) አዳምና ሄዋን የቤተሰብን ህብረት ስላፈረሱ በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ ገቡ፡፡ ከዚህ የተነሣ የባልና የሚስት ህብረትን አፈረሰ፡፡
● ዘፍ.2÷23
23- አዳምም አለ፦ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።

● ዘፍ.3÷12
12- አዳምም አለ፦ ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠሽኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ።

3) ቃየል ወንድሙን በመግደል የቤተሰብ ህብረት አፈረሰ፡፡ የመጀመሪያውን የቤተሰብ ስብስብ አፈረሰ፡፡
● ዘፍ.4÷3-9
3- ከብዙ ቀን በኋላም ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረበ
4- አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኵራትና ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ
5- ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም። ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ።
6- እግዚአብሔርም ቃየንን አለው። ለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ?
7- መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።
8- ቃየንም ወንድሙን አቤልን፦ ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው። በሜዳም ሳሉ ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሣበት፥ ገደለውም።
9- እግዚአብሔርም ቃየንን አለው፦ ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? እርሱም አለ፦ አላውቅም የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን?

4) ከ12ቱ ደቀ መዛሙርት ውስጥ አንዱ የአስቆሮንቱ ይሁዳ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ በመስጠት በህብረቱ ውስጥ አደጋ አመጣ፡፡
● ዮሐ.13÷2
2- እራትም ሲበሉ ዲያብሎስ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ በይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኋላ፥

★ የሚከፋፈል
ክፍል ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው የጉባኤ አስፈላጊነት ከጻፍክ በኋላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡፡

5. በክፍል ቤተክርስቲያንና በባህል ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው ልዩነት አግኝ፡፡

1) የትንሽ ቡድን ትርጉምና የዋጋ ልዩነት ምንድን ነው?

ክፍል ቤተ ክርስቲያን ማለት በሥጋና በነፍስ ጥቂቶች የሆኑ ማለት ነው፡፡ ደጋግሞ ደቀ መዛሙርት የሚያደርጉ ማለት ነው፡፡ ባህላዊ ቤተ ክርስቲያን የአንድ ድርጅት ፕሮግራም የሚታስፈጽም ማለት ነው፡፡ ይህ በትልቅ ቡድን ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡

2) ስለ ሕንፃ ሀሳብ ልዩነት ምንድን ነው?

ክፍል ቤተ ክርስቲያን ጉባኤውን (ስብስቡን) ማዕከል ያደረጉ ስለ ሕንፃው መጠን ያልወሰኑት ናቸው፡፡ ባህላዊ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃውን ማዕከል ያደረጉ ሁሉንም ፕሮግራሞችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

3) ታላቅ ሕንጻና የሕንጻ ልዩነት ምንድን ነው?

ክፍል ቤተክርቲያን ሂድና አገልግል የሚለውን መርህ ታደርጋለች፡፡ ባህላዊ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ና የሚለውን መርህ ታደርጋለች፡፡

4) ክርስቲያንና አገልጋይ (የሥራ ሰው) ልዩነት ምንድን ነው?

ክፍል ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች ሁሉም አገልጋዮች ካህናት የክፍል መሪዎች ናቸው፡፡ ይህንን የሚገነቡት በሥልጠና (በልምምድ) ነው፡፡ ባህላዊ ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ሰሜናሪ ትምህርት የተመረቁ ሰዎች ብቻ መሪ በመሆን ይመራሉ፡፡ ሥራቸው ሁሉ ውጤት ተኮር ነው፡፡

5) የልምምድ ልዩነት ምንድን ነው?

ክፍል ቤተ ክርስቲያን ጥሩ አስተማሪና መሪ የሚሆኑ ደግሞም ሆኖ እንዲገኙ ዋጋ የሚከፍሉ ናቸው፡፡ ባህላዊ ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ ያስተምራሉ፡፡

6) የመምራት ልዩነት ምንድን ነው?

ክፍል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪዎች እንዴት ያገለግላሉ? በባህላዊ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪዎችስ እንዴት ያውቃሉ?

6. ክፍል ቤተ ክርስቲያን እርግጥ መሠረትና ዋጋ ምንድን ነው?

1) የጠፉትን አንድናገኝ (ትንሽ) ክንፍ እያዳነን የእግዚአብሔር ቅርጽ ያላት ቤተ ክርስቲያንን ማግኘት ነው፡፡

2) በእኛም ህብረተሰብ ውስጥ እንዲኖር ነው፡፡ ቤተሰብ በእምነት ተመክቶ እንዲረዳዱ ነው፡፡

3) የጌታን መምጣት እንድንጠባበቅ ማድረግ ነው፡፡

4) ሁሉም ክርስቲያኖች አገልጋዮች እንዲሆኑ ነው፡፡

5) በማባዛት ሥርዓት እጥፍ ትውልድን ለማግኘት ነው፡፡

★ ማስተካከያ

ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተማረኸው ነገር ሕይወትህን ሊታስተካክል የፈለግኸውን ከጻፍክ በኋላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወደሆነች ቤተ ክርስቲያን ለመቀየር በደንብ ጸልይ፡፡

ምዕራፍ ስድስት

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚጠራጠር ሕይወት ይወድቃል፡፡

● ገላ.5÷16-24

16- ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።

17- ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።
18- በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም።
19- የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥
20- መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥
21- መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።
22- የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።
23- እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።
24- የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።

የዛሬ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ነው፡፡ አባታችን እግዚአብሔር ልጁም ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በኩል ሥራቸውን ያደርጋሉ፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ ርዳታ እግዚአብሔር አብንና እግዚአብሔር ወልድን ማወቅ አይቻልም፡፡ እኛ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ እንደሆነ ስናምን መንፈስ ቅዱስ ወዲያውኑ በውስጣችን ይገባል፡፡ የዛሬ ዘመን ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥልቅ ዕውቀት ባለመኖራቸው ምክንያት መንፈስ ቅዱስን ይጠራጠራሉ፤ መንፈስ ቅዱስንን ስጠራጠሩ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይጠፋል፡፡ መንፈስ ቅዱስ የማይገለጥ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛውን ሥራ የሚያገለግሉት በሀሳባቸው ብቻ ነው፡፡ ሰይጣን በእኛ ሕይወት ውድቀትን ለማምጣት ይወድዳል፡፡ የክርስቲያኖች ሥልጣን የመንፈስ ቅዱስ አብሮ መኖር ነው፡፡ አሁን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሥራ በሕይወታችን፤ በቢሮአችን፤ በተለያዩ ሥፍራችን እንዴት እናደርጋለን?

★ የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ሥጦታ ጥሩ መረዳት

① የፀጋ ሥጦታ እግዚአብሔር እንደወደደው የሚሰጥ ነው፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ነው እንጂ ርኩስ አይደለም፡፡
② የአገልጋዩ ሰው ፀባይና ውጤት አይገናኝም፤ ፀባይና ባህርይ ግኑኝነት የላቸውም፡፡ የፀጋ ፀባይ አያሰድብም፡፡ የጸጋ ሥጦታ መጠራጠር ማለት እግዚአብሔርን መሳደብ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም የሚገዛ ነው፡፡
③ የጸጋ ሥጦታ በራሱ ፈቃድ መቀበል አይቻልም፡፡ የጸጋ ሥጦታ በመንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ እንደፈቀደው ይሰጣል፡፡
④ የጸጋ ሥጦታ ከእግዚአብሔር ሥራ ጋር ግንኙነት አለው፡፡ እግዚአብሔር የሚሰራበትን አካባቢ ሁል ጊዜ ይገልጻል፡፡ ስለዚህ ለሰዎች ጸጋ ስጦታውን ያድላል፡፡ በውጊያ ጊዜ ጤበንጃ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ለክርስቲያኖች የጸጋ ሥጦታ በመስጠት ጠላትን እንዲያሸንፉ ያደርጋል፡፡

1. የዛሬ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ቀላል በሆኑ ዕቃዎች እንሳሳታለን፡፡ ይህ ነገር ሊሆን አያስፈልገውም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከስላሴ አንዱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህ ሕይወታችን ሁሉ፤ የሚንሰራበት አካባቢውን ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፈን መስጠት አለብን፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ እንዲሳሳቱ ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው?

1) የስህተት አስተመሪዎች መብዛት፡፡ እነዚህ አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ኃይል ክዶ ሐሰት ትምህርቶችን በማስተማር ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖር ስለሚያደርጉ ነው፡፡
2) ቤተ ክርስቲያን በእምነት ባለማደጓ ምክንያት ነው፡፡ በምንማርበትጊዜ ብዙ ሊንጎዳ ወይም መከራ ሊደርሰን ይችላል፤ ደግሞም ልናዝን እንችላለን፤ ነገር ግን በጌታ ፊት በንስሐ ወድቀን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሊንቀበል እንችላለን፡፡
3) ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ ዕውቀት ባለመኖር ምክንያት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡፡(ዕብ.13÷8)
4) ስለ መንፈስ ቅዱስ መረዳት ደካማ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡

● ማቴ.16÷21-23
21- ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር።
22- ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ። አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።
23- እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን። ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።

2. ሰይጣን ይህንን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጥቅም እንዳናገኝ ይጋርዳል፡፡ እንዴት እንደምጋርድ አግኝ፡፡

1) የሰይጣን ግብ ምንድን ነው?
① ግቡ በዓለም ሁሉ ንጉሥ ሆኖ መንገሥ ነው፡፡

● ኢሳ.14÷13-14
13- አንተን በልብህ። ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ
14- ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ።

② የሐሰት አባት መሆን

● ዮሐ.8÷44

44- እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።

③ ሰውን እስረኛ ማድረግ

● ሐዋ.10÷38

38- እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤

2) ሰይጣን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ተቃወመ (ጋረደ)

ኢየሱስ ከጾመ በኋላ ሰይጣን ፈተነ።(ማቴ.4÷1-11)

● ማቴ.16÷21-23

21- ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር።

22- ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ። አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።

23- እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን። ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።

3. መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያንና ለክርስቲያኖች ሰይጣንን የሚያሸንፉበትን ሥልጣን ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ሥልጣን ምንድን ነው?

1) የመንግሥተ ሰማይ መክፈቻ ቁልፍ ሰጠ፡፡

● ማቴ.16÷19

19- የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።

2) የሰይጣን ሥልጣን ሁሉን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥልጣን ሰጠ፡፡

● ሉቃ.10÷19

19- እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።

3) በአዲስ ኪዳን ዘመን የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር እንዳደረገችው ያንን ሥራ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ (ሐዋ.2 ምዕራፍ)

4) በአዲስ ኪዳን ዘመን የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በደንብ ለማየት የምትፀልይ፡፡

ክርስቲያኖች በዝርዝር ይፀልያሉ፡፡

● ሐዋ.4÷29-31

29-30 አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው።

31- ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

4. በመንፈስ ቅዱስ ሥራ በኩል የእግዝአብሔር ቤተክርስቲያን ጠንክረን ልንገነባ አደረጉ። ስለዚ እኛ የመንፈስ ቅዱስ ሐይል ለማግኘት መፀለይ ያስፈልጋል ፡፡

መንፈስ ቅዱስ ራሱን ለመቀበል ለሚስማማ ሰው ጠንካራ ሥራ ያደርጋል። መንፈስ ቅዱስ መቼ ይህን ይሠራል?

1) በሙሉ ልብ በሚፀለይበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ይሰራል፡፡

● ሐዋ.1÷14

14- እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።

2) ክርስቲያን በሚስብሰባ ጊዜ ይሰራል። ዓይኖችን ያሳያል፤ ጆሮአችን ይሰማል፡፡

● ሐዋ.2÷1-4

1- በዓለ ጎምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥

2- ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።

3- እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው።

4- በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።

3) ብዙ ድንቅና ታምራት ይሠራል፡፡

● ሐዋ 2÷43

43- ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።

4) የቤተ መቅደስ መግቢያ በር ላይ የማያስቀምጡት አንድ ከተወለደ ጀምሮ ሽባ የሆነ ሰው ነበረ፤ ይህ ሰው ተነሣ።
● ሐዋ 3÷6-8
6- ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።
7- በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና፥
8- ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፥ ይመላለስም ጀመር፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ።

5) በሙሉ ልብ በሚፀለይበት ጊዜ በአንድ ስፍራ ተናወጠ የእግዚአብሔርን ቃል በግልጥ እንዲናገሩ መንፈስ ቅዱስ በሙላት ይሰራል። መንፈስ ቅዱስ ይሠራል፡፡
● ሐዋ.4÷29-31
29-30 አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው።
31- ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

6) የወንጌል ምስክርነት እንዲያደርጉ ያደርጋል።
● ሐዋ 8÷4-8
4- የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።
5- ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው።
6- ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ።
7- ርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና፤ ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤
8- በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።

7) የእግዚአብሄርን ቃል እንዲሰሙ በቆርንሴዎስ ቤተሰብ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት እንዲቀበሉ አደረገ።
● ሐዋ 10÷44-46
44- ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ።
45- ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለ ፈሰሰ ተገረሙ፤
46- በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና።

8) የሐዋርያት ጳውሎስ ለብስ ጨርቅና መሐረብ ወደ ሕመምተኞች ሲወስዱ ጨርቁን የዳሰሱት እንዲፈወሱ ያደርጋል ፡፡
● ሐዋ 19÷11-12
11- እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር፤ ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር፥
12- ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር።

5. የጌታ ኢየሱስ ምሪትና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መፈለግ እንዴት እንደሚሰራ አግኝ።
1) ህመምተኞችን ስትሰበሰቡ እንዴት ማድረግ አለብን?
① ህመምተኞችን የራሳቸውን ነፍስ እንዲወድ ያደርጋል፡፡ ኢየሱስን እንዲቀበሉ ያደርጋል፤
② በሥጋ ቦታ ላይ እጅ በመጫን መጸለይ
ማስጠንቀቅያ - ለሴቶች አደገኛ ስፍራ ጡታቸው ላይ ጭኖ መጸለይ
አይፈቀድም በጭንቅላታቸው ስሜት በማይቀሰቅስ አካላት ላይ መጋቢው ጭኖ መጸለይ አለበት፡፡
③ በዝርዝር ትዕዛዞችን መናገር፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስልጣን መናገር
④ በጌታ ኢየሱስ ፍቅር በማፍቀር ግል ማድረግ

2) ስለሕመምተኞች ፈውስ ከመጸለይ በፊት የሚያገለግሉ አገልጋዮች ሊያዘጋጁ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
ከኃጢአቴ ከንስሐ በኋላ መጸለይ ያስፈልጋል፡፡

3) ስለ ፈወስ በሚጸለይበት ጊዜ እንዴት ማድረግ አለብን?
በጌታ ኢየሱስ ፍጹም በመታመን፤ በድፍረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

4) በኢየሱስ ስም እንዴት መናገር ይቻላል? በሀይልና በድፍረት በፍቅር ልብ በማረጋገጥ በደስታ መናገር ያስፈልጋል፡፡

5) ጌታ ኢየሱስ በማን በኩል ሊሰራ ይፈልጋል? በእኔ ወይም በአንተ በኩል ሊሰራ ይፈልጋል፡፡

6. ክርስቲያኖች እውነተኛ የፈውስ ሥራ ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡ ይህን እንዴት ማድረግ ይቻላል?

1) በማን ስም ማድረግ ይቻላል? በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማድረግ ይቻላል፡፡

2) በማን ስልጣን ማድረግ ይቻላል? በመንፈስ ቅዱስ ስልጣን፡፡

3) ስለ ምን እናደርጋለን? ስለ እግዚአብሔር ክብር፡፡

4) መቼ እናደርጋለን? ዘወትር ምቹ ጊዜ ስናገኝ፤ መንፈስ ቅዱስ ስሜታችንን በሚሰጠ ጊዜ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ያለ ጥርጥር መጸለይ ያስፈልጋል። የጸጋ ስጦታ ካልተጠቀምንበት ይጠፋል፡፡

5) ስለ ፈወስ በምታገለግልበት ጊዜ የልባችሁን ሁኔታና አቋም ምን ታደርጋላችሁ? ጌታ ኢየሱሰ ክርስቶስን በማመን በድፍረት ማድረግ ያስፈልጋል።

★ የፈውስ አገልግሎት ለምን እናደርጋለን?

① ሕመምተኖችን ለመርዳት የእግዚአብሔር ተስፋ ፍቅር ስለሆነ

② አገልጋዩ የራሱን እምነት እንዲያሳድግ

③ አገልጋዩ በመንፈሳዊ ህይወቱ ድል እንዲደርግ

④ አገልጋዩ በመንፈስ ቅዱስ ስልጣን በየቀኑ እንዲጨምር

⑤ በወንጌል ምስክርነት እንዲፈለገ፤
በየቀኑ ከአስር ደቂቃ የሚበልጠውን ሀይል የጸጋ (ፈውስ) ስጦታ ለመቀበል መጸለይ ያስፈልጋል፡፡

★ ማስተካከያ

ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተማረኸው ነገር ሕይወትህን ሊታስተካክል የፈለግኸውን ከጻፍክ በኋላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት

የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ለመቀበል በደንብ ልትጸልይ ያስፈልጋል ፡፡

ምዕራፍ ሰባት

ኢየሱስ ክርስቶስን መለማመድ ክፍል ቡድን(ሐዋ.2÷44-47)

በእስያ ታላቅ አንደኛ ክፍል ቤተክርስቲያን ማደግ የእንዶኔዚያ አገር GBI ቤተክርስቲያን መጋቢ Obaja እንዲህ ነገረ:: "you can be cell leader" "just do it'' ይህ ቃል ክርስቲያኖችና አዲስ ክርስቲያኖች የሚያዩ ዓይኖችን ከፈተ። መጋቢ Obaja የሚያያቸውን ሰዎች "አንተ የክፍል መሪ መሆን ትችላለህ" ብሎ መናገር ጀመረ፡፡ ከዚህ በኋላ GBI ቤተክርስቲያን በማደግ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ሆነ፡፡

1. ክፍል ቡድን ማለት ምን ማለት ነው?

1) በኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው አንድ የቤተሰብ ስብሰባ ነው፡፡

2) እንደ ቤተሰብ ሳይሆን አንድ ቤተሰብ የሆኑ ናቸው፡፡ ክርስቲያኖች አብረው መኖር ማለት አብረው በታማኝነት የሆኑ ማለት ነው፡፡

3) ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ስልጣንና ግብን ልምድ የሚያደርጉ ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ከፍ የሚያደርጉና የሚያከብሩ ናቸው፡፡ ኢየሱስን ስተስማማ መንፈስ ቅዱስ ይመጣል። ጨለማችን ይፈወሳል፡፡

4) የእኛ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሕይወታችንን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንድንገልጥ ማሳረፍ ያስፈልጋል፡፡

5) ክፍል ቡድን ሕያው ማብዛት ነው፡፡ የሕያው ምስክርነት ማብዛት ነው፡፡

2. ክፍል ውስጥ ያለው ቤተክርስቲያን ሀሳብ አግኝ::

1) ክፍል ማለት አካልን (ቤተክርስቲያን) መሰረታዊ ነገር ነው፡፡

2) ክፍል እንዲ ማብዛት እንዲያደርጉ ነው፡፡

3) ክፍልና ክፍል ግንኙነት እንዲያደርጉ ነው፡፡

4) የክፍል ግብ ነፍስን እንዲኖር ነው፡፡

5) የክፍል ሥራ (አገልግሎት) ቤተክርስቲያን መሪ ለመቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡

3. ክፍል ስላሴ እግዚአብሄር የሚኖርበት ውስጥ እንደገባ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሄር መምጣት ሥልጣንን፤ ግብና ልምድ ያስፈልጋል፡፡

1) የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ማለት ምን ማለት ነው?

በመዝሙርና በጸሎት ጊዜ ኢየሱስ መምጣት ይችላል። በእኛ ኑሮ ከእግዚአብሄር ጋር ሕብረት ማድረግ አለብን፡፡
2) የኢየሱስ ክርስቶስ ስልጣን ማለት ምን ማለት ነው?
የእግዚአብሄር ቃል እያንዳዱን ሰው መገንባት፤ ለመፈወስ፤ ያጽናናናል።
3) የኢየሱስ ክርስቶስ ግብ ምንድን ነው? ወንጌልን ለፍጥረታት ሁሉ መስበክ ነው፡፡
4) የእኛ ህይወት መሰረታዊ ነገር (DNA) ምንድን ነው? እየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በክፍል ቡድን ኢየሱስ ማዕከል መሆን ይፈልጋል፡፡

4. በክፍል ቡድን ሕያው የሆነውን ነገር ለመያዝ የሚጠቅሙ 6 ዓይነት አስፈላጊ ሁኔታዎችን አግኝ፡፡
★ የክፍል ሕይወት 6 ዓይነት ሁኔታዎች

1) ጉባኤ (ቤተሰብ)
አብሮ በመርዳት በእውነት ትመካለህ? ዮሐ.15 ምዕራፍ በክፍል በጣም የሚያስፈልግ ነገር ሁሉንም ሥራ በጉባኤ (ቤተሰብ) ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

2) ልምምድ (ስልጠና)
አዲስ ክርስቲያኖችና አዲስ ቤተሰብን ልምምድ (ስልጠና) ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
● ማር.10÷13
13 እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን ገሠጹአቸው።

3) እርስ በርሰ መርዳት
መንፈስ ቅዱስ በሚመጣበት ጊዜ እርስ በርሰ በመረዳዳት፤ በመጽናናት እንደስራ ይረዳል። መንፈስ ቅዱስ በትንሽ ቡድን ጉባኤ (ቤተሰብ) ውስጥ የሰዎችን ፍላጎት ሰጥቶ ፍቅር ግንኙነት ለማድረግ ይፈልጋል፡፡
● የሐ.14÷16
15-16 ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤

4) መሪነት (አገልግሎት)
በክፍል በአባታዊነት ልብ መያዝ በጣም የሚያገለግል የክፍል መሪ ነው፡፡
● ሮሜ.8÷15
15- አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና።

5) የወንጌል ምስክርነት
የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ማካፈል፤ የክፍል ቡድን ተልዕኮ ነው፡፡ ክፍል የሚያደርሱትን ግብ ይሰጣል፤ ወደ ጥፋት ሰዎች መሄድ ያስፈልጋል፡፡
● ዮሐ.3÷16
16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

6) የዚህ ሁሉ ማዕከል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡
ክፍል ሕያው ሆኖ እንዲሄድ ማዕከሉ ኢየሱስ ነው፡፡
● ቆላ.1÷27
27- ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፥ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው።

5. ክፍል ቡድን 5W ሊያደርጉ ይገባቸዋል። እንዴት እነዚህን ማድረግ አግኝ፡፡
1) በደስታ መቀበል(welcome)
የልባቸውን በር መክፈት፤ በአካባቢ በታሪክና በጨዋታ ወዘተ… የልባችንን በር መክፈት

2) ዝማሬና አምልኮ(worship)

3) ቃል(word)
የእግዚአብሄርን ቃል ሲሰማ የኢየሱስ መምጣት መሰማት፤ ወደ ጸጋ ስፍራ መሄድ ያደርጋል። የእግዚአብሔርን ቃል ብታዘዘ የእግዚአብሄር ድምፅ ሰማ። የልባችንን ትልቅ ስቃዮችን እንደሚፈውስ ልምድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

4) የወንጌል ምስክርነት(witnesses)
በልባችን ውስጥ ያለውን መከራዎችን ፈወሰን። እኛን የሚያሳስበን ነገር የሚጠፋውን ሰዎች እንድናገኝ ነው። እኔን የሚፈወሰው እግዚአርሔር ቤተሰቤንና ጎረቤቶችን እንደፈወሰ ራዕይን በመያዝ ስለ ሌሎች መጸለይ አለብኝ፡፡ የእግዚአብሔርን ፍቅር መያዝ ወደ ሰዎች እንዴት እንደሄድ ስትራቴጂ መገንባት ያስፈልጋል፡፡

5) መርዳትና ጸሎት(work and prayer)
የርዳታ የሚፈልጉ ሰዎች ባለው አንድ ላይ ጸሎት ማድረግ፡፡
① ችግሮቻቸውን ለእግዚአብሄር ሰጥቶ መጸለይ
② ስለ አዲስ ዋና ሰውና ስለ ክፍት ስብሰባ መጸለይ
③ ስለ ፈውስና ስለ መንፈስ ቅዱስ እንዲበዛ መጸለይ
④ ደሀዎችን እንዲረዳ መጸለይ
ክፍል መሪ በጨረሰ ጊዜ ጸለየ

6. በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የተትረፈረፈ ክፍል ቡድን ፍሬን ማፍራት እንዴት ማድረግ ይቻላል?
1) አንድ ሳምንት አንድ ጊዜ መሰብሰብ ሳይሆን አንድ ሳምንት አንድ ላይ በመኖር መርዳትና ማገልገል ነው፡፡
ክፍል ሕይወት በአንድ ሳምንት መቀጠል ማድረግ ነው። ክፍል ሕይወት ክንውን የተትረፈረፈ ክፍል ስብሰባ ገለጠ። ውጤት ማብዛት ነው፡፡
2) አብሮ መቀበልና መርዳት መስጠት
3) በግልጥ ማካፈል

★ ሰዎች ለምን ብቸኛ ሆነው ይኖራሉ?
① እምነት በማጣታቸው ምክንያት ውስጣቸው ስለተሰበረ፤ ነው፡፡
② አንዱ ሌላውን መጥፎ ነገር እንዳይለው ስለፈሩ ነው፡፡
③ ልባቸውን እንዴት በመክፈት ግኑኝነትን እንደሚያደርጉ ስላላወቁ ነው፡፡

4) በጸጋ ሥጦታ በኩል ማገልገል ያስፈልጋል፡፡
5) አብሮ ፍቅርን መካፈልና መጸለይ ያስፈልጋል፡፡

★ ጥሩ ክፍል ቡድን የሚደርግ ሁኔታዎች
① በፍቅር መቀበል
② ደኅንነትና እምነት
③ መረዳትና ማጽናናት
④ ተስፋና ምስጋና
⑤ ጥሩ ምሳሌን ሰጥቶ ስልጣንና መቆጣጠር
⑥ የተከፈተ ልብና በታማኝነት ማድረግ
⑦ ባለ ጊዜ በነጻነት መናገር
⑧ ስለ ሥራ ማዕከል መሆን

7. የክፍል ሕያው ስልጣን አዲስ ሕያው የሆነን መውለድ ነው። ይህ ለምን እንደሚያስፈልግ አግኝ።
1) የወንጌል ስብከት ትንሽ ቡድን አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ማለት ክፍት ስብሰባ (3-4 ሰዎች) ማለት ነው።
2) አዲስ ሰው ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጣ በባዶ ወንበሮች ላይ ማስቀመጥና መጸለይ ያስፈልጋል፡፡
3) የወንጌል ምስክርነት ዘዴ ብዙ ዓይነት አለ፡፡
4) ያልተወለደ ክፍል ቡድን የነቀርሳ ክፍል ነው። ያልተወለደ ክፍል በስጋ ውስጥ ነቀርሳ ነው።
5) ክፍል ቡድን እውነተኛ ፍሬ እንደገና ሌላ ክፍል ቡድን ነው። የማንጎ ፍሬ እውነተኛ ፍሬ እንደገና ሌላ የማንጎ ፍሬ ነው።

★ ማስተካከያ
ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተማረኸው ነገር ሕይወትህን ሊታስተካክል የፈለግኸውን ከጻፍክ በኋላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት

የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት፤ ሥልጣን፤ ግብን መልምድ ክፍል ቡድን እንዲሆን ጸልይ፡፡

አስቀድሞ ክፍል በሥራ ስዓት ዳግመኛ የተወለደ መሆን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በማባዛት በኩል ለማካፈል የደስታ ጊዜ ነው። 2 ዓመትና 3ዓመት ሳለ የማያባዛ ክፍል ሕያው የሚኖር ክፍል ጋር አንድ ላይ ህብረት ማድረግ ያስፈልጋል። የማያበዛ ክፍል ነቀርሳ ነው፡፡

ምዕራፍ ስምንት
የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ነፍስን መማረክ

● 1ቆሮ.12÷7-10

7- ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው፡፡

8- ለአንዱ በመንፈስ የጥበብን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው መንፈስ የዕውቀትን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤

9- ለአንዱ በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታዎች ይሰጠዋል፤

10- አንዱ ታምራትን የማድረግ፤ ለሌላው ትንቢትን የመናገር፤ ለሌላው ደግሞ መናፍስትን የመለየት፤ ለአንዱ በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር፤ ለሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ ልሳን የተነገረውን የመተርጐም ስጦታ ይሰጠዋል፡፡

ደቀመዝሙርነት ከመምህሩ ጋር አንድ ንግግር፤ አንድ ልብ፤ አንድ ፈቃድ፤ አንድ ፍሬዎችን ያፈራል። ደቀመዝሙርቱ መምህሩን የሚከተሉት ሰዎች ናቸው፡፡ የዘላለም መምህራችን የሆነው ጌታ ኢየሱስ የሚያሳስብ ነገር ነፍሳት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የጌታ ደቀመዝሙርቶች ደግሞ የሚያሳስባቸው ኢየሱስ ክርስቶስን ያላመኑ ሰዎች ሀሳባችን ያለው ያስፈልጋል።

ብዙዎች ቤተክርስቲያንና ክርስቲያኖች ያላመኑ ሰዎችን በወንጌል ብዙ መሐፍት፤ ለማሰልጠን ስራ አድርገው ይሰራሉ፡፡ ነገር ግን ከዚህ አይነት ከወንጌል ስብከት የሚበልጠው አስፈላጊ ነገር አለ፡፡ ይህም በአዲስ ኪዳን ዘመን ቤተክርስቲያን እንደገለጥ ታላቅ ተሐድሶ ማወቅ ማስተካከል፤ የእኛ ሥራ (አገልግሎት) ደግሞ ታላቅ የወንጌል ሰባኪዎች እንሆናለን።

★ አሁን ቤተክርስቲአን የጠፉ ነገሮች

① ደቀመዝሙርነት የማድረግ ራዕይ መጥፋት (ማቴ.28÷18-20)
② ሥልጣን መጥፋት (ሐዋ.1÷8)
③ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ሥጦታ መጥፋት (ቆሮ.12÷4-11)
④ ሥልጣንን የሚማርክ ደቀመዝሙር መጥፋት (ማር.3÷13-15)
ታማኝ ደቀመዝሙሮቶች አሉ፤ ነገር ግን ሥልጣንን ለመውሰድ ደቀመዝሙርት የለም፡፡

1. አዲስ ኪዳን ዘመን የመጀመርያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋ.ጴጥሮስ አንድ በስብከት ጊዜ 3ሽህና 5ሽህ ሰዎች በንሥሐ ወደ ጌታ መለሳቸው፤ ፊልጶስ ወንጌልን በመምስከር ጊዜ ብዙ ሰዎች ያመኑት ክርስቲያኖች ሆኑ፡፡ እንዴት ይህንን ሥራ ማድረግ ቻሉ? አዲስ ኪዳን ዘመን የመጀመርያ ቤተክርስቲያን መገለጸ ተሃድሶ ምሥጢር ምንድን ናቸው?

1) በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ሞላባቸው።

● ሐዋ.2÷1-4

1- በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥

2- ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።

3- እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው።

4- በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር

2) በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሁለት ክንፎች ያለት ቤተክርስቲያን ገነባ።

● ሐዋ.2÷41-47

41- ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤

42- በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።

43- ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።

44- ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤

45 ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።

46 በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤

47 እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

3) በመንፈስ ቅዱስ ሥራ፤ በቃል ሥልጣን 5ሺህ ስዎች አመኑ።
● ሐዋ.4÷4
4- ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፥ የወንዶችም ቍጥር አምስት ሺህ ያህል ሆነ።

4) የመንፈስ ቅዱስ ሥራና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በስፍራው ተገልጦ፤ የምድር መንቀጥቀጥ ታይቶ የእግዚአብሄርን ቃል አጥብቄ ስበኩ።
● ሐዋ.4÷28-31
27-28 በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ በኢየሱስ ላይ ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር፥ እጅህና አሳብህ እንዲሆን አስቀድመው የወሰኑትን ሁሉ ሊፈጽሙ፥ በዚች ከተማ በእውነት ተሰበሰቡ።
29-30 አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው።
31- ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

5) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጵልጶስ በሰማርያ ከተማ ወንጌልን ሰበከ።
● ሐዋ.8÷4-8
4- የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።
5- ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው።
6- ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ
7- ርኵሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና፤ ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤
8- በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።

2. የጸጋ ሥጦታ እግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው።
እኛ ይህንን ለማገልገል ቤተክርስቲያን መገንባት፤ ወንጌልን ሥልጣን ለመስበክ እንችላለን። ነገር ግን የጸጋ ሥጦታ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ መገንባትና ጥላቻ ብዙ አለ። የዚህ ሁሉ ምክንያት ምንድን ነው?
1) ስለ ጸጋ ስጦታ ሐሰተኛ ሰዎች መካድ ምክንያት
2) ስለ ጸጋ ስጦታ ባለማሰባቸው ምክንያት
3) ስለ ጸጋ ስጦታ የመረዳት እጥረት ምክንያት
4) የጸጋ ስጦታ የተሳሳተ ጥቅም ምክንያት

3. መንፈስ ቅዱስ ግልጽነት ግብን መያዝ ለቤተክርስቲያን የጸጋን ስጦታ ሰጠ።
1) የጸጋ ስጦታ የሚሰጠው ምክንያት ለቤተክርስቲያን ጥቅምን መስጠት ሰጠ፡፡
● 1ቆሮ.12÷7-11
7- ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል።
8- ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፥
9- ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፥ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፥
10- ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤
11- ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።

2) ዓለምን ሁሉ በማሸነፍ የአግዚአብሔር ምስክሮች ትሆናላችሁ፡፡
● ሐዋ.1÷8
8- ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

3) እንደ ተከፋፈለ እሳት የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ለያንዳንዱ ሰጠ።
● ሐዋ.2÷1-4
1- በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥
2- ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።
3- እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው።
4- በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።

4) የጸጋ ስጦታ የሚሰጠው ጥቅም ነፍስን ለማዳንና ቤተክርስቲያንን ለመርዳት ነው።
● ሉቃ.10÷17-19
17- ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው። ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት።

18- እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።
19- እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።

5) ነፍስን ለማዳን

● ማር.3÷13-15
13 ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ።
14 ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥
15 ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤

6) ነፍስን ለማዳን መንፈስ ቅዱስ ሥልጣንን ይስጣል፡፡

● ማር.16÷15-20
15-እንዲህም አላቸው፣ "ወደ መላው ዓለም ሂዱ፣ ለሰው ሁሉ ወንጌልን አስተምሩ፡፡
16- ያመነና የተጠመቀ ይድናል፣ የማያምን ግን ይፈረድበታል፡፡
17- በእኔ የሚያምኑ ሁሉ እነዚህን ተአምራት ያደርጋሉ፣ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፣ በአዲስ ቋንቋም ይናገራሉ፣
18- እባቦች ቢይዙ፣ ወይም የሚገድል መርዝ እንኳ ቢጠጡ አይጐዳቸውም፣ እጃቸውን በበሽተኞች ላይ ሲጭኑ በሽተኞቹ ይድናሉ፡፡"
19- ጌታ ኢየሱስ ይህን ሁሉ ከነገራቸው በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ፡፡
20- ደቀ መዛሙርቱም በየስፍራው ሁሉ እየሄዱ አስተማሩ፣ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፡፡ ተአምራትንም የማድረግ ሥልጣን በመሰጠት የትምህርታቸውን እውነተኛነት ያጸና ነበር፡፡

4. እግዚአብሔር ለሰዎች ሰጥቶ ከፀጋ ስጦታ የፈውስ ስጦታ የእግዚአብሔር ሕያውና ሥልጣንን መግለጫ በጣም ጥሩ ስጦታ ነው፡፡ በመጸሐፍ ቅዱስ መገለጥ የመፈወስ ሥራ በኩል የመፈወስ ስጦታ በወንጌል ስብከት እንዴት እንደሚጠቅም አግኝ፡፡

1) በሐዋርያዎች በኩል ታምራትና የመልክት መገለጥ ውጤት ምንድን ነው?
ኢየሱስን ያመኑ ሰዎች በየቀኑ ተጨመሩ:: የወንጌል ስብከት ፍሬ አለ::
የሕይወት ኩራት አለው:: የወደፊት ስጦታ እንዳለ አመኑ፡፡

● ሐዋ.2÷43-47
43 ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።
44 ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤
45 ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።
46 በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤
47 እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

2) የመቅደስ በር ፊት ሐዋርያ ጴጥሮስ በእየሱስ ስም ሽባ ሰውን በተነሳ የታምራት ውጤት ምንድን ነው?
የኢየሱስ ስም ስብከትና ወሬ ሁሉም ቦታ ተስፋፋ፡፡

● ሐዋ.3÷6-10
6- ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።
7- በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና፥
8- ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፥ ይመላለስም ጀመር፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ።
9- ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲመላለስ አዩት፤
10- መልካምም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ስለ ምጽዋት ተቀምጦ የነበረው እርሱ እንደ ሆነ አወቁት፤ በእርሱም ከሆነው የተነሣ መደነቅና መገረም ሞላባቸው።

3) በኢየሱስ ስም ታምራትና ምልክት እንደገለጥ መጸለይ ውጤት ምንድን ነው?
ሰዎች አብረው የሚገናኙት ቦታ ተናዋጠ፡፡ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡፡ በሐይል የእግዚአብሔርን ቃል ስበኩ፡፡

● ሐዋ.4÷30-31
29-30 አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው።
31- ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

4) በፊልጶስ በኩል እግዚአብሔር የሚያደርገው ሥራና ውጤት ምንድን ነው?
ሰማርያ ከተማ ብዙ ክርስቲያን ሆነ፡፡

● ሐዋ.8÷4-8
4- የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።
5- ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው።
6- ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ።

7- ርኵሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና፤ ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤
8- በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።

5. ስለ መፈወስ ሥራ የማይአውቅን ሰው መቀስቀስ ያስፈልጋል። በምቀጥለው ጥያቄ መልስ አደረገ፡፡

1) እግዚአብሔር አሁን ህማሞችን ይፈውሳል? አዎን።
እግዚአብሔር ሕያውና ሰዎችን ይፈውሳል። ነገር ግን ክርስቲያኖች ሥራ አይሰራም።

2) እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ሁሉ ስለ ሕመምተኞች እንዲጸልዩ ይፈልጋልን? አዎን።
እኛ ስለ ህመምተኞች በፀሎት መቀጠል ያስፈልጋል፡፡

3) ለምን ሰዎች ይታመማሉ?
① በኀጢአት ምክንያት
② በመጥፎ አካባቢ በመኖራቸው ምክንያት
③ ምግብና ውሃ በማጣታቸው ምክንያት
④ ስለ ስጋ አሮጌ
⑤ በክፉ መንፈስ ምክንያት

4) የመፈወስ ዋጋና አስፈላጊነትን ያውቃል?
① እግዚአብሔር እኛ ጤናማና ደስተኛ ሆነን እንድንኖር ይፈልጋል::
② እግዚአብሔር በወንጌል ምስክር ጊዜ ለሰዎች የመፈወስ ስጦታ ሰጠ።

5) ጌታ ኢየሱስ በእኛም በኩል የመፈወስ ሥራን ማድረግ ይፈልጋልን? አዎን

6. አሁን የእግዚአብሔር ስልጣን መቀጠል ማግለጫ አለ፡፡ እንዴት በኢየሱስ ስም ማዘዝ አገኘ፡፡

★ ፈውስ እንዲታዘዝልን ደጋግመን መጸልይ

① በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ አንተ በሽታ ውጣ!
② እኔ በኢየሱስ ስምና በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን አዝሃለሁ በጉልበቱ ላይ ያለህ ህመም ውጣ!
③ በናዝሬቱ በኢየሱስ ስም አዝሃለሁ ራስምታት ውጣ!
④ እኔ በኢየሱስ አዘዝኩት አንተ ጉንፋን ከእኔ ውጣ!
⑤ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ፀለይኩ ይህን ፈውስ ስጥ!

★ ማስተካከያ

ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተማረኸው ነገር ሕይወትህን ሊታስተካክል የፈለግኸውን ከጻፍክ በኋላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እስካመገለጠ ድረስ በደንብ ጠርቶ ጸልይ፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ

ጌታ በደስታ ደቀ መዝሙርት

● 1ቆሮ 1÷10
10- ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ።

እግዚአብሔር በሰው በኩል ይሰራል፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ሃሳብ ሰው ነው፡፡ ኢየሱስ የሰውን ሥጋ ለብሶ በምድር ላይ መጥቶ ሥራውን ስጀምር አስራ ሁለት ደቀ መዝሙርት መረጣቸው። ኢየሱስ ሁሉን አልመረጣቸውም፡፡ የፈለጋቸውን፣ የወደዳቸውን፣ ብቻ እንጂ፡፡ ኢየሱስም ደቀ መዝሙርን ለመገንባት ወደ ተራራ ሄዶ ፀለየ፡፡ ሰውን መምረጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ለመምረጥ ሌሊቱን ሙሉ ፀለየ፡፡(ሉቃ 6÷12)
የፀሎቱ ዝርዝር ምን ነበር? እግዚአብሔር ማንን በደቀ መዝሙርት ለመምረጥ ይሰራል? የእግዚአብሔር ደቀ መዛሙርት ሆኖ የምመረጡ ማን ናቸው? ስለዚህ ከመጸለይ በኋላ በማለዳ ተነስቶ ስመጣ ኢየሱስ በፀሎት መልስ በኩል አስር ሁለት ደቀ መዛሙርትን መረጣቸው፡፡

እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ፀጋን ተቀበልን፡፡ እኛ የሚገኖረው በፀጋ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሰጠው ታላቅ በረከት እንኖራለን፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ፍቅርን ለእኛ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ከፀጋ ፀጋና በፀጋ ላይ ፀጋ አለን፡፡ ይህ ማለት የተልዕኮ ሰው ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር የሥራ መሣሪያ መቀበል ማለት ነው፡፡ ሙሴ የእግዚአብሔርን ጥሪ ተቀበለ፡፡ በሙሴ ህይወት ታላቅ ፀጋ ነበረ፡፡
የኢየሱስ እናት ማርያም የእግዚአብሔርን ምርጫ ተቀበለች፡፡ በማርያም ሕይወት ታላቅ ፀጋ ነበረ፡፡

1. ጌታ ምን ዓይነት ደቀ መዛሙርትን ፈለገ?

1) በአንድ ቃል የሚናገርውን ደቀ መዝሙርት ጠራቸው፡፡

2) በአንድ ልብ የሚሆን ደቀ መዝሙርት ያስፈልጋል፡፡

3) በአንድ ፈቃድ የሚሆን ደቀ መዛሙርት ያስፈልጋል፡፡

4) በአንድ ተክል የሚያፈሩ ደቀ መዝሙርት ያስፈልጋል፡፡

● 1ቆሮ፡ 1÷10

10- ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ።

2. የእምነትን ሚዛን እንዲመዘኑ ያስፈልጋል፡፡ የእምነትን ሚዛን የተመዘኑ ደቀ መዝሙርት እነማን ናቸው?

1) አንድ እምነት አንድ እውቀት አንድ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡

● ኤፌ 4÷12-13

12-13 ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።

2) ከሰሙ በኋላ የሚያደርጉ ሰዎች ናቸው፡፡

● ያዕ 1÷25

25- ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፥ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው፥ በሥራው የተባረከ ይሆናል።

3) ትዕግስተኛ ሰው ነው፡፡

● ያዕ 1÷2-3

2-3 ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት

4) መንፈስ ቅዱስን የሚከተልና የሚያደርግ ሰው ነው፡፡

● ገላ.5÷16-18

16- ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።

17- ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።

18- በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም።

5) የክርስቶስን አይነት እድገት የሚያድግ ሰው ነው፡፡

● ኤፌ 4÷13

12-13 ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።

3. ደቀ መዘሙርት በሚቀጥለው በሦስት አይነት መንገድ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ አግኝ፡፡

1) እኔ ማን ነኝ? መልስ፡

① እኔ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ነኝ፡፡

② እኔ የኢየሱስ ወታደር ነኝ፡፡

③ እኔ በኢየሱስ ሌሎችን እንደገና ደቀ መዘሙርት የሚያደርግ ሰው ነኝ፡፡

2) እኔ የት ነኝ? መልስ፡

① እኔ በኢየሱስ ውስጥ ነኝ፡፡

② እኔ የቤተ ክርስቲያን አካል ነኝ፡፡

③ እኔ የአንድ ቡድን ቤተሰብ አባል ነኝ፡፡

3) የእኔ አስተማሪ ማን ነው? መልስ፡

① ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የእውነት አስተማሪ ነው፡፡

② የቤተ ክርስቲያኔ መጋቢ፡ ወንጌላዊና መሪዎች ናቸው፡፡
አስተማሪ ማለት ኢየሱስን እንድናገኝ የሚረዳው ሰው ነው፡፡

4. ጌታ ኢየሱስን የሚከተሉ ደቀመዛሙርት ምን ዓይነት ሀሳብ መያዝ ያስፈልጋቸዋል?

1) የእግዚአብሔርን ሥልጣን እንዴት መታዘዝ ይቻላል?
መልስ፡ ፍጹም መታዘዝ
● ሮሜ 6÷16
16- ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፥ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ።

2) እኛ እንዴት መሥራት አለብን?
መልስ፡ በዚህ ዘመን ታማኝ ሰው ያስፈልጋል፡፡ ታማኝ ሰው ዘመንን ያሸንናፋል፡፡ ታማኝ ሰው ማለት ትህትና እግዚአብሔርን የሚመካው ሰው ነው፡፡
● ፍልጵ 3÷13-14
13- ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥
14- በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።

3) ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን አይነት አስተሳሰብ አለን?
መልስ፡ የእምነትን ቃል የሚይዝ ሰው ነው፡፡
● 2ጢሞ 3÷16-17
16-17 የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።

4) ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን አይነት አስተሳሰብ አለብን?
መልስ፡ አስተማሪዬ አብሮኝ ያደርገዋል።
● ገላቲ 5÷16-18
16- ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።
17- ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።
18- በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም።

5) ስለ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ምን አይነት አስተሳሰብ አለን?
መልስ፡ ሁለት ክንፎች እንዲደረግ ያስፈልጋል፡፡
● ቆላ፡ 1÷24-29
24- አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፥ ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ።
25- ስለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ።
26- ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል።
27- ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፥ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው።
28- እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው።
29- ለዚህም ነገር ደግሞ፥ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ፥ እደክማለሁ።

6) ስለ ጌታ ራዕይ ምን አይነት አስተሳሰብ አለን?
መልስ፡ የእግዚአብሔር ቃል ማለት የእኔ ራዕይ ነው፡፡
● ሐዋ. 20÷24
24- ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።

5. የጌታ ደቀ መዘሙርት ማረጋገጥ እምነት መሆን ያስፈልጋል፡፡ በሚቀጥለው ቃል አገኝ፡፡
1) አሮጌ ማንነቴ ሞቶ መነሣት ማለት ከኢየሱስ ጋር መስቀል ላይ ሞቶ መነሣት ማለት ነው፡፡
● ገላ. 2-20
20- ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።

2) በዓለም ውስጥ መኖር ጥሩ አይደለም፡፡ ዓለም ለእኔ ታላቅ ትርጉም የለም፡፡

● ገላቲ. 6÷14
14- ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።

3) የእኔ ሥጋ፤ ስሜትና ም�ኞት ጨረሰሁ፡፡

● ገላቲ፡5÷24
24- የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።

4) እኔ ወንጌል ስብከትና ሌሎችን ደቀ መዘሙርት ማድረግ ሥራ ሕይወቴን በሙሉ እሰጣለሁ፡፡

● ሐዋ፡20÷24
24- ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።

5) የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ለመድረግ ሕይወቴን ሁሉ መስጠት።

● ቆላ፡1÷24
24- አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፥ ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ።

6. የጌታ ደቀ መዘሙርት የወንጌልን ስብከት መሆን ያስፈልጋል፡፡ በምድር ላይ ግብና ዓላማን የመውሰድ ዕቅድ ምንድን ነው?

1) ሁሉም አገሮች የሚስዮናዊ ራዕይ አለባቸው፡፡

● ማር. 16÷15-18
15- እንዲህም አላቸው፡- ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።
16- ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።
17- ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥
18- የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።

2) የመንፈስ ቅዱስ ኀይልን ተቀብሎ ወደ ዓለም መሄድ ሥራ ነው፡፡

● ሉቃ 24÷48-49
48- እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ።
49- እነሆም፥ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ

3) ሁሉም አገሮች የሚስዮናዊ ተልዕኮ መኖር አለበት፡፡

● ሐዋ፡1÷-8
8- ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

4) ደቀ መዛሙርት የማድረግ ዕቅድ መኖር አለበት፡፡

● ማቴ 28÷18-20
18- ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።
19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

★ ማስተካከያ

ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተማረኸው ነገር ሕይወትህን ልታስተካክል የፈለግኸውን ከጻፍክ በኋላ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት

ጌታ የሚደሰትበት የወንጌል ስብከት እንዲሆን መፀለይ፡፡

① ጌታን የሚከተሉና ታማኝ ደቀ መዝሙርት እንዲሆኑ መፀለይ፡፡
② በእምነት ታማኝ ደቀ መዝሙርት እንዲሆኑ መፀለይ፡፡
③ ስለ ኢየሱስ ሕይወታችንን ሁሉ የሰጠን ደቀ መዝሙርት እንድንሆን ጌታ እንዲረዳን መፀለይ።



ስለ ሌሎች የሚፀለይ ስብሰባ (ትምህርት ቤት) (ዘዳ.32÷30-32)

መግቢያ

ስለ ሌሎች የፀሎት ምሳሌ፤ አብርሃም ስለ ሰዶምና ገሞራ ጥፋት የፀለየበት ምሳሌ ታሪክ አለ፡፡
ይህንን ቃል በምነበብበት ጊዜ እግዚአብሔር ዕቅዱን ይቀየር ነበር፡፡ (ዘፍ.18÷24)
….በከተማይቱ ውስጥ 50(ሃምሳ) ፃድቃን ቢገኙ በውኑ ሁሉን ታጠፋለህን? (ዘፍ 18÷26) የእግዚአብሔር መልስ፤ እግዚአብሔርም በሰዶም ከተማ ውስጥ ሃምሳ ፀድቃንን ባገኝ ስፍራውን ሁሉ ስለ እነርሱ እምራለሁ አለ፡፡
አብርሃም 40 ሰዎች ቢገኙ እግዚአብሔር ሆይ አታጠፋም? 30 ሰዎች ወይም 20 ሰዎች ወይም 10ሰዎች ካሉ አላጠፋም አለው፡፡
ስለ ሌሎች በመፀለይ የእግዚአብሔርን ልብ መያዝ፤ ስለ ሰዎች መፀለይ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡
አብርሃም በፀለየ ጊዜ እግዚአብሔር ሰምቶ መልስ ሰጥቷል፡፡ ስለ ሌሎች መፀለይ ሞዴል (ምሳሌ) ኢየሱስ ነው፡፡ ኢየሱስ ስለ ደቀ መዝሙርት በደንብ ፀልየዋል፡፡ ጴጥሮስ ኢየሱስን ከካደ በኋላ ግን ፀለየ፡፡ ስለ ሌሎች መፀለይ ማለት እኛ ስለ ሌሎች ያለን የፍቅር መገለጥ ማለት ነው፡፡

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ - ስለ ሌሎች የመፀለይ ጥሪ .....

ምዕራፍ ሁለት - በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሌሎች ፀሎት.....

ምዕራፍ ሦስት - ስለ ለሌች መፀለይና የመንፈስ ጦርነት.....

ምዕራፍ አራት - በስልጣን ስለሌሎች መፀለይ .....

ምዕራፍ አምስት - ስለሌሎች መፀለይና በዓለም ላይ ወንጌልን መስበክ.....

ምዕራፍ ስድስት - ስለሌሎች የፀሎት ልምድ፤ ስለሌሎች የፀሎት ልዩ ወታደር.....

ምዕራፍ አንድ
ስለ ሌሎች የመፀለይ ጥሪ

● ዘፀ.32÷30-32
30- በነጋውም ሙሴ ለሕዝቡ። እናንተ ታላቅ ኃጢአት ሠርታችኋል አሁንም ወደ እግዚአብሔር እወጣለሁ ምናልባት ኃጢአታችሁን አስተሰርይላችኋለሁ አላቸው።
31- ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ፡- ወዮ! እኒህ ሕዝብ ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል፥ ለራሳቸውም የወርቅ አማልክት አድርገዋል
32- አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ።

ታርክ
ጆጂ ሙሉ በህይወት በነበረበት ጊዜ 50,000 የፀሎት መልስንም የተቀበለ ሰው ነው፡፡ እግዚአብሔር በእምነት ለሚፀልዩ ሰዎች ሁሉንም መልስ ይሰጣል፡፡ ጆጂ ሙሉ፤ና ኤልያስ ደግሞ እንድ ሰዎች ናቸው፡፡ ጆጂ ሙሉ ብዙ የፀሎት መልስ የተቀበለበት ምሥጢር ምንድን ነው? ጆጂ ሙሉ ስለ ሌሎች ሰዎች የሚፀልይ ሰው ስለሆነ ነው፡፡
የጆጂ ሙሉ የፀሎት ዝርዝር ብዙ የራሱ ሳይሆን ስለ ሌሎች የፀሎት ህይወት ነበረ። ስለ ጓደኞቹ፤ ስለ ጐረቤቶቹ፤ ስለ ወላጅ አልባ ልጆችና ስለ ሌሎችም የፀሎት ህይወት ነበረ። የፀሎት ሰው ማለት ስለ ሌሎች የሚፀልይ ሰው ነው፡፡

1. ስለ ሌሎች የመፀለይ ትርጉም ምንድን ነው?
1) ብዙ የጸሎት ዝርዝር ይዞ ወደ እግዚአብሔር መፀለይ ማለት ነው፡፡
ነገር ግን ስለ ሌሎች ፀሎት ማለት የሌሎችን የፀሎት ዝርዝር ይዞ ወደ እግዚአብሔር መፀለይ ማለት ነው፡፡

2) ስለ ሌሎች ፀሎት ዋና ትርጉሙ፤
Intercession= inter(between፤መካከል) + cession(go፤ሄደ)
በፀሎት ሌሎችን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንድሆኑ ማገናኘት ማለት ነው፡፡

3) ስለ ሌሎች ፀሎት ማለት እርዳታ በሚፈልገው ሰው ፈንታ ወደ እግዚአብሔር መፀለይ ማለት ነው፡፡

4) ስለ ሌሎች መፀለይ ማለት፡- ስለ ችግረኞች በእግዚአብሔር ፊት ፀሎት (ልመና) ማቅረብ ማለት ነው፡፡
● 1ጢሞ.2÷1-2
1-2 እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።

5) ስለ ሌሎች መፀለይ ማለት እንደ ካህን ሥራ ለሁሉም ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሰጠው ተልዕኮ ነው፡፡
ስለ ሌሎች መፀለይ ማለት የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮና ህይወት ነው፡፡(ሦስት ጊዜ ጮኽ ብሎ)
የእግዚአብሔር ቃልና የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ሚዛን ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ያድጋል፡፡
ስለ ሌሎች ፀሎት ከሌላ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፤ ወንጌላዊና መጋቢ በህይወታቸው ይወድቃሉ።
● 1ጴጥ.2÷9
9- እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤

2. ስለ ሌሎች የፀሎት ዋና፤ አስፈላጊነት ምንድን ነው?
1) ስለ ሌሎች ፀሎት መጀመር ኢየሱስ ነው።
● 1ጢሞ.2÷5
5- አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤

2) ኢየሱስ ስለ ሌሎች ፀሎት የመፀለይን ትዕዛዝ ለደቀ መዛሙርት ሰጣቸው፡፡
● ዮሐ.17÷22-23

22-23 እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል።

3) ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ስለ ሌሎች እንዲ ፀልዩ ላካቸው።
የእግዚአብሔር ልዩ ሰዎች፤ ስለ ሌሎች የምፀልዩ ሰዎች ናቸው፡፡
ስለ ሌሎች ፀሎት በምፀለይበት ጊዜ እግዚአብሔር ይሠራል፡፡
● ዮሐ.17÷18-21
18- ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው፤
19- እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ።
20-21 ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ።

4) ኢየሱስ ለሚፀልዩ ሰዎች ስልጣንን ሰጥቷል፡፡
● ማቴ.16÷19
19- የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።

5) ደቀ መዝሙርት በዓለም ላይ ስለ ሌሎች በፀሎት ጠራቸው፡፡
● ማቴ.28÷19-20
19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

6) ስለ ሌሎች የፀሎት ሰው፤ በኢየሱስ ስም ለእግዚአብሔር ክብርን እንድሰጠ ነው፡፡
● ዮሐ.14÷13
13- እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ።

3. ስለ ሌሎች የመፀለይ ሰው ተግባር ምንድን ነው?
1) የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ መታዘዝ ነው፡፡
● ሉቃ.22÷42
42- ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።

2) ስለ ሌሎች በምንፀልይ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቁጣና ፍርድን ማቆም ማለት ነው፡፡
ሙሴ የእስራኤል ህዝብ ጣኦትን ባመለኩ ጊዜ እግዚአብሔር ቁጣ (ፍርድ) ከሚሆን ስሜ ከህይወት መዝገብ ደምስሰኝ አለ፡፡
● ዘፀ.32÷31-32
31- ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ፦ ወዮ! እኒህ ሕዝብ ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል፥ ለራሳቸውም የወርቅ አማልክት አድርገዋል
32- አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ።

3) የኢየሱስን ልብ ይዞ መኖር ያስፈልጋል።
● ፊል.1÷8
8- በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር ሁላችሁን እንዴት እንድናፍቃችሁ እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና።

4) የመንፈስ መከርና ስሜት ይዞ መኖር ያስፈልጋል፡፡
● ዮሐ.4÷35
35- እናንተ። ገና አራት ወር ቀርቶአል መከርም ይመጣል ትሉ የለምን? እነሆ እላችኋለሁ፥ ዓይናችሁን አንሡ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ።

5) በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መኖር ያስፈልጋል፡፡
● ዮሐ.14÷23-24
23- ኢየሱስም መለሰ አለውም። የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።
24- የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።
● ዮሐ.15÷7
7- በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።

6) በሁሉም ሀገሮች ላይ ስላሉ ስለ ሌሎች ሰዎች ፀሎት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

● ዘፍ.18÷23-24
23- አብርሃምም ቀረበ አለም። በውኑ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ታጠፋለህን?
24- አምሳ ጻድቃን በከተማይቱ ውስጥ ቢገኙ በውኑ ሁሉን ታጠፋለህን? ከተማይቱንስ በእርስዋ ስለሚገኙ አምሳ ጻድቃን አትምርምን?

7) ከብዙ ፈተና፤ ራስን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ሰይጣን ስለ ሌሎች ፀሎት ሲደረግ አይወድም፡፡
● 1ጴጥ.5÷8-9
8- በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤
9- በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።

8) በመንፈስ ደፋር መሆን ያስፈልጋል፡፡
● ዮሐ.16÷33
33- በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።

9) በኢየሱስ ስም ብቻ ስለ ሌሎች መፀለይ ያስፈልጋል፡፡
● ዮሐ.14÷14
14- ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።

10) ስለ ሌሎች ፀሎት ማለት የተቀደሰ ሥራ ማለት ነው፡፡
ስለ ሌሎች ፀሎት ማለት የህይወት ሕያው ገመድ ማለት ነው፡፡
በፀሎት ጊዜ በሙሉ ልብ፤ ሀሳብ፤ መንፈስ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡
● ሉቃ.22÷44
44- በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ።

4. የሚፀልይ ሰው ከኢየሱስ የሚቀበሉት ልዩ ስልጣን ምንድን ነው?
1) ልምምድና ስልጠና ማድረግ ስለ ሌሎች የሚፀልይ ሰው ማረጋገጥ ተልዕኮ አለ፡፡
● ዕብ.5÷4
4- እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም።

2) ክፉ መንፈስን ማውጣትና ህመምን መፈወስ ይችላል፡፡
● ያዕ.5÷16
16- እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።

3) በየቀኑ ወደ እግዚአብሔር ማየት ያስፈልጋል፡፡
● ዕብ.12÷2
1-2 እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።

4) በየቀኑ ወደ እግዚአብሔር በማየት አዲስ ስልጣን መቀበል፡፡
● ኢሳ.40÷31
31- እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ ይሮጣሉ፥ አይታክቱም ይሄዳሉ፥ አይደክሙም።

5) በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔርን መንግስት ወራሽ ይቀበላል፡፡
● 1ጴጥ.1÷4
3-5 ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል።

6) በእግዚአብሔር ክብር ውስጥ ይገባል::
● 1ጴጥ.5÷1
1- እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤

7) በየቀኑ በደስታ ውስጥ ይኖራል፡፡

- ሐዋ.2÷46-47

46- በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤
47- እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

5. እግዚአብሔር ለእኛ ብዙ አይነት የፀጋ ስጦታ ሰጥቶታል። የሰጠንን የፀጋ ስጦታ መመርመር አገኘ።

★ ስለ ሌሎች ፀሎት የፀጋ ስጦታ የመመርመር ዘዴ

1 ከቶ የለም , 2- የለም , 3- መጠነኛ , 4- ትክክለኛ , 5- በጣም ትክክለኛ

1) እኔ በየቀኑ በምፀልየው ጊዜ እደሰታለሁ?

1 2 3 4 5

2) እኔ ስፀልይ ስለ ሌሎች ሰዎች እፀልያለሁ?

1 2 3 4 5

3) ስለ ሌሎች በምፀልየው ጊዜ የፀሎት ሥራ እደሰታለሁ?

1 2 3 4 5

4) ሌሎች ሰዎች ለእኔ ስለ ችግራቸው የፀሎት (ርዕስ) ዝርዝር ይሰጣሉ?

1 2 3 4 5

5) ሰዎች ለእኔ የፀሎት ዝርዝር በሚሰጡበት ጊዜ ከቶ ሳልረሳ እፀልያለሁ?

1 2 3 4 5

6) ስለ ሌሎች በሚጸልይበት ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል በአእምሮዬ ይመጣል?

1 2 3 4 5

7) ስለ ሌሎች በምፀልይበት ጊዜ እግዚአብሔር በሕልምና በመናገር ይናገራል?

1 2 3 4 5

8) ሌሎች ሰዎች ለእኔ የፀሎት ስጦታ እንዳለኝ ይናገራሉ?

1 2 3 4 5

9) ስፀልይ በድንገት የአንድ ሰው ጉዳይ ወደ አእምሮ ይመጣል?

1 2 3 4 5

10) ስለ ሌሎች በምፀለይበት ጊዜ ብዙ መልስ ይመልሳል?

1 2 3 4 5

እኔ (ቁጥር)

ምን ያህል መጠን እንደሆነ የመረጡትን ቁጥሮች ደምሮ የራሱን የፀሎት ሕይወት ማወቅ ወይም ቁጥሮች ደምሮ የራሱን የፀሎት ህይወት ማወቅ ወይም መመርመር ይችለሉ፡፡

① 40 ቁጥር ድምር ያህል ያለው ሰው ስለ ሌሎች የመፀለይ ህይወት ማወቅ ወይም መመርመር ይችላል፡፡
② 30 ቁጥር ያህል ያለው ሰው ስለ ሌሎች መጠነኛ የፀሎት ፀጋ ያለው ሰው ነው ማለት ነው፡፡
③ ከ20 ቁጥር በታች ያለው ሰው ስለ ሌሎች የመፀለይ ፀጋ አንድኖር በደንብ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

★ ማስተካከልና ማካፈል

1. ስለ ሌሎች ሰዎች መፀለይ እንደልብህ አረጋግጠሃል?
የዚህ ፀሎት ጥቅሙ ምንድን ነው? ሀሳቡን ከፃፍክ በኋላ ተከፋፈሉ፡፡

2. ስለ ሌሎች ፀሎት ጥሪ እንዴት መታዘዝ እንዳለበት በዝርዝር ከፃፍክ በኋላ ተከፋፈሉ፡፡

★ ፀሎት

ስለ ሌሎች ፀሎት ማለት የክርስቲያኖች ተግባር፤ ልዩ ስልጣን ነው፡፡
ለእኔ የሰጠኸኝን ስለ ሌሎች የመፀለይ ተልዕኮዬን እንዲያደርግ እፀልያለሁ፡፡

ምዕራፍ ሁለት
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሌሎች ፀሎት (ዘፍ.18÷22-33)

ታሪክ

ሪዝሐዋልዝ በ1879 ዓመት በእንግሊዝ ተወለደ፡፡ ሪዝሐዋልዝ ብዙ ዓመት በአፍሪካ የሚሽነሪ ሥራ ሠርተዋል፡፡ ስለ ሌሎች የሚፀልይ ታላቅ ሰው ነበር፡፡ አንድ ቀን ሐዋልዝ የሳንባ ህመም ላለባቸው ሰው ይፀልያል፡፡ ለማኝንና ወላጅ አልባን የሚረዳ ፀሎት ነበረ፡፡ ሐዋልዝ እንደ ኢየሱስ ስለ ሌሎች የፀሎት መንገድ የተከተለ ሰው ነበር፡፡
ስለ ሌሎች ፀሎት በሚፀለይበት ጊዜ እግዚአብሔር መልስ ይሰጠው ነበር፡፡

- ያዕ.5÷11

ደግሞም እነዚያን በትዕግሥት የጸኑትን፣ “የተባረኩ ናቸው” እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንዴት እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፡፡ ጌታም በመጨረሻ ያደረገለትን መልካም ነገር አይታችኋል፤ በዚህም ጌታ መሐሪና ርኅሩኅ መሆኑን ተመልክታችኋል፡፡

እግዚአብሔር ስለ ሌሎች ፀሎት በሚፀለይበት ጊዜ በዋና (በአስፈላጊ) ጊዜ መልስ ይሰጣል፡፡ እግዚአብሔር የእኛን ፀሎት ሰምቶሎ መልስ እንሰጣለን ::

- ኤፌ.3÷20

ስለዚህ በእኛ ውስጥ በሚሠራው ኀይሉ አማካይነት ከምንለምነውና ከምናስበው በላይ እጅግ አትረፍርፎ ሊያደርግ ለሚቻለው አምላክ፣

★ ተግባርና የፀጋ ስጦታ ልዩነት ምንድን ነው?

ተግባር ማለት ለሁሉም ክርስቲያኖች የሚሰጥ ነው::
የፀጋ ስጦታ ማለት ለአንዳንድ ሰዎች የሚሰጥ ልዩ ስጦታ ነው፡፡

ምሳሌ፡- የወንጌል ስብከት ክርስቲያኖች ሁሉ የሚቀበሉት ሥጦታ አይደለም:: ነገር ግን ክርስቲያኖች ሁሉ የወንጌል ስብከትን በተግባር ማድረግ አለባቸው፡፡

★ ስለ ሌሎች የመፀለይ ፀጋ ሥጦታ የተቀበለ ሰው ፀባይ

① ፀሎት ስጀምር ብዙ ጊዜ እንድን ፀልይ ያደርጋል፡፡
② በጎይለኛ እምነት ይፀልያል፡፡
③ ስፀልይ ይደሰታል፡፡ በሚፀልዩበት ጊዜ ድካም አለ፤ ነገር ግን የፀሎት ተልዕኮውን አውቆ ይቀጥላል፡፡
④ የፀሎት መልስ ብዙ ይኖረዋል፡፡
⑤ የፀሎት ውጤት ለቤተክርስቲያን ብዙ ጥቅም ይሰጣል፡፡ የመንፈስ ፍሬ ብዙ አለ፡፡
⑥ የእግዚአብሔርን ድምፅ በትክክል ሰምቶ መለየት ይችላል፡፡ ሌሎች በልሳን ቋንቋ በምፀልዩበት ጊዜ መጥፎ ወይም ጥሩ መንፈስን በመለየት ያወቃል፡፡ ትንቢት የመናገር የፀጋ ስጦታ ይኖረዋል፡፡
⑦ ሌሎች ሰዎችን የሚወደው ብዙ የሚፀልይ ሰው ነው፡፡ ዓለምና በዓለም ያሉትን ነገሮች አይወድም፡፡ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን ሀሳብ (ሥራ) ይወዳል፡፡

1. እግዚአብሔርን የሚጠቅሙ ሰዎች ስለ ሌሎች ሰዎች የሚፀልዩ ሰዎች ናቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ሰውን በኩል አገኘ፡፡

1) አብርሃም

አብርሃም ሰዶምና ጐመራ አገር ያለውን ሰዎች ጸለየ፡፡(ዘፍ.18÷22-33)

2) ሙሴ

እስራኤላውያን በወርቅ የበሬ ጣዖት አድርገው ስያመልኩ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሲረግማቸው ሙሴ ስፀልይ እግዚአብሔር ይቅር አላቸው፡፡ ደግሞ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ ተንኮል አመጽ ባደረጉ ጊዜ ብዙ እስራኤላውያን በእባብ በመነደፍ ሞተዋል፡፡ ሙሴ እባብን ገሎ በእንጨት ላይ ከሰቀለ በኋላ እስራኤላውያን እባቡን ባዩ ጊዜ ይፈወሱ ነበር፡፡

● ዘፀአት.32÷30-32
30- በነጋውም ሙሴ ለሕዝቡ። እናንተ ታላቅ ኃጢአት ሠርታችኋል አሁንም ወደ እግዚአብሔር እወጣለሁ ምናልባት ኃጢአታችሁን አስተሰርይላችኋለሁ አላቸው።
31- ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ፡- ወዮ! እኒህ ሕዝብ ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል፥ ለራሳቸውም የወርቅ አማልክት አድርገዋል
32- አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ።

● ዘሁልቁ.21÷7-9
7- ሕዝቡም ወደ ሙሴ መጥተው። በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ ስለ ተናገርን በድለናል እባቦችን ከእኛ ያርቅልን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን አሉት።
8- ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ። እግዚአብሔርም ሙሴን፡- እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል አለው።
9- ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ።

3) ሳሙኤል

ሳሙኤል ስለ እስራኤላውያን ያለ ዕረፍት ይፀልይ ነበር፡፡

● 1ሳሙ.12÷23
23- ደግሞ መልካሙንና ቅኑን መንገድ አስተምራችኋለሁ እንጂ ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ።

4) ኤርምያስ

ኤርምያስ በእስራኤል ኃጢአት ፋንታ ንስሐ ይጸልይ ነበር፡፡

● ኤር.14÷7-9
7- አቤቱ፥ ኃጢአታችን ብዙ ነውና፥ በአንተም ላይ ኃጢአት ሠርተናልና ኃጢአታችን ይመሰክርብናል ነገር ግን ስለ ስምህ ብለህ አድርግ።
8- አንተ የእስራኤል ተስፋ ሆይ በመከራም ጊዜ የምታድነው፥ በምድር እንደ እንግዳ፥ ወደ ማደሪያ ዘወር እንደሚል መንገደኛ ስለ ምን ትሆናለህ?
9- እንዳንቀላፋ ሰው ሰው፥ ያድንም ዘንድ እንደማይችል ኃያል ስለ ምን ትሆናለህ? አንተ ግን፥ አቤቱ፥ በመካከላችን ነህ እኛም በስምህ ተጠርተናል አትተወን።

5) ሐዋሪያ ጳውሎስ

ጳውሎስ ስለ ነገሥታት፤ ስለ ማሪዎችና ስለ ሌሎች ሁሉ ይፀልይ ነበር፡፡

● 1ጢሞ.2÷1-2

1-2 እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።

6) ሐዋሪያ ዮሐንስ
ስለ ሰዎች ነፍስ ጤናማነትና እድገት ይፀልይ ነበር፡፡
ሰዎች ከሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት ስላለ ብቻ መቀየር አይችልም፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ በሰዎች ልብ ውስጥ ስገባ መቀየር ይችላል፡፡
በስብከት ጊዜ 1ኛ ክርስቲያኖች በትኩረት ቢነጋገሩ ጥሩ ነው፡፡ እምነት ሦስት ደረጃ ሲኖረው
1ኛ ደረጃ እምነት ያላቸው ሰዎች በቃሉ ወዲያው ያድጋሉ፤
2ኛና 3ኛ የእምነት ደረጃ ያላቸው ክርስቲያንኖች በውስጣቸው የሚቋቋም ጉዳዮች ስለሌላቸው ቶሎ አያድጉም፡፡
● 3ዮሐ.1÷2
2- ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።

2. አንድ ሰው በእውነት በደንብ ስለሌሎች በሚፀልይበት ጊዜ አንድ አንድ አገሮች ዕጣ ይቀየራል፡፡
በሚቀጥለው ቃል በኩል ዕድልን መቀየር ስለሌሎች ፀሎት ማካፈል፡፡
1) ነህምያ ስለ እስራኤል አያቶች ሀጢአት በንስሃ ፀልዮል፡፡
● ነህምያ.1÷6
6- እኔ ባሪያህ ዛሬ በፊትህ ስለ ባሪያዎችህ ስለ እስራኤል ልጆች ሌሊትና ቀን የምጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ ጆሮህ ያድምጥ፥ ዓይኖችህም ይከፈቱ በአንተ ላይም ያደረግነውን የእስራኤልን ልጆች ኃጢአት እናዘዝልሃለሁ እኔና የአባቴም ቤት በድለናል።

2) ዳንኤል ስለ ሌሎች በመፀለይ ዕጣን አስቀይረዋል፡፡ (ዳን 9)

3) ሙሴ ስለሌሎች በፀለየ ጊዜ የእስራኤላዊያን ዕጣ ይቀየር ነበር፡፡
● ዘፀ.32÷11-14
11- ሙሴም በእግዚአብሔር በአምላኩ ፊት ጸለየ፥ አለም። አቤቱ፥ ቍጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብፅ ምድር ባወጣኸው በሕዝብህ ላይ ስለ ምን ተቃጠለ?
12- ግብፃውያንስ። በተራራ መካከል ሊገድላቸው፥ ከምድርም ፊት ሊያጠፋቸው ለክፋት አወጣቸው ብለው ስለ ምን ይናገራሉ? ከመዓትህ ተመለስ፥ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ።
13- ዘራችሁን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ፥ ይህችንም የተናገርኋትን ምድር ሁሉ ለዘራችሁ እሰጣታለሁ፥ ለዘላለምም ይወርሱአታል ብለህ በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን እስራኤልንም አስብ።
14- እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ።

4) ኤልያስ በፀለየ ጊዜ ሦሥት ዓመት ተኩል የነበረው ድርቅ በፀለየ ጊዜ ዝናብ ዘነበ፡፡
● 1ነገ.18÷41-46
41- ኤልያስም አክዓብን፦ የዝናቡ ውሽንፍር እጅግ ነውና ተነሥተህ ውጣ፥ ብላም ጠጣም አለው።
42- አክዓብም ሊበላና ሊጠጣ ወጣ ኤልያስም ወደ ቀርሜሎስ አናት ወጣ ፊቱንም በጕልበቱ መካከል አድርጎ በግምባሩ ተደፋ።
43- ብላቴናውንም። ወጥተህ ወደ ባሕሩ ተመልከት አለው። ወጥቶም ተመልክቶም። ምንም የለም አለ። እርሱም፦ ሰባት ጊዜ ተመላለስ አለው። ብላቴናውም ሰባት ጊዜ ተመላለሰ።
44- በሰባተኛውም ጊዜ። እነሆ፥ የሰው እጅ የምታህል ታናሽ ደመና ከባሕር ወጥች አለ። እርሱም፦ ወጥተህ አክዓብን፦ ዝናብ እንዳይከለክልህ ሰረገላን ጭነህ ውረድ በለው አለ።
45- ከጥቂትም ጊዜ በኋላ ሰማዩ ከደመናውና ከነፋሱ የተነሣ ጨለመ፥ ብዙም ዝናብ ሆነ አክዓብም በሰረገላው ተቀምጦ ወደ ኢይዝራኤል ሄደ።
46- የእግዚአብሔርም እጅ በኤልያስ ላይ ነበረች ወገቡንም አሸንፍጦ ወደ ኢይዝራኤል እስኪገባ ድረስ በአክዓብ ፊት ይሮጥ ነበር።

5) ክርስቲያኖች ስለ ጴጥሮስ በፀለዩ ጊዜ መልአክትን ልኮ ከእስር ቤት አወጣው፡፡
ስለዚህ ጴጥሮስ የተሰጠውን የተልዕኮ ሥራ ጨርሶ ሠርቷል፡፡
● ሐዋ.12÷5
5- ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።

● ሐዋ.12÷12
12- ባስተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ።

3. ህዝቅኤል 22🕑30 ስለሌሎች መፀለይ ሳይሆን የእግዚአብሔር ፍርድ ይቀበላል፡፡ በኢየሱስ ስም በምያምኑ ጊዜ ክርስቲያኖች ሁሉ ስለ ሌሎች የፀሎት ተልዕኮን ተቀብለዋል፡፡
● ህዝቅኤል.22÷30

30- ቅጥርን የሚጠግንን፥ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፥ ነገር ግን አላገኘሁም።

1) ኢየሱስ በምድር ላይ ራሱ ስለሌሎች በፀሎት ህይወት ኖረ::
● ሉቃ.22÷31-32
31- ጌታም፡- ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ
32- እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ።

2) ኢየሱስ ስለሌሎች የሚፀልይ ፍጹም ሰው ነው፡፡
● 1ጢሞ.2÷5
5- አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤

3) ኢየሱስ አሁን ስለ እኛ ይፀልያል::
● ሮሜ.8÷34
34- የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

4) ስለሌሎች የሚፀልይ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍርድ እንዳይሆን ንስሃ የሚገባ ሰው ነው፡፡
● ሕዝ.22÷30
30- ቅጥርን የሚጠግንን፥ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፥ ነገር ግን አላገኘሁም።

5) ስለሌሎች መፀለይ ማለት የክርስቲያኖች ተግባር ነው፡፡
● ኤፌ.6÷18
18- በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤

4. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መገለጥ ስለሌሎች ፀሎት ዕቅድ እንዴት ነው?
1) ስለሌሎች መፀለይ ማለት ህይወት ነው፡፡
መግለጫ፡- ስለሌሎች የፀሎት ሥራ መቆም የለበትም፡፡
● 1ሳሙ.12🕑23
23- ደግሞ መልካሙንና ቅኑን መንገድ አስተምራችኋለሁ እንጂ ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ።

2 ስለሌሎች ፀሎት በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንድንሆን ነው፡፡
● የሐ.17÷20-22
20- "በእነርሱ ቃል አማካይነት በእኔስለሚያኑትም እለምናለሁ እንጂ ለእነርሱ ብቻ አለምንም፡፡
21- እኔም የምለምነው ሁሉም አንድ እንዲሆኑ ነው፣ እንዲሁም አባት ሆይ! አንተ በእኔ እንዳለህ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ፣ እነርሱም በእኛ እንዲኖሩ ነው፣ አንተ እንደ ላክኸኝም ዓለም እንዲያምን ነው፡፡
22- እኛ አንድ እንደ ሆንን እነርሱም አንድ እንዲሆኑ ለእኔ የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቻቸዋለሁ፡፡

3) ስለሌሎች መፀለይ ማለት መሥዋዕት ነው፡፡ ምክንያቱም ስለሌሎች ስለምን ፀልይ ነው፡፡
● ሮሜ.9÷1-3
1-2 ብዙ ጎዘን የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሸምም፤ ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል።
3- በሥጋ ዘመዶቼ ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና።

4) ስለሌሎች መፀለይ ማለት የሌሎችን ውርደት መሸም ማለት ነው፡፡
● ዕብ.5÷7
7- እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤

● ነህምያ.1÷6-7
6- እኔ ባሪያህ ዛሬ በፊትህ ስለ ባሪያዎችህ ስለ እስራኤል ልጆች ሌሊትና ቀን የምጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ ጆሮህ ያድምጥ፥ ዓይኖችህም ይከፈቱ በአንተ ላይም ያደረግነውን የእስራኤልን ልጆች ኃጢአት እናዘዝልሃለሁ እኔና የአባቴም ቤት በድለናል።
7- እኛም በአንተ ላይ እጅግ ክፉ ሠርተናል ለባሪያህም ለሙሴ ያዘዝኸውን ትእዛዝና ሥርዓት ሕግም አልጠበቅንም።

5) ስለሌሎች መፀለይ ማለት የእግዚአብሔርን አካል እንድን ገነባ የሚያስችል ነው::

● ሐዋ.9÷31

31- በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።

6) ስለሌሎች መፀለይ ማለት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ማለት ነው፡፡

● ሮሜ.8÷27

27- ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።

7) ስለሌሎች መፀለይ ማለት ሥራና ቅዱስ ሥራ ነው፡፡

● ሉቃ.22÷44

44- በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ።

5. በመጸሐፍ ቅዱስ ውስት መገለጥ ስለሌሎች መፀለይ ስለመለሸ አግኝ፡፡

1) ስለሌሎች በፀለዩ ጊዜ የእግዚአብሔርን ልብ ለወጠ፡፡

● ምዝ.106÷23

23- እንዳያጠፋቸው ቀኣጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ፥ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ

2) ስለሌሎች በፀለዩ ጊዜ ኃጢአትን ይቅርና ሕመምን ፈወስ፡፡

● 2ዜና.7÷14

14- በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።

3) በፀለዩ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሥራ አየ፡፡

● ኢሳ.62÷7

6-7 ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ጕበኞችን በቅጥርሽ ላይ አቁሜአለሁ ቀንና ሌሊት ከቶ ዝም አይሉም እናንተ እግዚአብሔርን የምታሳስቡ፥ ኢየሩሳሌምን እስኪያጸና በምድርም ላይ ምስጋና እስኪያደርጋት ድረስ አትረፉ ለእርሱም ዕረፍት አትስጡ።

4) በሚፀለዩ ጊዜ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ቀድመው ያውቃሉ፡፡

● ዘፍ.18÷17

17- እግዚአብሔርም አለ፡- እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን?

● አሞጽ.3÷7

7- በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም።

5) በፀለዩ ጊዜ እግዚአብሔር በብዛት የተትረፈረፈ ኖሮ ያኖራል፡፡

● ኤፌ.1÷16-19

16- ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ስጸልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም፤

17- የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።

18-19 ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤

★ ማዋልና ማካፈል

1. በመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ስለሌሎች መፀለይ ሰዎች በፀሎት በኩል አዲስ ያወቅኸውን ፅፈህ ከጓደኛህ ጋር ተከፋፈል፡፡

2. እኔ ስለሌሎች መፀለይ መልስን ፅፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት

ስለ ቤተሰብ፤ ስለ ሥራ፤ ስለ አገሬ፤ በደምብ መፀለይ ያስፈልጋል::

ምዕራፍ ሦስት
ስለ ለሌች መፀለይና የመንፈስ ጦርነት

● ኤፌ.6÷10-12
10- በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።
11- የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።
12- መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

አንድ ምስዮንያዊ ሰው ብራዚልና ኡርጋዊ የሁለት አገር ዳርቻ ያለው የመንደር ስራ ሥራ፡፡
አንድ ቀን በጣም የሚገርም ነገር አየ፡፡ እርሱም ኡርጋዊው ወንጌልን ሲሰራ ሁሉም የእርሱን የወንጌል ሥራ ወረቀት አልተቀበሉም፡፡ ሁሉም አዝነውም ነበር፡፡ ነገር ግን ዳርቻን አልፎ ሄዶ ብራዚል ቢሆን ሁሉ ሰዎች የእርሱን ወንጌል ወረቀትን በደንብ የቀበላሉ፡፡ ስለ ኢየሱስ የእርሱን ምስክርትን ሰምቶው ልባቸው ተከፈተ፡፡

አንድ ቀን ከኡርጋዊ ወንጌል ወረቀትን ሲሰጣ አጥብቆ መጣላት አንድ ሴት ይህን መንገድ አልፎ ሄዶ ብራዜል እንዲሄድ አይቶ ይህ ምስዮናዊ ሰው ደግሞ አብሮ ዳርቻን አልፎ ወንጌልን በሰበኩ ጊዜ የምስጋና ወረቀት ተቀብሎ ልቡ ተከፈተች። በጣም በመገረም ልምምድን ሚስዮናዊ ይህን ምክንያት ማወቅ ጀመረ፡፡ በመገረም በብራዚል ስለ ብራዚል ልዩ መፀለይ ቡድን እንዲኖር ነው፡፡ ስለሌሎች የሚፀለዩ ሰዎች ፀሎታቸው ይህን አገር የያዘው ክፉ መንፈስ ስልጣንን አስሮ ወንጌል የሚገባበትን መንገድን አስቀድሞ እንዲከፈት ነው፡፡ የእኛ ውጊያ ከሰዎች ጋር ሳይሆን በሰማይ ያለው ክፉ መናፍስት ውጊያ ነው፡፡

★ የመንፈስ ጦርነት ማለት ምን ማለት ነው? (1ኛ ጢሞ 1÷18, 2ኛ ጢሞ 2÷3-4, ኤፌ 6÷11-13)
የመንፈስ ጦርነት ማለት ከእግዚአብሔር መንግሥት ሰዎችን ከሚያስወጣው ከሰይጣን ስልጣን ጋር ጦርነት ነው፡፡
ኢየሱስ በመስቀል ባያሸንፍ ኖሮ ሰይጣን አስቀድሞ ያጠፋን ነበር፤ ግን በፈፁም አያጠፋም፡፡
ይህ ጦርነት ከሰዎች ጋር ሳይሆን በስውር አየር ላየ ያለው ስልጣን ከያዘው ከሰይጣን ጋር ጦርነት ነው፡፡
ስለዚህ ሁሉም የፀሎጽት ሰዎች በመንፈስ ጦርነት መቁጣ መነሳት ያስፈልጋል፡፡
ፀሎት ማለት እንደ ተወርዋሪ ነው፡፡

1. ስለሌሎች ፀሎት ማለት ከሰይጣን ጋር የመንፈስ ጦርነት ነው፡፡ አስቀድሞ ጠላቶችን ማወቅ በዝርዝር ዕቅድና በፀሎት ጦርነት ማፍረስ ይቻላል፡፡ የሰይጣን ግብና የጦር ዕቅድ ምንድን ነው?
1) የሰይጣን ግብ ምንድን ነው?
① የእግዚአብሔር ክብር እንደ ሁከት ነው፡፡ የሚያምኑ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጸጋ እንዲቋረጡ ያደርጋል::
● ገላ.3÷1
1- የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?

② ኢየሱስን የማያምኑ ሰዎችን ያታለላል:: ሰዎች ደኅንነትን እንዳትቀበል ሁከት ያደርጋል::
● 2ቆሮ.3÷4
4- በክርስቶስም በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ እምነት አለን።

③ ሰዎችን በጠላትነት እንዲነሳሱ ያደርጋል፡፡ ሰይጣን ለሰዎች መቀጣል ኃጢአትን እንዳደርግ ይፈትናል፡፡
● 1ዜና.21÷1
1- ሰይጣንም በእስራኤል ላይ ተነሣ፥ እስራኤልንም ይቈጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው።

2) የሰይጣን የጦር ዕቅድ ምንድን ነው?
① ሃይልና ፖለቲካ ይዞ እንዲቆጣጠሩ ያደርጋል፡፡
● ቆላ.2÷15
15- አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።

② በስልጣን በሀገር ውስጥ ልዩ ቦታና ልዩ ሰዎችን እንዲቆጣጠሩ ያደርጋል፡፡
Cf. የጦርነት ግብ ማለት አሸናፊ ነው፡፡
● ኤፌ.6÷12
12- መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

③ የጨለማ ዓለም መሪዎች

ውሸት በመናገር በክፉ ወንጌል በኩል ሐሰት ሃይማኖትን፤ ማሰብን፤ ፍልስፍና፤ እውቀትን፤ ባህልን ይዞ እንዲቆጣጠሩ ያደርጋል፡፡

● 2ቆሮ.4÷4

4- ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።

④ በሰማይ ያለው ክፉ መንፈሶችና አጋንንት

ትንሽ ድርጅትና በየግል ሕይወት መስራት በመንፈስ ድርጅቶች ላይ እነዚህ ክፉ መንፈሶችና አጋንንት እንደ ጦር እቅድ አላቸው፡፡

A. ማሰብ፤ - መጨነቅ፤ ፍርሃት፤ ዋጋ ቢስ፤ ምኞት፤ ውድቀትና የጥፋተኛናነትን ሃሳብ::
B. መቃወም፤ - አለመታዘዝ፤ ክፉ ልብ እንዲኖር ያደርጋል፡፡
C. አፍ፤ - ትችትና ብልሽት ያደርጋል፡፡
D. ግንኙነት፤ - መጥላት፤ ምቀኝነትና ቅናተኛ ያደርጋል።

● 1ጢሞ.4÷1

1-2 መንፈስ ግን በግልጥ። በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፤ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው፥

● ኤፌ.6÷12

12- መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

⑤ ሴራ

በማታለልና በብልሃት ያደርጋል፡፡

● ቆላ.2÷8

8- እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ።

2. የሰይጣን የአደጋ ዘዴ ምንድን ነው?

1) ድካማችንን አይቶ አደጋ ለማድረስ ይፈትናል፡፡

● 1ዜና.21÷1

1- ሰይጣንም በእስራኤል ላይ ተነሣ፥ እስራኤልንም ይቈጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው።

2) የውሸት ወንጌልና እንክርዳዱን ይተክላል፡፡

● ማቴ.13÷38-39

38- መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤

39- እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፥ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፤ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፥ አጫጆችም መላእክት ናቸው።

3) በብዙ አይነት በሽታ በመታመም እንድንሰቃይ ያደርጋል፡፡

● ኢዮ.2÷7

7- ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፥ ኢዮብንም ከእግሩ ጫማ ጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቍስል መታው።

4) የሚያምኑ ሰዎችን በመለያየት፤ እርስ በርሳቸው ውሸታሞች እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

● ራእይ.12÷10

10- ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፦ አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና።

5) ሰውነታችን እንዲበላሽ ያደርጋል፡፡

● ማር.5÷2-5

2- ከታንኳይቱም በወጣ ጊዜ፥ ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው ከመቃብር ወጥቶ ወዲያው ተገናኘው፤

3- እርሱም በመቃብር ይኖር ነበር፥ በሰንሰለትም ስንኳ ማንም ሊያስረው በዚያን ጊዜ አይችልም ነበር፤

4- ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበርና ዳሩ ግን ሰንሰለቱን ይበጣጥስ እግር ብረቱንም ይሰባብር ነበር፥ ሊያሸንፈውም የሚችል አልነበረም፤

5- ሁልጊዜም ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበር።

3. በመንፈስ ጦርነት ስለሌሎች የፀሎት ሰው ማወቅ የሚገባቸው አስፈላጊ ሁኔታዎች ምንድን ነው?

1) በጣም በዝርዝር በእርግጥ ጦርነት ነው።

● 2ቆሮ.10÷4

4- የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤

2) ጌታ እኛን ወታደር ብሎ ጠራ።

● 2ጢሞ.2÷3-4

3- እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል።

4- የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም።

3) የእኛ ውጊያ በዓይኖቻችን ከምናያቸው ከስጋ ወይም ከደም ውግያ ጋር አይደለም፡፡
ከክፉ መናፍስቶችና ከኃጢአት ጦርነት ጋር ነው፡፡

● ኤፌ.6÷12

12- መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

4) ሰይጣን ቢቃወሙት ይሸሻል። ስለዚህ ሰይጣን የሚፈራው መልአክ አይደለም።

● ያዕቆ.4÷7

7- እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤

5) አጋንንትን ማስወታት ያስፈልጋል::

● ማር.16÷17

17- ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥

6) ሁሉን ስልጣንን የመቆጣጠር ኃላፊነትና ስልጣን ለእኛ ሰጠ::

● ማቴ.10÷1

1- አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፥ እንዲያወጡአቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው።

● ሉቃ.10÷19

19 እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።

7) በመንፈስ ጦርነት ማሸነፍ ኃይል መሣሪያን ለእኛ ሰጠ:: (ኤፌ.6÷10-20)

● 2ቆሮ.10÷4

4- የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤

4. በመንፈስ ጦርነት የማሸነፍ ዝርዝር ዘዴ ምንድን ነው?

1) የኢየሱስ ክርስቶስ የደምን ስልጣን ይመካል፡፡

● ራእይ.12÷11

11- እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።

● ዘፀ.12÷23

23- እግዚአብሔር ግብፃውያንን ይመታ ዘንድ ያልፋልና ደሙንም በጉበኑና በሁለቱ መቃኖች ላይ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በደጁ ላይ ያልፋል፥ አጥፊውም ይመታችሁ ዘንድ ወደ ቤታችሁ እንዲገባ አይተውም።

2) እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሰይጣንን እንጥላለን።

● ያዕ.4÷7-8

7- እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤

8- ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ።

★ እግዚአብሔርን በመታዘዝ የሰይጣን ስራ የማፍረስ ሶስት አይነት ዘዴ አለ።

① በእግዚአብሔር ፊት በትህት ለሰይጣን ኃይል የእግዚአብሔር ቃል ይነገራል።(1ኛ ጴጥሮስ.5÷6-7)

② በእግዚአብሔር ቃል ይኖራል፡፡ (ኤፌ.6÷17)

③ የእምነት ቤተሰብን አጥብቆ ይገነባል፡፡ (1ኛ ጴጥሮ.3÷7)

3) የመንፈስ መምጣትና ስልጣንን ይለምናል፡፡

● ሉቃ.4÷18-19

17-19 የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፥ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ። የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ።

● ኤፌ.5🕑18

18- መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤

● ማቴ.12÷28

28- እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።

4) እግዚአብሔርን እንድናመሰግን ያደርጋል::

● መዝ.22÷3

3- በእስራኤል የተመሰገንህ አንተ ግን በቅድስና ትኖራለህ።

● 2ዜና.20÷21-23

21- ከሕዝቡም ጋር ተማክሮ በሠራዊቱ ፊት የሚሄዱትን፡- ምሕረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ የሚሉትንም፥ ጌጠኛ ልብስም ለብሰው የሚያመሰግኑትን፥ ለእግዚአብሔርም የሚዘምሩትን መዘምራን አቆመ።

22- ዝማሬውንና ምስጋናውንም በጀመሩ ጊዜ ይሁዳን ሊወጉ በመጡት በአሞንና በሞዓብ ልጆች በሴይርም ተራራ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ድብቅ ጦርን አመጣባቸው እነርሱም ተመቱ።

23- የአሞንና የሞዓብ ልጆችም በሴይር ተራራ በሚኖሩት ላይ ፈጽመው ይገድሉአቸው ዘንድ ያጠፉአቸውም ዘንድ ተነሥተውባቸው ነበር በሴይርም የሚኖሩትን ካጠፉ በኋላ እያንዳንዱ ባልንጀራውን ለማጥፋት ተረዳዳ።

5) በመንፈስ ይፀለያል::

● ኤፌ.6÷18

18- በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤

● ሮሜ.8÷26

26- እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤

6) በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስልጣንና ኃይል ይሰበካል፡፡

● ሉቃ.10÷17

17- ኢየሱስም መልሶ፡- አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ?

● ማር.16÷17

17- ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥

● ፊልጵ.2÷9-10

9- በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤

10- ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥

★ በመንፈስ ጦርነት አስር ትዕዛዛት፡፡

① እኔ የኢየሱስ ክርስቶስ ወታደር ነኝ:: (2ኛ ጢሞ.2÷3-4)

② በመዝሙርና በአምልኮ የእግዚአብሐየርን መምጣት እንድንለማመድ ያስፈልጋል፡፡(2ዜና.20÷20-23)

③ በቃል ውስጥ የእግዚአብሔርን ድምጽ እንድሰማ ያስፈልጋል፡፡(መዝ. 95÷7)

④ ስለሌሎች ኃጢአት ፈንታ አንተ ንስሃ እንድትገባ ያስፈልጋል፡፡ (ኢሳ.53÷12)

⑤ በመልካም ሥራ ክፉን እንዳሸንፍ ያደርጋል፡፡(ሮሜ.12÷21)

⑥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡ (ሮሜ.12÷2)

⑦ የእግዚአብሔር የጦር መሳሪያ እንድንለብስ ያደርጋል፡፡ (ኤፌ.6÷10-20)

⑧ የሰይጣንን ጠንካራ ግንብ እንዳፍርስ ያደርጋል፡፡(2ኛ ቆሮ.10÷5)

⑨ ታምራትና ምልክትን እንድሰጠ እንጸልያለን። (ማር.16÷17-20)

⑩ ለእግዚአብሔር በቅድስና እንድንታዘዝ ያደርጋል::(ያዕቆ.4÷7-8)

በመተባበር፤ በቡድን እንድንሰራ ያደርጋል፡፡

5. ስለሌሎች በፀሎት አብሮ ስፀለይ የምናሸንፍበት አጭር መንገድ ነው፡፡

1) ምሳሌ - ሙሴ፤ አሮን፤ ሑር አብረው በሚጸልዩ ጊዜ ማሸነፍ አመጣ፡፡

● ዘፀ.17÷8-13

8- አማሌቅም መጥቶ ከእስራኤል ጋር በራፊድም ተዋጋ።
9- ሙሴም ኢያሱን፡- ጕልማሶችን ምረጥልን፥ ወጥተህም ከአማሌቅ ጋር ተዋጋ እኔ ነገ የእግዚአብሔርን በትር በእጄ ይዤ በኮረብታው ራስ ላይ እቆማለሁ አለው።
10- ኢያሱም ሙሴ እንዳለው አደረገ፥ ከአማሌቅም ጋር ተዋጋ ሙሴና አሮንም ሑርም ወደ ኮረብታው ራስ ወጡ።
11- እንዲህም ሆነ ሙሴ እጁን ባነሣ ጊዜ እስራኤል ድል ያደርግ ነበር እጁንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር።
12- የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር ድንጋይም ወሰዱ፥ በበታቹም አኖሩ፥ እርሱም ተቀመጠበት አሮንና ሑርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር ፀሐይም እስክትገባ ድረስ እጆቹ ጠነከሩ።
13- ኢያሱም አማሌቅንና ሕዝቡን በሰይፍ ስለት አሸነፈ።

● መክብብ.4÷12

12- አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።

2) እርስ በርሳቸው አንድ ላይ ስፀልዩ ተላቅ ታምራት ይሥራል፡፡

● ያዕ.5÷16

16- እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።

● ሐዋ.12÷5

5- ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።

3) በመንፈስ መተባበር የፀሎት ውጤት በእጥፍ ያድጋል፡፡

● መክብብ.4÷9

9- ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል።

4) በፀሎት ስምምነት የፀሎት ምላሽ አስቀድሞ ሁኔታ ነው፡፡ ስለዚህ አብሮ መስማማትና ይቅር መባባል ያስፈልጋል፡፡ አብሮ ካልጸዩ የመንፈስ ተሃድሶ የለም::

● ማቴ.5÷23-24

23- እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥
24- በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።

● ቆላ.3÷13-14

13- እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ። ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ።
14- በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጹሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት።

5) ክርስቲያኖች ደግሞ አብሮው በሚጸልዩ ጊዜ አጥብቀው የእግዚአብሔርን ቃል ይሰብካሉ፡፡
ስለሌሎች ፀሎት ማለት በመንፈስ መዘመር ነው፡፡ አብሮ ካልጸዩ ተሃድሶ ይከብዳል፤ ደግሞ በመንፈስ ጦርነት ማሸነፍ ከባድ ነው፡፡

● ሐዋ.4÷31

31- ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

★ ማዋልና ማካፈል

1. ስለሌሎች ፀሎት በመንፈስ ጦርነት እንዲያውቁ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ከፃፉችሁ በኋላ እርስ በርሳችሁ ተካፈሉ።

2. ስለሌሎች ፀሎት ስለ ማሸነፍ እኔ እንደማዋል ምንድን ነው፤ በዝርዝር ከፃፉችሁ በኋላ እርስ በርሳችሁ ተካፈሉ፡፡

★ ፀሎት

በየቀኑ ማሸነፍ ስለሌሎች የፀሎት ህይወት እንደሆነ በደንብ እንጸልይ::

ምዕራፍ አራት
በስልጣን ስለሌሎች መፀለይ(ሐዋ.12÷1-12)

ስለሌሎች የፀሎት ሰው ቤተ ክርስቲያንን የሚጠብቅ ሰው ነው፡፡

1. ስለሌሎች የፀሎት ጌታ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስን መመካት ሲፀለይ እኛ ታላቅ የፀሎትን ስልጣን መቀበል ይሆናል፡፡

1) መንፈስ ቅዱስ መጸለይ ሊያደርጉ ሰዎችን ማሰብ ይሰጣል::

● ዮሐ.14÷26

26- አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።

2) እኛ የጸሎት ዝርዝር አናውቅም ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ስለ እኛ ራሱ ይለምናል::

● ሮሜ.8÷26

26- እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤

3) በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍላጎት እንድንጸልይ ያደርጋል፡፡

● 1ኛ ቆሮ.2÷10

10- መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።

4) መንፈስ ቅዱስ ለእኛ አጥብቆ እምነት ሰጥቶ ዓለምን እንድናሸንፍ ያደርጋል፡፡

● ዮሐ.16÷33

33- በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።

2.በ መንፈስ ቅዱስ መርዳት ምላሽ መቀበል የፀሎት ፀባይ ምንድን ነው?

1) በእግዚአብሔር ፈቃድ አንድ ልብ ይሆናል፡፡

● 1ኛ ዮሐ.5÷14-15

14- በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል።

15- የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።

2) በኢየሱስ በኩል እግዚአብሔርን እንድናከበር ያደርጋል፡፡

● ዮሐ.14÷13

13- እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ።

3) የእግዚአብሔር ማጠንከር በዘዴና በቃል መሰረታዊ ነው፡፡

● ዮሐ.15÷7

7- በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።

4) በንፁህ ልብ ይገለፃል፡፡

● ያዕቆ.5÷16

16- እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።

5) የተትረፈረፈ እምነት በጽኑ እምነት መካከል ይገለፃል፡፡

● ያዕ.1÷6

6- ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና።

6) በኢየሱስ ስም ይለምናል::

● ዮሐ.14÷14

14- ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።

3. በስልጣን ስለሌሎች የሚፀልዩ ሰዎች ራሳቸውን መግዛት ያስፈልጋል::

1) ራሳቸውን መግዛት አስፈላጊ ነው፡፡ እኔ አስቀድሜ በምኖር ጊዜ ስለሌሎች ሰዎች መኖር ይቻላል፡፡

ስለሌሎች የሚጸልዩ ሰዎች እንደ ዳንኤል በፀሎት በኩል የእግዚአብሔርን የውስጥ መንፈስ ምሥጢርን ይካፈላል።

ስለሌሎች የሚፀልይ ሰው ሁልጊዜ ለራሱ በመቀደስ ኖሮ በእውቀት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

● ዳንኤ.9÷20-23

20- እኔም ገና ስናገር ስጸልይ፥ በኃጢአቴና በሕዝቤም በእስራኤል ኃጢአት ስናዘዝ፥ በአምላኬም በእግዚአብሔር ፊት ስለ ተቀደሰው ስለ አምላኬ ተራራ ስለምን፥

21- ገናም በጸሎት ስናገር አስቀድሜ በራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ በማታም መሥዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ።

22- አስተማረኝም፥ ተናገረኝምእንዲህም አለ፡- ዳንኤል ሆይ፥ ጥበብንና ማስተዋልን እሰጥህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ።

23- አንተ እጅግ የተወደድህ ነህና በልመናህ መጀመሪያ ላይ ትእዛዝ ወጥቶአል፥ እኔም እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ አሁንም ነገሩን መርምር፥ ራእዩንም አስተውል።

2) ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ህብረት እንዲቋርጥ የሚያደርግ ታላቅ ዕንቅፋት ነው፡፡

የክፉን ስልጣን መርመሮ በጠላትነት መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ ከአገልግሎታችን አስቀድመን ራሳችን ንጽሕ መሆን ያስፈልጋል፡፡

● ኢሳ.59÷1-2

1- እነሆ፥ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፥ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም

2- ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።

3) ክፉ ልብን መፈወስ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ የፀሎት ሰዎች የራሱ ውጊያ በህመም ምክንያት ሰዎችን መሳሳት በመንገድ መምራት ያደርጋል፡፡ ክፉ ልብን መፈወስ ያስፈልጋል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በትክክል መጸለይ ይቻላል::

ክፉ ልብ ያለው ሰው የራሱ ልብ እንዲፈውስ መጸለይ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ልባችን ንጹህ መሆን ያስፈልጋል፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ድምጽን ሰምቶ መጸለይ ይቻላል::

ዕብ.12÷15

15- የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፥ ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ፥ ሴሰኛም የሚሆን እንዳይገኝ፥

4) ስለሌሎች እንድንፀልይ የሚያነሳሳ ምክንያት ፍቅር ነው::

● ፊል.2÷2-4

2- በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤

3- ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤

4- እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።

★ ስለ ሌሎች የፀሎት ሰው የራሱ የእድገት ዘዴ

① በኢየሱስ ደም እንድንታጠብ መፀለይ፡፡
ከፀሎት በፊት በኢየሱስ ደም ነፍስንና ስጋን መታጠብ፡፡

② በየቀኑ የፀሎት ሕይወታችን ያድጋል:: የጸሎት ሰዓት በሚያልፍበት ጊዜ በመንፈስ ደካማ እንሆናለን፡፡

③ የፀሎት ሰዓታችንን እንድ ጨምር ያደርጋል፡፡

④ በጉልበታችን ወድቀን እንዲፀልይ ያደርጋል፡፡
በመንፈስ ቅዱስ አስር እጥፍ እንድናድግ ያደርጋል፡፡
⑤ ታላቅ ግብ መያዝ ጥሩ አይደልም፡፡ ትንሽ ትንሽ የፀሎት ሰዓት መጨመር ጥሩ ነው፡፡

4. በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ መግለጫ በስልጣን ፀሎት የሚበላሽበት ቅርጽ ምንድን ነው?

1) በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለውን መቀያየም ሙሴ ሲፀልይ የእግዚአብሔርን ልብ ተለወጠ፡፡

● መዝሙር.106÷23

2) ስጸልይ የእኔ ህዝብን ኃጢአት ይቅር ይላል ህመምማቸውንም ይፈውሳል፡፡

● 2ዜና.7÷14

14- በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።

3) ስንጸልይ የእግዚአብሔርን ስራ እንድን ለማመድ ያደርጋል፡፡

● ኢሳ.62÷7

6-7 ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ጕበኞችን በቅጥርሽ ላይ አቁሜአለሁ ቀንና ሌሊት ከቶ ዝም አይሉም እናንተ እግዚአብሔርን የምታሳስቡ፥ ኢየሩሳሌምን እስኪያጸና በምድርም ላይ ምስጋና እስኪያደርጋት ድረስ አትረፉ ለእርሱም ዕረፍት አትስጡ።

4) ስንጸልይ እግዚአብሔር ግብንና ዕቅድ አስቀድሞ ያውቃል።

● ዘፍ.18÷17

17- እግዚአብሔርም አለ፦ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን?

5) ስንጸልይ የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትንና የተትረፈረፈ ኑሮን ይኖራል::

● ኤፌ.1÷17-19

17- የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።
18-19 ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤

5. ስለ ህመምተኞች ስንጸልይ የእግዚአብሔርን ስልጣን በፅኑ እምነት ልንለማመድ ያስፈልጋል፡፡

1) ስለ ህመማችን የፀለይንበት መልስ ተስፋ አለን፡፡

① እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ ነው፤ በራሱ ይገለጣል፡፡
② ኢየሱስ ደግሞ በስራ ጊዜ 67% በላይ ህመምተኞችን ፈወሰ፡፡
③ ስለ ህመምተኞች ጸሎት ክርስቲያኖች የሚያድጉት ተግባር ነው፡፡
④ ኢየሱስ የመንፈስ ማዳንና የስጋ ፈወስን አብሮ ማድረግ ተስፋን ይሰጣል፡፡

● ዘፀ.15÷26

26- እርሱም፦ አንተ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቀህ ብትሰማ፥ በፊቱም የሚበጀውን ብታደርግ፥ ትእዛዙንም ብታደምጥ፥ ሥርዓቱንም ሁሉ ብትጠብቅ፥ በግብፃውያን ላይ ያመጣሁትን በሽታ አላደርስብህም እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና አለ።

● ማር.16÷15-18

15- እንዲህም አላቸው፦ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።
16- ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።
17- ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥
18- የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።

● 1ኛ ጴጥ.2÷24

24- ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ *ፍ1*

2) ስለሌሎች በፀሎት በኩል መፈወስ ምሳሌ

① 100 ወታደሮች መሪ ስለ አገልጋይ በሚፀልዩበት ጊዜ ፈወስ::

● ማቴ.8÷🕑5-13

5- ወደ ቅፍርናሆምም በገባ ጊዜ የመቶ አለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥
6- ብላቴናዬ ሽባ ሆኖ እጅግ እየተሣቀየ በቤት ተኝቶአል ብሎ ለመነው።
7- ኢየሱስም፦ እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ አለው።

8- የመቶ አለቃውም መልሶ፡- ጌታ ሆይ፥ በቤቴ ጣራ ከታች ልትገባ አይገባኝም፤ ነገር ግን ቃል ብቻ ተናገር፥ ብላቴናዬም ይፈወሳል።
9- እኔ ደግሞ ለሌሎች ተገዥ ነኝና፥ ከእኔም በታች ጭፍራ አለኝ፤ አንዱንም። ሂድ ብለው ይሄዳል፥ ሌላውንም። ና ብለው ይመጣል፥ ባሪያዬንም። ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል አለው።
10- ኢየሱስም ሰምቶ ተደነቀና ለተከተሉት እንዲህ አለ፡- እውነት እላችኋለሁ፥ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም።
11- እላችኋለሁም፥ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ፤
12- የመንግሥት ልጆች ግን በውጭ ወደ አለው ጨለማ ይጣላሉ፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።
13- ኢየሱስም ለመቶ አለቃ። ሂድና እንዳመንህ ይሁንልህ አለው። ብላቴናውም በዚያች ሰዓት ተፈወሰ

② <u>የሲሮፊኒቃዊት ሴት ስለ ልጅዋ በምትጸልይበት ጊዜ ተፈወሰች::(ማር.7÷24-30)</u>
③ <u>የንጉሥ አገልጋዩ ስለ ወንድ ልጁ በጸለየ ጊዜ ተፈወሰ::(ዮሐ.4÷46-53)</u>

<u>3) ስለ ህመማችን የፀሎት ዘዴ(ማቴ.8÷5-13)</u>
① <u>በእግዚአብሔር ፊት የህመማችንን ሁኔታና ስም ይዘን በመፀለይ እንለምናለን፡፡(ማቴ.15÷22)</u>
② <u>የህመም ሁኔታና ስም በእግዚአብሔር ፊት ይፀለያል::(ማቴ.8÷6)</u>
③ <u>ጌታ ኢየሱስ ህመማችንን እንዲሰራ ይፀለያል::(ማቴ.8÷8)</u>
<u>ስለ ህመም በዝርዝረ በመታዘዝ ይፀለያል::(ሐዋ.16÷18)</u>
<u>ምሳሌ:- በአበራሽ ውስጥ ያለው የሆድ ህመምና ማንኛውም በሽታ ሁሉ በኢየሱስ ስም አዘዛለሁ ውጣ።</u>
④ <u>የጌታ ኢየሱስ መፈወስ እናመሰግንሃለን ክብር አንሰጣለን፡፡</u>

<u>★ ማዋልና ማካፍል</u>
<u>1. በስልጣን ስለ ሌሎች መጸለይ በእኔ ውስጥ መፍትሄ ችግር ምንድን ነው?</u>
<u>ከፃፋችሁ በኋላ እርስ በርሳችሁ ተካፈሉ፡፡</u>
<u>የፀሎት ዝርዝር ከፃፋችሁ በኋላ በየቀኑ በሰዓት አንድ ላይ ይጸለያል፡፡</u>

<u>2. ስለህመማችን ፀሎት ማድረግ ምክንያትና በዝርዝር የማድረግ ዘዴ ከጻፍክ በኋላ እርስ በርሳችሁ ተካፈሉ፡፡</u>

<u>እግዚአብሔር ፈዋሽና ፍቅር ነው። እኔ ስጸልይ እግዚአብሔር ሰምቶ መልስ ይሰጣል፡፡ የእኔ ርእሶች ዝርዝር ከጻፍኩ በኋላ መቀጠል መጸለይ ያስፈልጋል፡፡ እስከ መፈወስ ድረስ ይጸልያል፡፡ እስከ መቀበል ድረስ ይጸልያል፡፡</u>

<u>★ ፀሎት</u>
<u>በመንፈስ ቅዱስ እንዲመራ የመንፈስ ቅዱስ በስልጣን እንድንጸልይ በደንብ ይፀለያል፡፡</u>
① <u>እግዚአብሔር ለእኔ መንፈስ ቅዱስን በብዛት እንዲሰጥ እጸልያለሁ::</u>
② <u>ለእኔ ንጽሕ ልብን እንዲሰጥ እጸልያለሁ::</u>
③ <u>እግዚአብሔር የመንፈስ ሀይልን እንዲሰጥ እጸልያለሁ::</u>
④ <u>እኔ ህመምተኞችን የሚፈወሰበትን ስልጣን እንድሰጠ እጸልያለሁ:: አጋንንትንም የማወጣበትን ስልጣን እንድሰጠ እጸልያለሁ::</u>

<u>ምዕራፍ አምስት</u>
<u>ስለሌሎች መፀለይና በዓለም ላይ ወንጌልን መስበክ (ሐዋ. 2÷41-47)</u>

<u>ታሪክ</u>

ጋቴማላ አገር ያለው አልሞሮም ከተማ አለ። አልሞሮም ትርጉም ማለት የሙት አምላክ ይባላል፡፡ በከተማው ውስጥ የአልኮል ሱሰኞች፤ ብዙ የጣኦትን አምላክዎች ያለ ከተማ ነበር። ነገር ግን አሁን የቤተክርስቲያን ከተማ ይባላል፡፡
በከተማው ኢየሱስን የሚያምኑ ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡ ወንበዴዎች ሁሉም ተለውጠው መጋቢ ሆኑ፡፡
ከ36 መጠጥ ቤቶች መካከል 33 ቤቶች ተዘጋ፡፡ ወንጀልና አመጽም ቀነሰ። ከዚህ ለውጥ በስተኋላ አልሞሮም ከተማ ያለው አረማኖ መጋቢ ስለሌሎች ስለጸለየ ነው፡፡ አረማሮ ስለ ራሱ አገር ከ7 ሳምንት 3 ወይም 4 ቀን በጾም ይጸልያል፡፡ አሁንም በመቀጠል ይጸልያል፡፡ ይህ የጾም ጸሎት በስልጣን ለቤተ ክርስቲያን ተሀድሶ ይሆናል፡፡

ብዙ ህመምተኞች ይፈወሳሉ። ብዙ አዳዲስ ሰዎች ከንስሐ በኋላ ወደ ጌታ መጡ። አረማኖ መጋቢና ክርስቲያኖች ስለ ከተማው አብረው መጸለይ ጀመሩ፡፡ በጸሎት ስልጣን የዚህ ምድር መሬትቶች ወደ ጥሩ መሬት ተለወጠ፡፡
ደግሞ አትክልት በምርት ጊዜ 1,000 እጥፍ አደገ፡፡ ስለዚህ የለውጥ ምንጭ የአሜሪካ የእርሻ ፕሮፔሰሮች ጎብኝተው ልዩ ምንጭ መረመሩ ግን አላገኙም፤ አንድ ሰው ስለሌሎች በጸለየ ጊዜ ከተማው ሁሉ ተለወጠ፡፡

ስለሌሎች የሚፀልዩ መጋቢ፤ ወንጌላዊና መሪዎች ቢኖሩ ቤተክርስቲያን ይኖራል፡፡

1. አዳዲስ ሰዎች እንደገና ሌሎች ሰዎች ቤተክርስቲያን እንዲሰፋ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የሚሰፋው የእግዚአብሔር ፍቃድ ስለ ሆነ ነው፡፡ ስለሌሎች የሚፀልዩ ሰዎች ኢየሱስን ለማያምኑ ሰዎች በፀሎትና ወንጌልን ስብከት ያስፈልጋል፡፡
1) ሰዎችን ወደ እግዚአብሔርና ቤተ ክርስቲያን ማምጣት ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር እንዲጀምሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
● ሐዋ.2÷41-42
41- ቃሉን የተቀበሉትም ተጠመቁ፣ በዚያ ቀን ሶስት ሺህ ያህል ሰዎች በቀኑጥራቸው ላይ ተጨመሩ፡፡
42- እነርሱም በሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት፣ እንጀራውንም በቀኑረስና በጸሎት ይተጉ ነበር፡፡

2) ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያን ማምጣትና ስለ ተሃድሶ ጸሎት በደንብ መፀለይ ያስፈልጋል።
● ነህምያ.1÷4-5
4- ይህንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፥ አያሌ ቀንም አዝን ነበር በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር፥
5- እንዲህም አልሁ። አቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ፥ ለሚወድዱህና ትእዛዝህን ለሚያደርጉ ቃል ኪዳንንና ምሕረትን የምትጠብቅ፥ ታላቅና የተፈራህ አምላክ ሆይ፥

3) ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ማምጣትና ስለ ተሃድሶ መፀለይ አዲስ ህይወት ስለ ተወለደ ሥቃይ መቀበል ማለት ነው::
● 1ኛ ተሰሎ.2÷8-9
8- እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በነ ፈቃዳችን ነበረ፥ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና።
9- ወንድሞች ሆይ፥ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን፥ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን።

4) እግዚአብሔር የሚያደርገውን ተሃድሶ ማመን ያስደስታል፡፡
● ኢዩኤል.2÷23
23- እናንተ የጽዮን ልጆች፥ አምላካችሁ እግዚአብሔር የፊተኛውን ዝናብ በጽድቅ ሰጥቶአችኋልና፥ እንደ ቀድሞውም የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ አዝንቦላችኋልና በእርሱ ደስ ይበላችሁ፥ ለእርሱም እልል በሉ።

● ነህም.8÷10-12
10- እርሱም፡- ሂዱ፥ የሰባውንም ብሉ፥ ጣፋጩንም ጠጡ፥ ለእነዚያም ላልተዘጋጀላቸው እድል ፈንታቸውን ስደዱ ዛሬ ለጌታችን የተቀደሰ ቀን ነው የእግዚአብሔርም ደስታ ኃይላችሁ ነውና አትዘኑ አላቸው።
11- ሌዋውያንም። ቀኑ የተቀደሰ ነውና ዝም በሉ፥ አትዘኑም ብለው ሕዝቡን ሁሉ ጸጥ ያደርጉ ነበር።
12- ሕዝቡም ሁሉ የተነገረላቸውን ቃል አስተውለዋልና ሊበሉና ሊጠጡ እድል ፈንታም ሊሰድዱ ደስታም ሊያደርጉ ሄዱ።

2. በክፍል ቡድን ከቤተክርስቲያን ጋር ስለ ማያምኑ ሰዎች በየቀኑ መጸለይ ያስፈልጋል፡፡ የክፍል ቡድን እንዲያድግ የተኃድሶ ልምምድ ያስፈልጋል፡፡
1) ስለሌሎች ሲፀለይ በየቀኑ ኢየሱስን የምያምኑ ሰዎች ይጨመራሉ::(ሐዋ.2🕑41-47)

2) ስለሌሎች ሲፀለይ መንፈስ ቅዱስ እንዲበዛ አጥብቆ የእግዚአብሔር ቃል በደንብ ይሰበካል፡፡
● ሐዋ.4÷31
31- ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

3) ስለሌሎች ሲፀለይ ጴጥሮስ ከወህኒ ቤት በታምራት ነጻ ሆነ::

● ሐዋ.12÷5

5- ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።

4) ስለሌሎች ሲፀለይ የእግዚአብሔር መምጣትና ሥልጣን ይገለጻል፡፡

● ሐዋ.3÷6-10

6- ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።

7- በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና፥

8- ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፥ ይመላለስም ጀመር፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ።

9- ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲመላለስ አዩት፤

10- መልካምም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ስለ ምጽዋት ተቀምጦ የነበረው እርሱ እንደ ሆነ አወቁት፤ በእርሱም ከሆነው የተነሣ መደነቅና መገረም ሞላባቸው።

5) ስለሌሎች ስንፀለይ ከለመነው ይልቅ አብዝቶ ይሰጣል።

● ኤፌ.3÷20

20- እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥

3. ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ድርጅት ማደግ መጋቢ፤ ወንገላዊ፤ መሪ፤ ከክርስቲያኖች ጋር አብሮ መጸለይ ያስፈልጋል፡፡
መጋቢ፤ ወንጌላዊና መሪ ስለ ክርስቲያኖች መጸለይ ያስፈልጋል፡፡ ደግሞ ክርስቲያኖች ስለ መጋቢ፤ ወንጌላዊና መሪ እንዲጸልዩ ያስፈልጋል፡፡

ምሳሌ ታሪክ - በአሜሪካን አገር ሴፔራንሲስኮ ከተማ አለ፡፡ በዚህ ከተማ ውስት የሰይጣን ቤተ ክርስቲያን አለ፡፡ የሰይጣን ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ሶስት መቶ ሀምሳ ሺህ ሰዎች አሉ፡፡ ሰይጣንን የሚያመልኩ ሰዎች በየቀኑ አርባ ደቂቃ ወደ ሰይጣን ይጸልያሉ:: ክርስቲያን ሰዎችንና ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ይለምናሉ፡፡ እኛ ደግሞ ለክፉ መንፈስና ለሰይጣን ለአጋንንት እንዲወጣ መናገር ያስፈልጋል፡፡

1) ስለ መጋቢ፤ ወንጌላዊና መሪ መጸለይ መፈለግ ምንድን ነው?

① በቤተ ክርስቲያን ስለ አገልግሎት ብዙ ተልዕኮና ስራ ስለሰጠ ነው፡፡
② የሰይጣን ሥራ አስቀድሞ መጋቢ፤ ወንጌላዊና መሪን ማጥቃት ነው፡፡
③ መጋቢ፤ ወንጌላዊና መሪ ክርስቲያኖችን እንዳደግ ስላደርግ ነው፡፡
ሰይጣን መጋቢን፤ ወንጌላዊንና መሪን ያጥቃታል።

2) ስለ መጋቢ፤ ወንጌላዊና መሪ መጸለይ በዝርዝር መውጫ ምንድን ነው?

① ከሰይጣን ፈተናና ማታለል እንዲጠበቁ ይፀለያል፡፡ ከስጋ ህመምና ከአእምሮ ስቃይ እንዲጠበቁ ይፀለያል፡፡
② በመጋቢ፤ በወንጌላዊና በመሪ በኩል ስልጣንና ተሃድሶ እንድናደርጉ ይፀለያል፡፡
ሁሉ ቦታ ቃል በሚሰበክበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ይዘን በቃል በኩል ሰዎችን መማርክ፤ እንዲፈወሱ ይጸለያል፡፡
③ የሚፈልገውን ሁሉ እንዲቀበሉ ይፀለያል፡፡
④ የሚፈልገውን ጥሩ ራእይ እንዲቀበሉ ይፀለያል፡፡
⑤ በችግሮች ጊዜ መንፈስ ቅዱስ አጥብቆ እንድጠብቅ ይፀለያል፡፡

3) እኔ ስለ መጋቢ፤ ስለ ወንጌላዊና ስለ መሪ እንዴት መፀለይ እንደሚገባ ጻፉ፡፡

4. ስለ ቤተ ክርስቲያን የጸሎት የስራ ዘዴ ማካፈል፡፡

1) በየግል ፀሎት

● ፊልጵ.1÷3-5

3-5 ሁልጊዜ በጸሎቴ ሁሉ ስለ እናንተ ሁሉ በደስታ እየጸለይሁ፥ ከፊተኛው ቀን እስከ ዛሬ ድረስ ወንጌልን በመስበክ አብራችሁ ስለ ሥራችሁ፥ ባሰብኳችሁ ጊዜ ሁሉ አምላኬን አመሰግናለሁ።

2) አብሮ መፀለይ

● መክብብ.4÷12

3- ከፀሐይ በታች በሚደክምበት ድካም ሁሉ የሰው ትርፉ ምንድር ነው?

4- ትውልድ ይሄዳል፥ ትውልድም ይመጣል ምድር ግን ለዘላለም ነው።

5- ፀሐይ ትወጣለች፥ ፀሐይም ትገባለች፥ ወደምትወጣበትም ስፍራ ትቸኵላለች።

● ሐዋ.12÷5

5- ጴጥሮስም በወጎኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።

3) ልዩ ጸሎት - በየቀኑ አንድ ላይ ሰዓትን በማስቆጠር ልዩ ጸሎት ይፀለያል።

● ያዕቆ.5÷15-16

15- እንዲህ ዐይነቱ በእምነት ላይ የተመሠረተ ጸሎት በሽተኛውን ያድነዋል፤ ጌታም ከበሽታው ይፈውሰዋል፤ የሠራው ኃጢአትም ቢኖር ይቅር ይባልለታል፡፡

16- ስለዚህ እንድትፈወሱ ኃጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፤ እያንዳንዱም ለሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት ብዙ ውጤት የሚያስገኝ ታላቅ ኀይል አለው፤

4) የጾም ጸሎት

● ኢሳ.58÷6

6- እኔስ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ፥ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቅቁ ዘንድ፥ የተገፉትንስ አርነት ትሰድዱ ዘንድ፥ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን?

5) ስለሌሎች በመፀለይ ልዩ ወታደር መሆን፡፡

ሙሴ፤ አሮንና ሑርም ታሪክ፤ - አንተ ሙሴ፤ አሮንና ሑርም ነው?

● ዘፀ.17÷10-12

10- ኢያሱም ሙሴ እንዳለው አደረገ፥ ከአማሌቅም ጋር ተዋጋ ሙሴና አሮንም ሑርም ወደ ኮረብታው ራስ ወጡ።

11- እንዲህም ሆነ ሙሴ እጁን ባነሣ ጊዜ እስራኤል ድል ያደርግ ነበር እጁንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር።

12- የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር ድንጋይም ወሰዱ፥ በበታቹም አኖሩ፥ እርሱም ተቀመጠበት አሮንና ሑርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር ፀሐይም እስክትገባ ድረስ እጆቹ ጠነከሩ

5. ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ሰው በኩል የእርሱን ስራ እንድንፈጽም ያደርጋል፡፡

ስለሌሎች በመፀለይ ዓለምን ማሸነፍ ይቻላል፡፡

1) ሰዎችን በምንመርጥ ጊዜ እግዚአብሔር መልካም ሰዎችን እንዲሰጥ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

● ማቴ.9÷37-38

37- በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን። መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤

38- እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው።

2) አገርና ወገን ሁሉ ኢየሱስን እንዳይሰሙ የሚያደርገውን የሰይጣን ስልጣን እንዲጠፋ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

● 2ኛ ቆሮ.4÷3-4

3- ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው።

4- ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።

3) የምስዮናዊዎች ሥራ እንዲባረክ መፀለይ ያስፈልጋል::

● ኤፌ.6÷18-19

18- በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤

19- ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፤

4) ዓለምን በወንጌል ለማስፋት የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ለማምጣት በደንብ መፀለይ ያስፈልጋል።

● ሐዋ.1÷8

8- ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

★ ማዋልና ማካፈል

1. እንደገና አዲስ ክርስቲያን እንዳለ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡ ስለ ትንሽ ቡድንን፤ መጋቢን፤ ወንገላዊን፤ መሪን፤ በተ ክርስቲያንን መፀለይ ያስፈልጋል፡፡ ስለ ፀሎት ፈለገ ከፃፋችሁ በኋላ እርስ በርስ ተካፈሉ፡፡

2. ስለ እኛ ቤተ ክርስቲያን፤ ስለ መጋቢ፤ ወንገላዊ ፤መሪዎች መቼ እንደምንጸልይ ከጻፋች በኋላ እርስ በርስ ማካፈል፡፡

① ስለ ሌሎች ጸሎት ማለት የእኛ ቤተ ክርስቲያን በኃይል እንድቀጠለ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡ ስለ ሌሎች ጸሎት ማለት የተሃድሶ ስራ ምንጭ ነው፡፡

② <u>የእኔ ቤተሰብ ጤናማ እንዲሆኑ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡ የቃል ስልጣን፤ የፀሎት ስልጣን ለመሪዎችና ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቶ በደንብ እንዲያገለግሉት ያስፈልጋል፡፡</u>

<u>★ ፀሎት</u>

<u>እኔ ስለሌሎች ጸሎት በኩል ታላቅ ተሃድሶ እንዲያደርጉ በደንብ ይጸለያል፡፡</u>

<u>ምዕራፍ ስድስት</u>

<u>ስለሌሎች የፀሎት ልምድ፤ ስለሌሎች የፀሎት ልዩ ወታደር</u>

● ማቴ.6÷33

33- ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።

<u>እግዚአብሔር በፀሎት ጊዜ በሰው በኩል ይሰራል፡፡ ወደ እግዚአብሔየር በሚፀልይ ሰው በኩል ዓለምን እንድ ወሰደ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የሚፀለይ ሰው የስራ ዋና ሰው ነው፡፡ ስለሌሎች የሚፀልይ ሰው ልዩ ወታደር ልምምድ ተቀብሎ ውጊያ ይችላል፡፡</u>

<u>1. ስለሌሎች መፀለይ በእርግጥ ስለ ጸሎት ቦታ ማካፈል፡፡</u>

<u>1) ስለ ቤተሰብ መፀለይ</u>

<u>2) ስለ ማያምኑ ሰዎች መፀለይ</u>

<u>3 ስለ ጎረቤታችን መፀለይ</u>

<u>4 ስለ ሥራ መፀለይ</u>

5 ስለ ቤተክርስቲያን መፀለይ

6 ስለ አገርና ስለ ወገን መፀለይ

7 ስለ አገር ሁሉ መፀለይ

★ ስለሌሎት የሚፀልይ ሰው ጥቅም ምንድን ነው?

ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ 3 ዓይነት ልዩ ወታደር አለ፡፡

3 አይነት ልዩ ወታደር ምንድን ነው?

① ስለሌሎች የሚፀለይ ልዩ ወታደር ነው፡፡

② የወንጌል ስብከት ልዩ ወታደር ነው፡፡

③ የማያምኑ ሰዊችን ሄዶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ማምጣት ልዩ ወታደር ነው፡፡

ጤናማና እድገት ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ስለሌሎች መፀለይ ልዩ ወታደር አለ፡፡

2. ስለሌሎች መፀለይ የስራ መፈለግ ትርጉም ምንድን ነው?

1) በመቀጠል በዝርዝር ስራ ይቻላል፡፡

● ዘፀ.17÷12

12- የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር ድንጋይም ወሰዱ፥ በበታቹም አኖሩ፥ እርሱም ተቀመጠበት አሮንና ሖርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር ፀሐይም እስክትገባ ድረስ እጆቹ ጠነከሩ።

2) በጦር ዕቅድና በፅኑ እምነት መጸለይ ይቻላል፡፡

● ዘፀ17÷10-11

10- ኢያሱም ሙሴ እንዳለው አደረገ፥ ከአማሌቅም ጋር ተዋጋ ሙሴና አሮንም ሖርም ወደ ኮረብታው ራስ ወጡ።

11- እንዲህም ሆነ ሙሴ እጁን ባነሣ ጊዜ እስራኤል ድል ያደርግ ነበር እጁንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር።

3) በጥሩ መፀለይ ይቻላል፡፡

● መክብብ.4÷12

12- አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።

4) ስለ ቤተክርስቲያን ጠንካራ መገናዘብን፤ ፍቅርን አለብን፡፡

● 1ኛ ቆሮ.12÷26-27

26- አንድም ብልት ቢሣቀይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሣቀያሉ፤ አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል።

27- እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ።

5) በመንፈስ ግንኙነት፤ ህብረትና የፈውስ ሥራ ልምምድ ይሆናል፡፡

● ያዕ.5÷15-16

15- የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል።

16- እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።

6) በስሜት ወንጌልን መስበክ ይቻላል፡፡

● ሐዋ.4÷17-21

17-ነገር ግን በሕዝቡ ዘንድ አብዝቶ እንዳይስፋፋ፥ ከእንግዲህ ወዲህ ለማንም ሰው በዚህ ስም እንዳይናገሩ እየዛትን እንዘዛቸው ብለው እርስ በርሳቸው ተማከሩ።

18- ጠርተውም በኢየሱስ ስም ፈጽመው እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዙአቸው።

19- ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰው። እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደ ሆነ ቍረጡ፤

20- እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው።

21- እነርሱም እንደ ምን እንደሚቀጡ ምክንያት ስላላገኙባቸው፥ እንደ ገና ዝተው ከሕዝቡ የተነሣ ፈቱአቸው፤ ሰዎች ሁሉ ስለ ሆነው ነገር እግዚአብሔርን ያከብሩ ነበርና።

7) በዝርዝር ስለ ሌሎች መፀለይ ሰዎችን ለመገንባት፤ መለማመድ ምቹ ጊዜ ይሆናል፡፡

● ኢሳ.62÷6-7

6-7 ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ጕበኞችን በቅጥርሽ ላይ አቁሜአለሁ ቀንና ሌሊት ከቶ ዝም አይሉም እናንተ እግዚአብሔርን የምታሳስቡ፥ ኢየሩሳሌምን እስኪያጸና በምድርም ላይ ምስጋና እስኪያደርጋት ድረስ አትረፉ ለእርሱም ዕረፍት አትስጡ።

★ ስለሌሎች መፀለይ ልዩ ወታደር 7 ዋጋ ምንድን ነው?

① አስቀድሞ የራሱ ነፍስን እንዲቀደስ መሞከር ያስፈልጋል፡፡
የፀሎት ስልጣን ከንፁህ ምንጭ ስለ ፈሰሰ ነው፡፡(መዝ.66🕑18)

② በእግዚአብሔር ፍቅር የምንረዳበትን ልብ መያዝ ያስፈልጋል፡፡

③ በድርጅቶች መቀጠል ሌሎች ስለ ፈለጉ በዝርዝር መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

④ ሌሎች ከፀሎት ሰዎች ጋር አንድ ልብ መሆን ያስፈልጋል፡፡

⑤ በፀሎት የሰይጣንን ስልጣን ማሰረ ያስፈልጋል፡፡

⑥ ማሸነፍንና መስበክ ያስፈልጋል፡፡

⑦ የተስፋን ቃል መናገር ያስፈልጋል፡፡

3. ስለሌሎች የፀሎት ልምድ ሥራና ስለ ዘዴ ማካፈል፡፡

1) ስለ መጋቢ፤ ወንጌላዊና መሪዎች፤ ስለ ቤተ ክርስቲያን መፀለይ፡፡
ምሳሌ፤ - በየሰኞ መፀለይ

2) እሁድ በአምለኮ ጊዜ መፀለይ፡፡
ምሳሌ፤ - እሁድ ቀን ከአምልኮ በፊት አንድ ሰዓት መፀለይ፡፡

3) ተራ በተራ መፀለይ፡፡
ምሳሌ፤ - በየቀኑ አንድ ሰዓት መፀለይ፡፡

4) ስለሌሎች ፀሎት ልዩ ወታደር፡፡
ምሳሌ፤ - ስለሌሎች የፀሎት ትምህርት ከጨረስ በኋላ ፀሎትን የሚያስፈልግ ሰው በየቀኑ አንድ ሰዓት ላይ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡
ይህ ማለት በየቀኑ አንድ ሰዓት ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጥቶ እንድ መፀለይ ማለት ነው፡፡

★ ስለሌሎች በመፀለይ ክፍል ውስጥ ተራ በተራ ፀሎት ማውጫ፡፡

ምሳሌ

① መዝሙር 5 ደቂቃ
② ስለ መጋቢ፤ ወንጌላዊና መሪ መፀለይ 10 ደቂቃ
③ ስለ ቤተ ክርስቲያን መፀለይ 10 ደቂቃ
④ ሌሎች የፀሎት ዘርዘር ካርድ ከአነበቡ በኋላ መፀለይ 15 ደቂቃ
⑤ ስለእኔ እና ቤተሰቤ መፀለይ 5 ደቂቃ
⑥ ስለማያምኑ ሰዎች መፀለይ 5 ደቂቃ
⑦ ስለ እኔ አገርና ወገን፤ ስለ ዓለም መፀለይ 5ደቂቃ
⑧ የምስጋና ፀሎት 5 ደቂቃ

4. ስለሌሎች መፀለይ ምላሽ 7 ደረጃ ምንድን ነው?

1) የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያደርግ በቃል በኩል ፅኑ እምነት መኖር ያስፈልጋል፡፡

● ኢሳ.55÷11

11- ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።

2) የእግዚአብሔርን ቃል በጥሞና ማንበብ፡ ፡

● መዝ.1÷2-3

2- ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል።

3- እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።

3) በዝርዝር ጌታን መለመን ያስፈልጋል::

● ማቴ.7÷7-9

7- ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል።

8- የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።

9- ወይስ ከእናንተ፥ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው?

4) የመንፈስ ቅዱስን መምራት መቀበል ያስፈልጋል::

● ሮሜ.8÷26

26- እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤

5) ያለ ጥርጥር ጌታን መመካት፡ ፡ እግዚአብሔር እንደሚያደርግ ተስፋ ያስፈልጋል::

● ያዕ.1🕑6

6- ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና።

● ኢሳ.43÷19

19- እነሆ፥ አዲስ ነገርን አደርጋለህ እርሱም አሁን ይበቅላል፥ እናንተም አታውቁትምን? በምድረ በዳም መንገድን በበረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ።

6) እኛ እንድንፀልይ እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደንሰጠ ማመስገን ያስፈልጋል፡ ፡

● 1ኛ ዮሐ.5÷14-15

14- በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል።

15- የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።

7) የምላሽ ምስክሮችን ፃፍ፡ ፡

● ኢያሱ.4÷5-7

5. ስለሌሎች የሚፀልዩ ሰዎች ልዩ ስልጣን እንድንሰጥ ፅኑ እምነት ያስፈልጋል፡ ፡

1) ስለሌሎች በፀሎት ሰው በኩል የእግዚአብሔር መንግስት ያድጋል።

● ሐዋ.4÷29-31

29- አሁንም ጌታ ሆይ፤ ዛቻቸውን ተመልከት፤ አገልጋዮችህ ቃልህን ያለ ፍርሀት በድፍረት እንዲናገሩ አድርግ፤

30- በቅዱስ ልጅህ በኢየሱስ ስም በሽተኞች እንዲድኑና ተአምራትም፣ ድንቅ ነገሮችም እንዲደረጉ እጅህን ዘርጋ፡ ፡"

31- ጸሎት ከጨረሱ በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ የእግዚአብሔርንም ቃል ያለ ፍርሀት በድፍረት ተናገሩ፡ ፡

2) በኢየሱስ ስም በስልጣንና በሃይል ይኖራል።

● ሐዋ.3÷6-10

6- ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።

7- በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና፥

8- ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፥ ይመላለስም ጀመር፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ።

9- ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲመላለስ አዩት፤

10- መልካምም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ስለ ምጽዋት ተቀምጦ የነበረው እርሱ እንደ ሆነ አወቁት፤ በእርሱም ከሆነው የተነሣ መደነቅና መገረም ሞላባቸው።

3) በእግዚአብሔር ክብር ውስት ይኖራል።

● 1ኛ ጴጥ.5÷10-11

10- በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁምል ያበረታችሁማል።
11- ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን።

4) ስለሌሎች የሚፀልይ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖር ሰው ነው።
● ዘፍ.18÷17
17- እግዚአብሔርም አለ፦ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን?

5) ለሰማይ አክሊል የሚዘጋጁ አሉ።
● 2ኛ ጢሞ.4÷7-8
7- መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤
8- ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።

★ ስለ ሌሎች መፀለይ ልዩ ወታደር ላይ ወታደራዊ ልምምድ ምንድን ነው?

① በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና በጥሞና መስማት ያስፈልጋል፡፡ (2ኛ ጢሞ.3÷17)
በእኛ ህይወት መሠረታዊ ልምምድ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በጥሞና መለማመድ ነው፡፡
የሚፀልይ ሰው የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማትና ስለሌሎች በሚፀልይ ጊዜ እግዚአብሔር ፈቃድ ማወቅ ያስፈለረጋል
እኔ በምፀልይ ጊዜ እግዚአብሔር በሚሰጠው ቃል መሠረት መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

② ራሳችንን በመቀደስ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ (2ኛ ጢሞ.2÷20-21)
መቀደስ ማለት የራስን የሚፈልገው ነገር ማድረግ ሳይሆን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ማድረግ ነው፡፡
አስቀድመን ከመቀደሳችን በፊት የእኛን ኃጢአት መመርመር ያስፈልጋል፡፡

③ ችግር ሲመጣ ማሸነፍ ያስፈልጋል (2ኛ ጢሞ.3÷10-12)
● 1ኛ ቆሮ.10🕑13
በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል፡፡

④ እኛ እስከምንጨርስ ድረስ መልካም የጦርነት ውጊያ መኖር ያስፈልጋል፡፡(2ኛ ጢሞ.4÷7-8)
ለእኔ የሚዘጋጀልኝን የፀጋ አክሊል አይቼ እስክጨርስ ድረስ በትዕግስት መቀጠል ያስፈልጋል፡፡
እኛ በትዕግስት በመቀጠል የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

★ ማዋልና ማካፈል

1. ስለሌሎች የመፀለይ ሥራ ስለፈለጉ ከፃፉችሁ በኋላ እርስ በርሳችው ተካፈሉ፡፡

2. ከሳምንት ራሱ ተራ በተራ ስለሌሎች መፀለይ እንድንችል ሰዓቱን መመርመር ያደርጋል፡፡

★ ፀሎት

በየቀኑ ስለሌሎች የፀሎትን ሕይወት እንድንኖር በደንብ እንፀልያለን፡፡